
መዝገበ ታሪክ



ክፍል ፪

«ተዘከሩ መኳንንቲክሙ ዘነገሩክሙ ቃለ እግዚአብሔር»
ዕብ 13:7

«የእግዚአብሔርን ቃል የነገሩአችሁን መምህሮቻችሁን አስቡ»
ዕብ 13:7

ከመምህር ጎሩይ ኤርምያስ

ጥቅምት 1995 ዓ.ም
አዲስ አበባ

© መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው

ታህሳስ 2001 ዓ.ም
አዲስ አበባ

አንደኛ ዕትም 1995 ዓ.ም
ሁለተኛ ዕትም 1997 ዓ.ም
ሦስተኛ ዕትም 1999 ዓ.ም
አራተኛ ዕትም 2000 ዓ.ም
አምስተኛ ዕትም 2001 ዓ.ም
ስድስተኛ ዕትም 2004 ዓ.ም
ሰባተኛ ዕትም 2004 ዓ.ም
ስምንተኛ ዕትም 2005 ዓ.ም
ዘጠነኛ ዕትም 2006 ዓ.ም

ይህን መጽሐፍ በአቲላ አቡነ ተክለሃይማኖት ገዳም በቅኔ መምህርነት ተመድቤ ሳስተምር በ1988 ዓ.ም አዘጋጀሁት፤ በልዑል እግዚአብሔር ቅዱስ ፈቃድ በጥቅምት ወር 1995 ዓ.ም አሳተምሁት።

ማስታወሻነቱ

ከ46 ዓመታት በላይ ትባኄ ሠርተው በማስተማር እያሉ ምዕራፉን ለቅድስት ቤተክርስቲያን ላበረከቱት ለእኔም በመንፈስ ቅዱስ አባቴና መምህሬ ለሆኑት ታላቁ የቅኔ ምሁር ለክቡር መምህር መንግሥቱ ዘለዓለም ይሁንልኝ።

በመጽሐፉ ሙሉ ዝግጅት ላይ አስፈላጊውን ሙያዊ አስተያየት ለሰጡኝ የቅኔና የወንጌል መምህሬን ለመምህር ዓምደ ወርቅ ደሴ እና መምህር ኢያሱ ገ/እልፋ፤ ለክፍል ፩ መጽሐፍ ሕትመትና እገዛ ላደረጉልኝ ለወንድሜ ፈቃዱ ገ/መሬድና ለ[illegible] ማተሚያ ድርጅት ኃላፊዎች እንዲሁም በማሠራጨት ለተባበሩኝ በሙሉ፤ አስተያየት ለሰጡኝ እና ይህን ጽሑፍ በኮምፒዩተር በመጻፍ ለተባበሩኝ ለወ/ት ሙብንሽ አዲሱ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

ማውጫ

ተራ ቁ		አርእስት
1		መግቢያ
2	ምዕራፍ	1 መዝገበ ታሪክ ዘመጋቢት
3	"	2 መዝገበ ታሪክ ዘሚያዝያ
4	"	3 መዝገበ ታሪክ ዘግንቦት
5	"	4 መዝገበ ታሪክ ዘሰኔ
6	"	5 መዝገበ ታሪክ ዘሐምሌ
7	"	6 መዝገበ ታሪክ ዘነሐሴ
8	"	7 መዝገበ ታሪክ ዘጳጉሜን
9	የግዕዝ ቅኔያት	

መግቢያ

የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ፡-

ክርስቶስ ኢየሱስ ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በዕሪና የሚመሰገን፤ በዚህ ጊዜ ተገኘ በዚህ ጊዜ ያልፋል የማይባል በባሕርይ ሁሉን የሚያውቅ የሚመረምር እርሱ ግን የማይመረመር ሁሉን በከሀሊነቱ ያስገኘ እርሱ ግን አስገኝ የሌለው ሁሉ በእርሱ የሆነ፣ ምንም ምን የሚሳነው የሌለ ዓለማትን ፈጥሮ የሚገዛ፣ በኋለኛው ዘመን ሰውን በኃጢአት ምክንያት ካጣ በኋላ ልጅነት ክብሩን ያጣ ሰውን ወደ ቦታው ወደ ክብሩ ይመልሰው ዘንድ ከንጽሕት ድንግል ማርያም ከግመረ ሥጋ ነፍስን ተዋሕዶ በድንግልና ተወልዶ በፈቃዱ ሞትን ሞቶ በትንሣኤው ድል ነሥቶ ለዓለም ፍጹም ድኅነትን የሰጠ። በክብር በምስጋና እንዳረገ እንዲሁ ለጻድቃን ሊፈርድላቸው በኃጥአን ሊፈርድባቸው በግርማ መለኮት በይባቤ መላእክት ዳግመኛ የሚመጣ ለኀልፈት የተፈጠረውን የሚያሳልፍ ለኀልፈት ያልተፈጠረውን በትንሣኤ የሚያድስ የሕያዋን ጌታ የነገሥታት ንጉሥ፣ የአማልክት አምላክ ገባሬ ፍጥረታት /ዮሐ 1:1፣14፣ ዮሐ 7:24፣ ሐዋ 1:11 ቆላ 1:14 20፣ዮሐ 1:20/ መሆኑን የምታምን የምታስረዳ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተገኘች እውነተኛና ቀጥተኛ ሃይማኖት ናት።

ይህች ሃይማኖት ለሰው ልጆች ድኅነት /ሕይወት/ መሠረት ናት። ስለዚህም ክርስቶስ መሠረታት ነቢያት ጸጎትዋት ሐዋርያት ሰበኩት ገለጧት፣ ሰማዕታት በሰላውያን ፊት መስክረው አንገታቸውን ለሰይፍ ሰውነታቸውን ለእሳት ሠውላት፣ ጻድቃን ዓለምን ንቀው ራሳቸውን ክደው ተከተሉአት ተገዙላት/ ሊቃውንት ከመናፍቃን ተከራከሩላት መከራም ተቀበሉላት፣ እምነ የነርሱ ቤቶች ተዋሕዶን በእኃንነት በመናፍቃን ከመዋጥ ታደጓት። ቤተክርስቲያን መከራውን ታግሠው ተቀብለው ይህቸን ርትዕት ሃይማኖት ጠብቃ በማቆየትና ለተተኪ በማስተላለፍ ታላቅ ውለታ የዋሉ /በጎ ሥራ የሠሩ/ ነቢያት ሐዋርያትን ጻድቃን ሰማዕታትንና ሊቃውንትን ሁሉም ስታስባቸው በጎ ሥራቸውንም ስትመሰክርላቸው ትኖራለች።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ከሐዋርያት ከሊቃውንት ሲያያዝ በመጣ ትምህርተ ሃይማኖትና ሥርዓቷ ላይ

በቀለያ መገበድ ትችት የሚያቀርቡ በተለይም እነሆን ራሳቸውን ለሃይማኖት አሳልፈው ቤዛ አድርገው የሠው ቅዱሳንን ማክበር ማዘከርን የሚቃወሙ፣ ባይረዱትም ተቀብለናል የሚሉትን ወንጌልን በዘሁኒዎችና ከተወራኞች የክህደት መንጋጋ ከመተረማመስ ታድገው ያቆዩላቸውን ባለውለታዎቻቸውን መዘንጋታቸው ግልጽ ነው። በሃይማኖትና በበጎ ምግባር አርአያ የሚሆኑ ቅዱሳን ሃይማኖታቸውና በጎ ምግባራቸው ወንጌል በተነገረበት ሁሉ በዝክራቸው ሊመሰክርላቸው እንደሚገባ ጌታ ክርስቶስ ኢየሱስ እማን እብልክሙ በኀበ ተሰብከ ዝ ወንጌል በኵሉ ዓለም

ዝክር ያገብእ ላቲ ዘገበረት ላቲ ብእሲት ወይእዜኒ እውነት እላችኋለሁ፤ በዓለም ሁሉ ይህ ወንጌል በተሰበከበት በታ ይህች ሴት ያደረገችውን ደግሞ ያሰቡአት ማቴ 26:13 ሲል ማርያም እንተ ዕፍረት ስለ ዕቀባችው ጊዜ ለሐዋርያት የተናገረውን፤ ቅዱስ ጳውሎስም መምህሮቻችሁን አስቡ ዕብ 13:7 ያለውን ሳያነቡ ቀርተው ከሆነ ወንጌሉን ተከትሎ ለመኖር እንጂ እንበ ለመጠቀም ባለመታደላቸው "የተማሪኖቻችሁን አትናቁም..." እንደተባለው ሆኑ ማለት ነው እጅግ ያሳዝናል። እንዲውቁት ከወንጌም እነርሱ ሊፈጽሙት ባለመቻላቸው ቁና ሙሉ ቅናት አድርጋቸዋል ማለት ነው። ለማንቸውም የቤተክርስቲያን ሥርዓቷ ምንም የማይወጣ ተገቢና እውነተኛ መሆኑን ሊረዱት ይገባል።

የዚህም መጽሐፍ ዓላማ ቤተክርስቲያን በሃይማኖትና በበጎ ምግባራቸው የምታስባቸውንና እንደ ወንጌልም ቃል ገድላቸውን የምትመሰክርላቸውን ቅዱሳንና በዓላቸውን ማስታወስ ነው። ከመስከረም 1 የዕለት 30 ቀን ድረስ ባሉት ዕለታት በዓል ተሠርቶላቸው የሚታሰቡትን ቅዱሳን እንዲሁም የጌታ፣ የእመቤታችንና የመላእክት በዓላት ታሪክ «መዝገበ ታሪክ ክፍል ፩» በሚል ርእስ ከዚህ በፊት ታትሞ መሠራጨቱ ይታወሳል። ይህም የዚያ ሁለተኛ /ተግባይ/ ክፍል ሆኖ ከመጋቢት 1 እስከ ጳጉሜን 5 ቀን ድረስ ባሉት ዕለታት የሚዘከሩትን የያዘ ነው ከጥር 1 መጽሐፉን ያዘ ምእመናን ታሪክ የተፈጸመበት ዘመን እንዲያውቁት በመፈለግ መሠረት ከዚህ መጽሐፍ በተመጠረበት መጽሐፍት ዋቢነት ረቂቁን ዘመኑን እያስተቸተ በድጋሚ ከፊያለሁ። የክፍል 1 ታሪኮች በመጀመሪያ በዚህ መጽሐፍ የመጨረሻ ገጾች ላይ ተገልጿል።

እንበብ እንድናበተወለው የእግዚአብሔር ፈቃድ ይሁንልን።

አሜን።

ምዕራፍ 1

መጋቢት 5 ዕረፍቱ ለአቡነ ገብረመንፈስ ቅዱስ

ሀገራቸው ንሂግ (ግብጽ) ነው። አባታቸው ስምዖን እናታቸው አቅሌስያ ይባላሉ። ልጅ አጥተው 30 ዘመን ሲያዝኑ ኖረዋል። አንድ ቀን አቅሌስያ ቤተእግዚአብሔር ገብታ ከስዕለ ሥላሴ ሥር ወድቃ ስትማፀን "ንግሥት ወልደ [illegible] .. ክብሩ ከሰማይ ከፍታ የሚበልጥ ልጅ እንዲ ተቀበጹ" የሚል ድምጽ ሰማች። በዚህም መሠረት አባታችን መጋቢት 29 ቀን ተጸንሰው ታኅሣሥ 29 ቀን ተወለዱ።

ዓይን በገለጡት ጊዜ ከሚታይ ነገር ላይ እንዲያርፍ አርጋቸውም በተወለዱ ጊዜ አፈፍ ብለው ተነሥተው "ስብሐት ለአብ ስብሐት ለወልድ ስብሐት ለመንፈስ ቅዱስ ዘአውፅአኒ እምጽልመት ውስተ ብርሃን" ብለው በማመስገናቸውና አሻም ምድራዊ መብል መጠጥ ሳይመገቡ ሳይጠጡ ለምስጋና ተግተው በመኖራቸው መላእክትን ይመስላሉ።

ሦስት ዓመት ሲሆናቸው ቅዱስ ገብርኤል ከእመቤታችንና ከብዙ ካሉ ቅዱሳን ዘንድ አስባርኮ ኀዳማውያን ካሉበት ምድረ ወሰዶ ከቡሩ እኖራቸው፤ እበምኔቱ አባ ዘመደብርሃን ምልክት ተነግሮት ቢጠብቅ ፍሁሓ ገዙ ሆነው አገኙአቸዋል። አባይን አስተምሮ ከመንግሥ ምንኩስና አድርጓቸዋል። ከዚህ በኋላ ሀብተፈውስ ተሰጥቷቸዋል። ባንድ ቀን እልፍ ዕውራን ሀንካሳን ፈውሰዋል። ኋላ ግን እሲስ ቆላላቱ ካህናቱ ዝናቸውን ሰምተው እየመጡ ግብር የሚያስፈፅቸው ቢሆን ቅዱስ ገብርኤል በክንፉ ነጥቆ ከጌታ ፊት አቀረባቸው። በገድልህ በትሩፋትህ ከምድር ነፍስ ክርድተ ገኘም የሚደርስ ብዙ ነፍሳት አሉና ከሰው ተለይተህ ወደ ሚካ ግባ። ኦርብም ከ60 አናብስትና ከ60 አናምርት ጋር ይሁን አላቸው። ጌታዬ ምን ተመግቤ ይኖራሉ? አሉት። "ዘሲሳዮ ሰብእ-ሰብአ ይሲስዮ ወበውእቱ ይጸግብ .. የፈጠረውን ትቢያ ልሰው ያለ ምግብ ሆዳቸው ይኖራሉ" ብሏቸው ዐርጓል። ገዳም ገብተው ከአናብስትና አናምርት ጋር ይኖሩ ጀመር። ዳንኤል ከአናብስት ጉድጓድ በተጣለ ጊዜ አናብስቱ እንደ ድመት ከእግሩ በታች ሆነው እንደተገኙ የፈጠራቸውን ትቢያ ይልሱ ይታዘዙዋቸውም ነበር።

በዚህ መልኩ 30 ዓመት ከቆዩ በኋላ ጌታ ባንድነት በሦስትነት ተገልጾ ምን ላደርግልህ ትሻለህ? አላቸው። መጀመሪያ [illegible] ምድረ ደምባልና የምድረ ዝናብ ሰዎች ማርልኝ አሉት። 3000 ኃጥአንን ከሲኦል አውጥቶ ገነት አገብቶላቸዋል። ከዚህ በኋላ

"ሑር ምድረ ኢትዮጵያ ወበሆኒ ሀሰውከ ንፍሳት ዘታወጽእሙ ወደ ኢትዮጵያ ሂድ" አላቸው፡፡ ቅዱስ ገብርኤል በሠረገላ ነፋስ ጭኖ ምድረ ክብድ አድርሷቸዋል፡፡ ዳግመኛም ወደ ዝቋላ (ደብር ቅዱስ) ወስዷቸው ከዚያ ሆነው በንጽሐ ልቡና የኢትዮጵያን ሕዝብ ኃጢአት አይተው ከዛሕሩ በራሳቸው ቆመው ይጸልዩ ጀመር፡፡ አርባ ቀን ሲሆናቸው መልአኩ መጥቶ "ዘገብረ ተዝካረከ ወዘጸውዐ ስመከ እምሕር ለከ ብሎሀል" አላቸው፡፡ መላ ኢትዮጵያን ካልማረልኝ አልወጣም ብለው መቶ ዓመት ሲጸልዩ ኖረዋል፡፡ ከመቶ ዓመት በኋላ ጌታ "ተንሥእ ወጻእ መሐርኩ ለከ ኩሉ ኢትዮጵያ ምሬልሀለው ውጣ" ብሏቸው ወጥተዋል፡፡

ከዚህ በኋላ ምድረ ከብድ ወርደው ከምድር በላይ ከሰማይ በታች ሆነው ሰባት ዓመት እንደ ትኩል ዓምድ ሆነው፣ ዓይናቸውን ሳይከድኑ ሰባት ዓመት ቆመው ጸልየዋል፡፡ ሰይጣን ለምቀኝነት አያርፍምና ቁራ መስሉ መጥቶ ዓይናቸውን አንቁሮ አሳወራቸው፡፡ ሁለት ሰባቱ ሲፈጸሙ ቅዱስ ሚካኤልና ቅዱስ ገብርኤል መጥተው እፍ ብለው አድነዋቸዋል፡፡ ከዚያ ተነስተው ወደ ዝቋላ ሲሄዱ ሥላሴን በእምሳለ አረጋውያን ከጥላ ሥር አርፈው አገኟቸው፡፡ በእግዚአብሔር ዙፋን ተማጽነናል እዝለሁ አንድ አንድ ምዕራፍ ሸኙን አሏቸው፡፡ አዝለው ከሸኙአቸው በኋላ በአንድነት በሦስትነት ሆኖ ታያቸው፤ ደንግጠው ወደቁ፡፡ እንሥቶ ዝቋላ ወርደህ ጠላቶችህን ተበቀላቸው አላቸው፡፡ በዘበነ መብረቅ ደርሰው ሰባቱን ሊቃነ መላዕክት አጋዥ አድርገው እልፍ አእላፍ አጋንንትን በመብረቅ አጭድዋል፡፡

አባ ሳሙኤል ዘዋልድባ፣ አባ እንበሴ ዘሐዘሎ እና አባ ብንያም ዘግብጽ ዜናቸውን ሰምተው አናብስቶቻቸውን አስከትለው ሊጠይቋቸው መጡ፡፡ በሰባተኛው ቀን ተገለፁላቸው፡፡ አናብስቶቻቸው በርሳቸው አናብስት ተውጠው አዝነው ነበርና አናብስቶቻቸውን ጌታ ያዘዛችሁ የእግሬን ትቢያ እንጂ ሥጋና ደም ነውን? ትፉ ብለው ካስተፏቸው በኋላ ቢባርኳቸው ተንሥተዋል እነርሱም ርኢ መንክረ ... አባ እያሉ ተመልሰዋል፡፡

ከዚህ በኋላ ወደ ምዕራብ ሀገር ወሰዳቸው፡፡ የዐረብ ንጉሥ በማያታቱ ያደሩ አጋንንት ፈርተው ሲሸሹ ማያታቱ ሲሰባበሩ አይቶ ሰውነታቸው የሐር ፈትል በመሰለ ፀጉር የተሸፈኑ ነበርና አንተ ፀጉር ልብሱ ምንድር ነህ ሰው ነህን? አላቸው፡፡ እምን ሰማይና ምድርን በፈጠረ በኢየሱስ ክርስቶስ የማምን ሰው ነኝ አሉት፡፡ አይሁድ ሰቅለው ባደሉት ሰው ታምናለህን? አላቸው፡፡ አፍርበት መስሉሁልን እንተም ብታምንበት የዘለዓለም ሕይወት ባገኘህበት ነበር አሉት፡፡ እሳት አንድዱና አቃጥሉት አለ፡ አነደዱ፡፡ ግንም ግድ ሳይላቸው

በፈቃዳቸው ከእሳቱ ገብተው ወጡ ከሠራዊቱ ብዙዎች አመን አሉ፡፡ በሰይፍ አስፈጃቸው፡፡ እርሳቸውንም ሲመታቸው ሲቃጣ መብረቅ ወርዶ ከነተከታዮቹ ፈጅቷቸዋል፡፡ ወዲያውም መላእክተ ጽልመት ነፍሶቻቸውን እጅ ሲያደርጉ አይተው ይህ ሁሉ በኔ ምክንያት አይደለምን? ብለው ከታላቅ ገደል እግራቸውን በገመድ አስረው ቁልቁል ተሰቀሉ፡፡ ሰይጣን ገመዱን በጠሰው፡፡ ቅዱስ ሚካኤል ተቀበላቸው፡፡ ተወኝ በራሴ ልቁም አሉት፡፡ በራሳቸው ቆመው በጥርሳቸው ደንጊያ ነክሰው 30 ዘመን አልቅሰዋል፡፡ ጌታ ምሬልሃለሁ ብሏቸው ደንጊያውን ሲጥሉት አራት ጥርሶቻቸው በደንጊያው ላይ ተተክለው ቀርተዋል፡፡



መስቀሉን እንደፀሐይ ሲያበራ አገኘው፡፡ ቢይዘው አቃጠለው፡፡ ከዚህ በኋላ ሁሉቱን ዲያቆናት አሸከሞ ሲላውንም ንዋያተ ቅድሳት ዘርፎ ወደሀገሩ ተመለሰ፡፡

የሮም ንጉሥ ሕርቃል ይህን በሰማ ጊዜ እጅግ አዘነ፡፡ ግብር ገብቶ ቀኖና ይዞ አንድ ሱባዔ ሲፈጸም ፈቃደ እግዚአብሔር መሆኑን ተረድቶ በእቀጅ ዘምቶ ድል ነሣው፡፡ መስቀሉም ያለበት ጠፍቶት ሲቸገር ሲቀብር ዲያቆናቱን ሲገድል በመስኮት ሆና ያየች ከኢየሩሳሌም የተማረከች አንዲት ብላቴና አሳይታው አውጥቶ በልብሰ መንግሥቱ ጠቅልሎ ወደቁስጥንጥንያ ወስዶታል፡፡
• ታሪኩ የተፈጸመው በ614 ዓ.ም ነው፡፡/1/

መጋቢት 11 - ዕረፍቱ ለአባ አሌፍ ዘእም ፱ ቅዱሳን

መጋቢት 12 በዓሉ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ.መ

(1) ገሪ የቤ/ክ ታሪክ በዓ.መ ገጽ 145

በዚህ ዕለት ወደ በለዓም ተልኳል፡፡ ሀብተ መርገም የተሰጠው ነውና እስራኤል ከምድረ ግብጽ ወጥተው አርባ ዘመን በረሀ ለበረሃ ተጉዘው ሞአብ ሲደርሱ የሞአብ ንጉሥ ባላቅ ወልደ ሶፎር ግብጻውያንን በዘጠኝ መቅሰፍት በአሥረኛ ሞተ በኩር በአሥራ አንደኛ ስጥመት ያጠፋ! ጦር የማይመልሰው ጽኑ ጠላት ተነሥቶብኛል መጥተህ ርገምልኝ ብሎ እጅ መንሻ እሲያ ላከበት፡፡ ዋሉ እደሩ አላቸው፡፡ ሌሊት ወደጌታ ቢያመለክት አትሂድ አለው፡፡ አልሆነም ሂዱ እጅ መንሻው ቢያንስበት መልእክተኞቹ ተራ ቢሆንብት ይሆናል ብሎ እጅ መንሻውን በርክት አድርጎ ሹማምንቱን ላከ፡፡ ዋሉ እደሩ ፈጣሪዬን ልጠይቅ አላቸው፡፡ ዋሉ እደሩ፡፡ ወደ ጌታ ቢያመለክት ሂድ ነገር ግን አትርገም አለው፡፡ ሂድ ብሎ አትርገም ማለት እንደምን ነው? ከሄድኩስ የማደርገውን አውቃለሁ ብሎ የሚረገመውን እያሰበ ሲሄድ ቅዱስ ሚካኤል ሰይፉን መዞ ለአህያው ታያት ፈርታ ቆመች፤ ሂጂ እያለ መላልሶ መታት፡፡ በሦስተኛው ከቅጽርና ከቅጽር መካከል ይዞው ገባች እግሩን ጋጠችው፡፡ አርጌ ነቢይ ብለሽ ነው እንዲህ የምትጫወቺብኝ፧ ወይኔ ጦር በያዝሁ በወጋሁሽ ሰይፍ በያዝሁ በቀላሁሽ ነበረ አለ፡፡ በሰው አንደበት "አኮኑ እድግትከ ዘትጼዕነኒ እምንዕስከ-ከልጅነትህ ጀምሮ የምትቀመጥብኝ አህያህ አይደለሁ ምን፧ እስከ ዛሬ ሚዳውን ሩጪ ዳገቱን ወጪ ብትለኝ እንቢ እውቃለው፧ አለችው፡፡ እውነትሽን

ነው አለ፡፡ በዚህ ጊዜ መልአኩ ተገለፀለት፤ ከአህያው ወርዶ ሰገደለት እነሆ መንገድህ በፊቴ ጠማማ ነውና ለቅቃያህ መጣሁ፤ ለምን አህያህን መላልሰህ መታሃት፧ ብሎ ገሠጸው፡፡ እርሱም በግንባሩ ተደፍቶ ከሰገደለት በኋላ ልመለስን? ብሎ ጠየቀ መሄዱን ሂድ ነገር ግን እግዚአብሔር የገለጸልህን እንጂ ሌላ እንዳትናገር እወቅ አለው፡፡ ሄደ፡፡ ባላቅ ደስ አለው፡፡ ሰለመጣሁ ደስ አያሰኝህ የምናገረው እግዚአብሔር የገለጸልኝን ብቻ ነው አለው፡፡

ከዚህ በኋላ መሥዋዕት መቶ ከመሥዋዕትህ ቁም አለው፡፡ ወደ ምሥራቅ ተሂዶ "ምንተ እረግም ዘእግዚአብሔር ኢረገሞ፤ ምንተ እጸልእ ዘእግዚአብሔር እጸልእ-እግዚአብሔር ያልረገመውን በምን ነገር እረግማለሁ እግዚአብሔር ያልጠላውን በምን ነገር እጠላለሁ" አለ፡፡ ርገምልኝ ብልህ ትመርቃቸዋለህን፧ አለው፡፡ የገለፀልኝን ብቻ እናገራለሁ አላልሁምን? አለው፡፡ ሁለተኛ መሠዊያውን ከፍ አድርጎ ሠርቶ መሥዋዕቱን ጨምሮ መቶ ርገምልኝ አለው፡፡ እሱንም እያሟረተ ወደ ምሥራቅ ተሂዶ "ከተራሮች በላይ አየሁት ከኮረብታዎችም በላይ አስተዋልሁት እግዚአብሔር እምላኩ ከርሱ ጋራ ያለ ሕዝብ ከሀገሮች ይናራል" አለ፡፡ ባላቅም ርገምልኝ ብልህ ሁለተኛ ትመርቃቸዋለህን? ብሎ አዘነ፡፡ በሦስተኛ ከሌላ ኮረብታ ወስዶ ርገምልኝ አለው፡፡

"ሚ ይሤኒ ተዓይኒከ ያዕቆብ ወአድ እብያቲከ እስራኤል - ያዕቆብ ከተማህ ምን ያምር፧ እስራኤል ቤቶችህ ምን ያምር" ብሎ አደነቀ እምነሰ፡፡ እያይዞም "ይወፅእ ኮከብ እምያዕቆብ ወየአትት ኃጢአተ እምእስራኤል" ብሎ የጌታን ሥጋዌ ተናገረ፡፡ ርገምልኝ ብልህ ሦስተኛ ትመርቃቸዋለህን? አለው፡፡ እግዚአብሔር የገለጸልኝን ብቻ እንድናገር አስታውቁህ የለምን? እሁንም የምትቀምቸው ተፋታቸውን ከሆነ ረገሜ ላጠፋለሁ ... ደናግሉን ጣኦት እሳዝለህ መሥዋዕተ እርያ አሲዘህ ስደዳቸው፤ እንድረክብቸሁ ይሏቸዋል ... ብሎ ... ከዚህ ጊዜ እምላካቸው ተቆጥቶ ያጠፋቸዋል ብሎ መከረው፡፡

እንዳለውም ደናግሉን ጣኦት አሳዝሉ መሥዋዕተ እርያ አሲዞ ለደላቸው፡፡ ተቀመጣቸው፡፡ ለጣዖት ሰገዱ መሥዋዕታቸውን በሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ቸነፈር ይፈጃቸው ጀመር፡፡ የይሁዳ ቤት አለቃ ዘምሪ ከስምዖን ቤት አለቃ ልጅ ከከስቢ ጋር ተጠቃቅሰው ከእልፍኝ ሲገቡ አንድ ብላቴና አይቶ ለፊንሐስ ወልደ አልአዛር ነገረው፡፡ ሁለቱንም ከተኙበት በጦር ወጋቸው ጌታም ፊንሐስ ወልደ አልአዛር አስተንፈሰኝ ለልብየ-በሉታል፡፡ መቅሰፍቱም በምሕረት መልሶቸዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ለፊንሐስ 300 መሥዋዕት ከሀነት ተሰጥቶታል፡፡
ዘኁ ምዕ 22 እና 23

በሌላ ጊዜ ሲመለሱ ጥርሶቻቸው በተተከሉበት ደንጊያ መንፈስ ደስ የሚያሰኝ የሽቱ እንጨት ደግቶ ከጠበበትም ወደን በቅሉበት አግኝተዋል፡፡

እንዲህ ለበጋ ዕፅው በሆነ ግብር 262 ዓመት በኢትዮጵያ ኖረው በ562 ዓመታቸው በተሰፋቸው ያመነውን በኪዳናቸው የተማፀነውን ጌታ ከመከራ ሥጋ ከመከራ ነፍስ ሲምርላቸው ተስፋቸውን ተቀብለው በዚህ ዕለት - በዕለተ እሁድ ዐርፈዋል፡፡ መላእክት በአክናፈ እሳት ኢየሩሳሌም ወስደው በየማነ ምስዋዕ ቀብረዋቸዋል፡፡

ገብረ መንፈስቅዱስ የአምላክ አገልጋይ
ለኢትዮጵያ ብርሃን ነህ ፀሐይ
እናብስት እናምርት ሲታዘዙህ ኖሩ
የአግርህን ትቢያ ልሰው እያደሩ
ፈጣሪን በሀም ስለተማፀኑ
ኃጢአን ከሲኦል ከማም ...

እንደሰማይ መልአክ ቢሆንም ኑሮህ
የአባም ልጅ ነህ እንተም ዋንኛ ምትህ
ምስጋና ቀስዝህ ልብህ የአምላክ ጸጋ
እንተን ለማወደስ ነፍሴ ሁሌም ትትጋ
የጻድቅ ሰው ጸሎት በብዙም በሥጋ
ታማልአችና ለማያቋ ቀጋ

ሮሜ 12፡12 1 15፡30 ያዕ 5፡16

❖ ወደኢትዮጵያ የመጡት በቅዱስ ላሊበላ ዘመነ መንግሥት መሆኑ ለማያሳውቅ የዕፍረት ከ9 - 14 ኛው ም.ዓ ድ/ል/ክ/ መሆኑ ነው፡፡

መጋቢት 8 - ዕረፍቱ ለማትያስ ሐዋርያ

ማትያስ ማለት ምትክ ማለት ነው፡፡ ጌታ ካረገ በኋላ ሐዋርያት መቶ ሃያ ሆነው ከእመቤታችን ጋር ሆነው በጽርሐ-ጽዮን - በማርያም እመ ማርቆስ ቤት - ለጸሎት ይተጉ ነበር፡፡ አንድ ቀን ቅዱስ ጴጥሮስ ከእኛ ጋር የነበረ አስቆሮታዊ ይሁዳ ሳኖት "ወይኩና መዋዕሊሁ ኅጹጸ ወኪመቶሂ ይንሣእ ባዕድ - ዘመናቱ ጥቂት ይሁኑ ሹመቱንም ሌላ ይውሰድ" መዝ 108፥8 ብሎ ትንቢት ተናግሯልና ከኛ ጋር ከሚቴቱ ወንድሞች አንዱን መርጠን ይሾም አለ፡፡ የሴፍንና ማትያስን አቁመው እኛ ባውቅን የሴፍንና ማትያስን መርጠናል፡፡ አንተ እግዚእ ማእምረ ከሉ ልብ አርአይ እሐደ እምእሉ ዘኅረይከ ዘይነሥእ ላዕተ መልእክተ ሢመተ ሐዋርያት ዘነ ዳጋ ይሁዳ ይሰጥር ... ከሳሊት ያመላለሰውን ልብ ያሰበውን መርምረህ የምታውቅ ሆይ ይህችን የሐዋርያት ሹመት ገንዘብ የሚያደርጋትን ከእነዚህ ከሁለቱ የመረጥኸውን ግለጽልን "ብለው ጸልየው ዕጣ ሲያጣጥሏቸው ለማትያስ ወጣ፡፡ የዚህ ጊዜ አሥራ ሁለተኛ ሐዋርያ ሆኖ ተቆጠረ፡፡ ሐዋ 1፥13 ፥ 20

ከበዓለ ሃምሳ በኋላ መዲናቸው ኢየሩሳሌምን ዓመት አስተምረው ዓለምን ተከፋፍለው ለማስተማር ዕጣ ሲጣጣሉ ለርሱ ሀገረ በላዕተ ሰብእ ደረሰው፡፡ በዚህ ሀገር ያሉ ሰዎች እንደ አራዊት ሥጋ

የሚመገቡ ነበሩ፤ ከአደባባያቸው ገብቶ ሲያስተምር ይዘው ዓይኑን አውጥተው እንደላም ሣር እየመገቡ ከዘግ ቤት አስቀመጡት፡፡ በ40 ቀን ዓይኑ ምድሩ ሲሰወጥ አይተው ሊመገቡት ነው፡፡ ከዚህ አስቀድሞ ግን ጌታ ሐዋርያው እንድርያስን ልከለት ዓይኑን ፈውሶት ከእስሩ ፈትቶት ወጥተው ሲያስተምሩ ሊጣሏቸው መጡ፡፡ ወደ ጌታ ቢያመለክቱ ው፡ እስከ አንገታቸው አጥለቀለቃቸው ኋላ ግን ጸልየው አድነዋቸው እምነው ተጠምቀዋል፡፡ ባሕርያቸውም ተመልሶላቸው እሀል የሚመገቡ ሆነዋል፡፡ ከዚህም የበሰጠ ቤተክርስቲያን አሳንጸ ቀሳውስት ዲያቆናትን ሸሞ ሥጋ ወልደ እግዚአብሔር ደመ ወልደ እግዚአብሔር የሚመገባቸው ሆኗል፡፡ "ከቶና ማትያስ በዓዕለ - እኩያን ኅረ፤ ሥጋ ወልድ ቅዱስ ሲሰጦሙ ወደም ከቡረ፤ ተወላጠ ሲሰይም ሎቱ ከመላሀም "ግዕረ" እንዲል አርኬ፡፡

ሠላሳ ዘመን ካስተማራቸው በኋላ ወንጌል ካልደረሰበት ለማዳረስ ደማስቆ ወረደ፡፡ አረማውያን በብረት አልጋ አስተኝተው ሃያ አራት ቀን እሳት ሲያነዱበት ቆይተዋል፡፡ እርሱ ግን ሰውነቱ አምር ገዱ ደምቆ ይገኝ ነበር፡፡ በዚህ እምነው ተጠምቀዋል፡፡ በመጨረሻም በይሁዳ ከተሞች እየተዘዋወረ አስተምሮ በዚህ ዕለት በሰላም አርፏል፡፡

ፈሱን አዋርዶ ለሰወንጌል ከብር
ማትያስ እንደላም ተመገበ ሣር፡፡
አንዲሸጋገሩ ከሞት ወደ ሕይወት
ተግሩ ቢላቸው የወንጌልን ትምህርት
እንደእሁል ተቀሰት አቃጠሉት በእሳት፡፡
አሉ አለማቀ ልብ ደንዳኔት!

ኦሕዘብ ተገዝዘው በገዥ ሲያስታቀት
ይስልስ ነበረ እንዲያየኸ ምሕረት፡፡
ከተውን በከተ መመለስ ቀላል
ቢከተድም መታገሥ ዋጋ ያሰጣል፡፡
ግልፍ በጥንት ውስጥ መከራን መታገሥ
ምኘነት አይደለም መድኃኒት ነው ለነፍስ፡፡

ሮሜ 12፡ 12 1 ቆሮ 4፡12 2 ቆሮ 4፡18

መጋቢት 10 - መስቀል

በዚህ ዕለት ጌታ የተሰቀለበት መስቀል በተለያዩ ጊዜያት በተለያዩ ሰዎች እማኅደነት ሁለት ጊዜ ከተቀበረበት ወጥቷል፡፡ መጀመሪያ በንግሥት ዕሌኒ ከኢየሩሳሌም፣ ሁለተኛ በንጉሥ ሕርቃል ከፋርስ ወጥቷል፡፡ "ወበዛቲ ዕለት እንበለ ድልዕ ጊዜሁ፡ መስቀል ተረክበ እምዘተ ኀበ ወገብረ ሰላመ፡ በኢየሩሳሌም ትድመ ወበፋርስ ዳግመ" እንዲል አርኬ፡፡

የኢየሩሳሌሙ በክፍል 1 መጽሐፍ በገጽ 32 ተጽፏል፡፡ የፋርሱ ግን እንደሚ፡፡ መላፍንቱ ፋርስ ግብጽ ዘምተው ድል ነስተው ሲመለሱ ከመከልቶቻቸው አንዱ ኢየሩሳሌም ወርጀ አይሁድን ግርኬ እመጣለሁ ብሎ እገረ መንገዱን ወደ ኢየሩሳሌም ወርዶ አይሁድን ግርኬ ሲመለስ ንግሥት ዕሌኒ በብልሃቷ ካሠራችው ቤተ መቅደስ ቢገባ

• ታሪኩ የተፈጸመው በ1280 ዓ.ም ገደማ ነው፡፡

መከራና ችግር የማይለውጠው
ጠላት ተመቅኝቶ የማያጠፋው
ቢታመም የማይጠ ወድቶ ሚነሳው
እግዚአብሔር ከርሱ ጋር ያለለት ሰው ነው፡፡
ያን ምኞቱን ወሰዶ ምን ያስጠንቅቃል
ጌታ ካበረሰው ማን ያጥርጸዋል?

ስው ለምን ይለፋል እያለው ገብቶ
ያለ አምላክ ፈቃድ እንዳች ሳይሆን ከቶ፡፡
በነ በነ እለሁ በነ ከለዓ
ሁልጊዜ ደግፋል እግዚአብሔር አብሮህ
እግዚአብሔር ካለ ሁሉ በንገሀ
ከፈትህ ለመቆም ያፍሬል ጠላትህ፡፡

መዝ 22፥4 ሮሜ 8፡3

መጋቢት 13 አርባዓ ሐራ ሰማዕት

የብስጥያ የጦር ሠራዊት ነበሩ፡፡ የብስጥያው መስፍን ሊሞት ንጉሡ ቁስጠንጢኖስ አልፍያኖስን መስፍን-ብስጥያ አድርጎ ሾመው፡፡ ለጊዜው ከክርስቲያን ጋራ እተባበራለሁ እብያተ ክርስቲያናትን አንጸለሁ ብሎ ተሾሞ ነበረ፡፡ ኋላ ግን የወርቅ የብር ምስል አቁሞ ሃይማኖታችሁን ካዱ ለጣዖት ስገዱ አለ፡፡ ብዙዎች ከመሞት መሰንበትን ሽተው ሃይማኖታቸውን ክደው ለጣኦት ሲሰግዱ እነዚህ አርባው ሃይማኖታችን እንክድም ለጣኦት እንሰግድም አሉ፡፡ ሥጋቸው እስኪተራተር ድረስ አስገርፎ ወርጨው በውኃት ከሚገበጣው ጥልቅ የውኃ ጉድጓድ ጣላቸው፡፡ ሠላሳ ዘጠኝ ቀን ሲመላቸው ከሁሉ አንዱ መከራውን ጸልቶ ሥጋቸን ተሰቶ ወጣ፡፡ በማግሥቱ አርባ አክሊላት በሰማይ ረበው ሠላሳ ዘጠኙን ሠላሳ ዘጠኙ ሲቀዳጁ አንዲቷ ተንጠልጥላ ቀረች፡፡ ይህን አይቶ አንድ አረማዊ አምኖ ዘሎ ገብቶ ተቀብሏታል፡፡ ከዚህ በኋላ እልፍያኖስ ሥጋቸውን ስበረቸው አለ፡፡ ቢሄዱ አርፈው ተገኝተዋል፡፡

• ታሪኩ የተፈጸመው በ4ኛው ም.ዓ ድ-ል-ክ ነው፡፡

ትጠጊ ቢመርም የተከለ ትዕግሥት
ፍሬዋ ጣፋጭ ነው እንደወለበ ጸጋ
ረሀብ ጥም እርዝ ችግር ካለመመ
ፀንቶ ከተገኘ ሁሉጊዜ በትዕግሥት
የክርስቶስ ወዳጅ ብቻ እርሱ ነው ነው፡፡
መከራን መታገሥ ... የገው
መስቀሉም ፀጋ ነው የአወነቶቹ ምእመን
የምን ተስፋ መቁረጥ ፈጣሪ ግግሪር
ከተ ምን አለና የማያልፍ ዘለዓም ምድር

ትናንት የበረው ዛሬ ካልታየም
ዛሬም ያለው ነገ ካልተደገመ
እንዲያው ሁሉም ነገር ከተለወጠ
አንዳችም አይበጅም ተስፋ መቁረጥ
መታገሥን ግን መልካም ይሆናል ግን
ቸገር ተስፋው ልበ እንዲሁ ልክም
የታገሠ ክብርን ሳያገኝ አይቀርም፡፡

ሉቃ 22፡15 1 ጴጥ 2፡14 3፡16 ፡ 4፡12

መጋቢት 21 ትንሣኤ አልዓዛር

በጌሉ የጌታ ወዳጅ ነው፡፡ በዚህ ዕለት አልዓዛርን ከሞት አንሥቶታል፡፡ ወዙ እልፉ ብሌ ዘደደዊ ... አልዓዛር

በቢታንያ ዘሀገረ ማርያ ወማርታ ይላል፤ አልዓዛር ሞተ፤ ቢሞት እኅቶቹ ማርያምና ማርታ ወዳጅህ ሞተ ብለው ላኩበት፡፡ ወያፈቅሮን እግዚእ ኢየሱስ ለማርያ ወለማርታ እኅታ ወለአልዓዛር ይላል ይወዳቸው ነበረ፡፡ ሁለት ቀን ካለበት ውሉ ዓርብ ጉ ንሑር ብሔረ ይሁዳ - ወደ ይሁዳ እንሂድ አላቸው፡፡ አይሁድ በደንጊያ ወግረው በእሳት ተከሰው ሊገድሉህ ሲፈልጉህ እንሂድ ትላለህን? አሉት፡፡ አልዓዛር ዐርከነ ሞተ ወዳጃችን አልዓዛር ሞተ አላቸው፡፡ ቢታንያ ቀርበው እደሩ፡፡ ቢነጋ ማርታ መምጣቱን ሰምታ ከመንገድ ተገናኝታ ረበስ ሀሉከ ዝየ እምኢሞተ እኁየ ከዚህ ኑረህ ቢሆን ወንድሜ ባልሞተም ነበረ፡፡ አሁንም ጌታ (አብ) የለመንከውን እንዳይነሳህ አውቃለሁ አለችው፡፡ ዘየአምን ብየ እመኒ ሞተ የሐዩ - በኔ ያመነ ቢሞትም ይነሳል አላት፡፡

ማርያ(ም) ከቤት ነበረች፤ ናሁ መጽአ ሊቅነ ብላ ማርታ ነገረቻት፡፡ እየተቻኮለች ተነሥታ ወጣች፡፡ አብረዋት የነበሩትም ከመቃብሩ ሄዳ ልታለቅስ ነው ብለው እያለቀሱ ተከተሏት፡፡ እጅ ነሥታ እሷም እንደ እኅቷ ረበስ ሀሉከ ዝየ እምኢሞተ እኁየ አለችው፡፡ ወአንብዐ ካዐበ እግዚእ ኢየሱስ ይላል እንባውን አፈሰሰ፡፡ አይቴ ቀበርክምዎ - የት ቀበራችሁት? አለ፡፡ መለኮትስ ሁሉን ያውቃል እንዲህ ማለቱ ግን ሥጋን መዋሐዱን ለማጠየቅ ነው፡፡ ወሰደው አሳዩት መቃብሩ ዙሪያውን የታነጸ ከላይ በታላቅ ደንጊያ የተገጠመ ነበረ ደንጊያውን አንሡት አላቸው፡፡ ማርታ እግዚኦ ናሁ ወድአ ጺአ - ከሞተ አራት ቀን ነውና ፈጽሞ ተበላሽቶ ይሆናል አለች፡፡ ብታምኚስ የእግዚአብሔርን ጸጋ ታያለሽ አላት፡፡ ወዲያውም አባቱን አመስግኖ አልዓዛር አልዓዛር ነዓ አፍአ - ና ውጣ አለው፡፡ ወወጽአ ውእቱ ምውት እንዘ ግኑዝ ወእሡር እደዊሁ ወእገሪሁ ይላል - እጅ እግሩ እንደታሰረ ወጥቷል፡፡ ለጊዜው ምትሐት መስሏቸው ነበርና ፍቱት ይሂድ አላቸው፡፡ ፈትተውት በመካከላቸው እየተመላለሰ አመስግኗል፡፡
ዮሐ 11፥1-45
ኋላም በቆጵሮስ ኤጲስ ቆጶስነት ተሹሞ አርባ ዘመን አስተምሮ ግንቦት 26 ቀን በሰላም አርፏል፡፡
• ጌታ ከሞት ያነሳው በ33 ዓ.ም አስተምሮ ያረፈው በ73 ዓ.ም ነው

ሊ. አግብኦተ - ግብር በቤተ ስምዖን

ከስቅለቱ ሰምንት ቀን አስቀድሞ ትላንት ከቤተ ስምዖን ግብር አገቡለት፡፡ አልዓዛርን ጨምሮ ደቀመዛሙርቱን ይዞ ግብር ቀረበ፡፡ ማርታ በጭር ታጥቃ ታገለግላቸዋለች፡፡ ወማርያስ ነሥአት ዕፍረተ

ለተረ ዘናርዱ ከበተቂስ ዘዕፀብ ሤጠ ወተቀብዐ ለእግዚእ ኢየሱስ ይላል ማርያም የከበረ ሽቱ ቀብታዋለች።
ይህስ እንደምን ነው? ቢሉ ይህች ማርያም ከእግር ጥፍሯ እስከ ራስ ፀጉሯ ድረስ ተረሸ የማትባል ቆንጆ ነበረች። ውበቷን በመስታወት አይታ ይህ ሁሉ ማማር ከንቱ መሆኑን ተረድታ ኃጢአቷን እንዲያስተሰርይልኝ ሽቱ ገዝቼ ከመምህሬ ዘንድ ልሂድ ብላ በአስባ ደስ የሰበሰበችውን 300 ወቄት ወርቅ ይዛ ልትገዛ ስትሄድ ሰይጣን የምታውቀው ወዳጇን መስሎ ከነጋዴ ቀድሞ ወዴት ትሄጃለሽ? አላት ዝም አለችው። እንግዲ ወንድ መተቀብሽ ሽቱ ልትገዢለት አይደለምን? አላት። አዎን አለችው። ዳግመኛ ፍቅሩ ያስቀብለት ወንድ መተቀብሽ ሽቱ ልትገዢለት ይሆናል አላት። አዎን አለች። ምስተኛ ብዙውን በዋጋ የሚሸጥ ነጋዴ መተቀብሽ ነው አላት። አዎን አለችው። ሁሉንም አዎን አልሽኝ እውነቱ የቱ ነው? አላት። እንግዲ ወንድ አልሽኝ ከዚህ ዓለም ሌላ የሆነ! ፍቅሩ ያስቀብለት አልሽኝ የሰው ፍቅር አትበርት ሊሆት የመጣ! ብዙውን በዋጋ የሚሸጥ ነጋዴ አልሽኝ በዋጋ ትፋፋት ብሎ በረከት የሚሰጥ ክርስቶስ ኢየሱስ መጥቷል ለርሱ የምቀባው ሽቱ ልገዛ እሄዳለሁ ብላ በሙሉ ብትጠራበት እንደጠለ ተኖ እንደትቢያ በኖ ጠፍቷል።

ከዚህ በኋላ ሐድግክ ከሚገባ ነጋዴ ሄዳ ይትረከበሙ ዐብሊ ቅብዐ አፈው ዘይደለ ለነገሥት ለነገሥታት የሚገባ ሽቱ ካለህ ስጠኝ ብላ 300 ወቄት ሰጠችው። ሽቱ ሰሎሞን ተቀብተውለት የተረፈ ጌታም ግብሩ ሲወርድ ግብሩ ታቸት ላይ ከእብብ ላይ ያረፈ ወዛን ሲያጣው ሽቱ የሆነው ተጠራጥበት የተቀመጠ መንክረ ዷና ሽቱ ነበር። ሰጣት። ይህን ይዛ ሄዳ ከስምዖን ቤት ስትደርስ ስምዖን ሽቱ ተቀብታ የመጣች መሰሎት ገውለት አላስገባም አላት። ጌታ ወደ ትድንደ እንተዋ አለው - ግን እንዴት አምንስ እንዳደርግ ከስሕተቴ? አለው። ኃጥእን እትውድም ብሎ አለው። መድኃኒት የሚያስፈልገው ለበሽተኛ እንጂ ለጤነኛ ነውን? የሰው ልጅ መምጣቱ ኃጥአንን ወደንስሐ ሊጠራ ነው ከፍተህ አስገባት አለው። ገብታ ከወደኋላው እያለቀሰች ሽቱውን ቀባችው! እግሩንም በእንባዋ አርሳ በፀጉሯ አበሰች።

ይሁዳ (አስቆሮታዊ) ለምንት ኢሤጥዎ ለዝንቱ ዕፍረት በመጠነ ምዕት ዲናር የሀብዎ ለነዳያን ለነዳያን ይሰጡት ዘንድ በ300 ወቄት ይሸጥ አልነበረምን? ብሎ ተቆጣ። የገንዘብ ሹም ነበርና ከሙሉ አንድ የሚያገኘው ስለተረሳት እንጂ ለነዳያን አስቦ አልነበረም። ጌታም በሙሴ ብር የሸጠው የቀረበትን ለማግኘት ነው። ነዳያን ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ናቸው። ይህች ግን እስመ ተቀብዐ ለቀብርየ ለምትቀብርበት አስጠብቃዋለችና ተዋት አለው። እሷንም አትንሳት ይህ ወንጌል በሚሰበክበት ዓለም ሁሉ ይህቺ ሴት ያደረገችውን ለመታሰቢያዋ ይነገራል ብሎ አስተምሮአታል። ማቴ 26፥ 6-14

መጋቢት 22 - ሆሣዕና

ውሰበ በጽሐ ቤተፋጌ ወቢታንያ ኀበ ደብረ ዘይት ዘውእቱ ኢሊዮን ትእግን ከሰዎን ዘለምድ ቤት ጋብር ገብቶስት ያለ። የሐንስ ወበጽሐ ይላል በማጎኑ ደብረዘይት ሲደርስ ከደቀመዛሙርቱ ሁለቱን ሐሩ ሀገረ ዘቅድሜክሙ - ከፊታችሁ ወዳለ ሀገር ሂዱ ሰው ያልተቀመጠበት የአህያ ውርንጫ ታገኛላችሁ፤ ፈትታችሁ አምጡልኝ ለምን ትፈታላችሁ የሚል ቢኖር በሉ እግዚአ - ይፈቅዶ - ጌታው ይፈልገዋል በሉ ብሎ ላካቸው። ሄደው ጌታው እንደነገራቸው ወረዱ አህዪቱ ይዘው አብዛኛውንም ልብሳቸውን ጎዝጉዘውበት በዚያ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ። ደቀመዛሙርቱም ሰግደው ተከፍተው ፀሐይ ከእህያው ፊት ሆኖ ስትሰግድ ምድሪቱም ብርሃን ጽድልት ስትሆን መላእክትም ከሰማይ ወርደው አህያውን ከበው ሲያመሰግኑት እያዩ ልብሳቸውን ከመንገድ እያነጠፉ ብሩክ ዘይመጽእ በስመ እግዚአብሔር በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ የተመሰገነ ነው እያሉ አመሰገኑት።

እስራኤልም ሲደርስ ከገበያ ብርሃን የተነሣ ከተማዋ ብርሃት ሆነች። ሕዝቡ የሆነውን ሲያዩ ወጡ። ሕፃናት ወሐዲግ ስትሰግድለት መላእክት ከበው ሲያመሰግኑት እያዩ በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው የሰሌን ዝንጣፊ ይዘው ሆሣዕና በአርያም ሆሣዕና ለወልደ ዳዊት ቡሩክ ዘይመጽእ በስመ እግዚአብሔር እያሉ አመሰገኑት። ሆሣዕና ማለት በአርያም ያለ የሚያድን መድኃኒት ማለት ነው። ከምን አንዴት? ቢሉ ጌታ ወደ ገበያ ሲወርድ አመሰግኖን ሲደርስ ዕውራን አንዳቸ ካለችበት ቦታ ተነሥታ ደብረዘይት እንድትተክል አዘዛት፤ እሜሃ ሰረረት ወሰተ እየር ወተተከለት ሀየ ይላል በአየር በራ ደብረዘይት ተተክላለች ከዚያ ቆርጠው እምጥተዋል።

ሕፃናቱ ሦስት አፍል ናቸው። የነርሱ ምስጋና ከመላእክት ምስጋና ተዋህዶ ኢየሩሳሌም ተናወጸች። ሬድና ኢያሱስ ምን መጣበት ብለው ደንግጠው ቢጠይቁ ሕፃናቱን ሲያመሰግኑ አገኙ። እግዚአብሔር በሚመሰገንበት ምስጋና የተሰደ ልጅ እንዲታመሰግኑ ግን አስተማራችሁ? አሏቸው። እናንተ አወርች ዐሕይ ስትሰግድለት መላእክት ሲያመሰግኑት አታዩምን? ዳዊትስ በለኝ "እምአፈ ደቂቅ ወሕፃናት አስተዳሉከ ስብሐተ" መዝ 8፥3 ያለውን አላነበባችሁምን፤ አሏቸው። ግብተው የማያቋርጡ ቢሆን ደረቁ ጌታን አዘው-

ለሕፃናት ከመያርምሙ ዝም እንዲሉ ሕፃናቱን እዘዛቸው አሉት። እነሆ ሕፃናት ዝም ቢሉ ደንጊያዎች ያመሰግኑኛል መሰላችሁ? አላቸው። ወዲያው ደንጊያዎች ከደብረዘይት እየዘለሉ መጥተው ሆሣዕና በአርያም ለአምላክ ሆሣዕና በሩክ ለመድኃኒት ዘይመጽእ በስመ እግዚአብሔር ብለው አመሰገኑታል። ወተደመረ ዖሉ ሕፃናት ወዖሉ-እሰባን ምስለ ስብሐተ መላእክት እንዲሉ ዳድሳ። መቅደሱን ሦስት ጊዜ ዞሮ ወገፍትአ ማዕዱቲሆሙ ለመወልጣን ይላል ሻጮችን ለዋጮችን መገፉ መሰወጫቸውን እፈራርሶ አገርስንም በጅራፍ እየገረፈ አስወጣቸዋል። ማቴ 21፥ 10-13

• ይህ ሁሉ የሆነው "ተፈሥሒ ወለተ ጽዮን ወተሐሠዪ ወለተ ኢየሩሳሌም ነየ ይመጽእ ንጉሥኪ የዋህ ወትሑት ተጽዒኖ ዲበ እድግት" ተብሎ በነብዩ የተነገረ ትንቢት ይፈጸም ዘንድ ነው። ዘካ 9፥9

ከመጋቢት 23-28 - ሰሙነ ሕማማት

የዐቢይ ጾም ስምንተኛ ሳምንት ሰሙነ ሕማማት ይባላል። ጌታ የሰው ፍቅር አትብሮት ከሰማያት ወርዶ ከድንግል ተወልዶ ሰው ሰውቻውን ኑሮ በአይሁድ እጅ ተይዞ ተገርፎ ተሰቅሎ መሞቱን የምናስብበት ጊዜ ስለሆነ ነው። በእነዚህ በድስት ዕለታት ከደስታ ከጨዋታ ተለይቶ ሕማሙን ሞቱን እያሰቡ ሊያዝኑ ቀን ከሌሊት ከቤት ከርስቲያን ሳይለዩ ሕማሙን ሞቱን የሚናገሩ መጻሕፍትን ሊያነቡ፤ ሊሰሙ መዝሙረ ዳዊት ውዳሴ ማርያም ከሰሚድ ጋራ ሊያደርሱ ይገባል። የመላእክት የጸድቃን የሰማዕት መልክእ ግን አይነበብም። የቻለ ሁለት ሁለት ቀን ያለፈ እስከ ዕርበተ ፀሐይ ሊጾም ይገባዋል! ምግቡ ንብበት በጨው መጠጡ ጥሩ ውሃ ነው። በእነዚህ ዕለታት ሥጋ የሚቆርጥ ወይን ጠጅ የሚያንቀረቅር ቢኖር ዕድል ፈንታው ጽዋ ተርታው ጌታን በመስቀል በመግደል ደስ ከተሰኙት አይሁድ ጋራ ነው። ሕመም ድውይ ቢሆን ግን ከዘጠኝ ሰዓት በኋላ ተከቶ ሊጾም ይችላል። ይልቁንም ከሴት የደረሰ ሰውነቱን ያረከሰ ፅዱ ፍጹ ይደናበታል። እሊ ሉቀ ለዘይገብሩ ለሥጋ ኃጢአት በሰሙነ ሕማማት ትድስት
እንዲል ፍት-ነገ-አንቀጽ 24፥5

መጋቢት 23 - ዕረፍቱ ለዳንኤል ነቢይ

ዳንኤል ማለት ዳኛ እግዚአብሔር ማለት ነው። ትውልዱ ከነገደ ይሁዳ ነው። በምርኮ ፋርስ በባቢሎን ይኖር ነበር። ንጉሡ

ናቡከደነፆር አንድ ቀን በሌሊት ጠዋት ከእንቅልፉ ሲመላለስ የተመለከተውን ህልሙ ረሳው፤ እፁብ እኔ ይህን ጊዜም እንደ ዕቃ ላይ ነበር ሊሆን ሰው ፈልጎ እንደሚያስቀድሙ ሰዎች ጣቸ ከሲ ቀጥሎ የሚያንቀጠቅጥ እንደኔ ብርሃን ይሆን? ብሎ አሰበ። ሌሊቱ በሕልሙ ራሱ የወርቅ እንቶች ደረቱ የብር ወገቡ የነሐስ የሚጨጉን ጭኖቹ የነሐስ እግሮቹ የብረት የሸክላ ምስል ከፊት ቆሞ ሲያየው ከሩቅ ተፈነቅሎ እጅ ሳይነካው የወረደ ደንጊያ እድቅቶ ተመለሰ ተራራ ሲያከል አየ። ስለዚህ ሕልሙ ሐሰተኛ ህሊናውን ሕልም አስረኛ፤ ሕልሙንም የሚተርጉምለት ከባቢሎን ጠቢባን ለምልክት ሕልም እደቼ ሕልሙም ትርጓሜውም ጠፋኝ ንገሩኝ አላቸው። ንጉሥ ፍርድ አስበ ያም ጊዜ የሕልም ሰቃሮን በብሔ ቢተረጉምለት እንደማይገባን ይመላለስ ነበር። እንደምታስታውሳ ከአንደኛው ቀን ኑሮ እንደጠፋ ይደረሳል። ቢሆንም በየዓለሙ ዓለም ሲገሩት ኢገባ ኢይያስተውሉ እንደጸማቸው ኢገባሀሙ ለሕልሙ ግን ብቻ በማዘዝ ሁሉን ለማስወገድ ባለአቆሚዎች ሰሙ።

እንደ ዐዋ እየኖቹ ሲወስዳቸው ዳንኤል አገኘው። ወዴት ትወስዳቸዋለህ? አለው። ንጉሥ ሕልም አይቶ ጠፍቶት ንገሩኝ ቢላቸው አላገኙምና፤ በለዚህ ፍቅቸው ብሎኝ ሊገድላቸው እወስዳቸዋለሁ አለው። ቀን ስጠኝ እኔ እነግረዋለሁ ተጥቼው አለው። ሦስት ቀን ሰጠው። ከመለሰ ደቀቅም ላከላቸው። ለእርሱ በሦስተኛ ቀን ተገለጸለት። ሕልሙ ግን ዕለቱን ተገለጸለታል። በሰትሕትና ለንብቶ በሦስተኛው ቀን ንብቶ ሕልሙን ከትርጓሜው ነገረታል። በዚህ ምክንያት በምርኮ ላይ ሾሞታል።

ከዚህ በኋላ ናቡከደነፆር አልፎ ብልጣሶር! ብልጣሶር አልፎ ዳርዮስ ነገሡ። ዳንኤልን በሦስ ይወደው ነበር። ባለሟሎችም ቀናበት ነገር መፈለጉ ፈልጎ በለምክ አትሰገድም? አሉት። አይሰሙ አልበም ግን ምን ለእግዚአብሔር እሰገድ ስለዳቸው? አልሱ ዘማዊ ሞኝ ዳበላ ይህ ሆኖ ሚያ አያሉ ምግቡን በያደኑ አፍሐሉ ሚስጥራቸውንና አጋዎቻቸውን ይዘው ይመጣው ነበሩ - እያሉ እየሆኑ? አለው። አለው ሰሙ ቀንዶ ተያዛው ባሉ መናሥቦ የአሊድ ከመሸ ዘኩሉ ምግበን ወኙን ብርሃን አስቀምጦ በምትተው ንጉሥ እትዋ ፈየ። በሙሴ ሆን። ከበር ተውቀው ተመስሉ፦ ንጉሥ በለ ኃያል እምላክ ዳንኤልን አሳፈርኸውን አለ ... ዳንኤልም ከ እውር ከመጊዜ የሚገኝ ነው? አያለ ዐዋን እለዋሉ። የመናፍቅ ጣዖ ቀን! የምስጋናቸውንና የልጆቻቸውን አበሮ እና። አስከ ለሚገባውን ኮሮዋ ብሉ አስተ ከብደቸው እስመትቷቸዋል።

ከዚህ ሌላ መንፈስ ርኩስ ያደረበት ዐቢይ ዘንዶ ያመልኩ ነበር። ያ እደበላም አይጠጣም አልህ፤ ስለዚህ ለሚበላው ለሚጠጣው አትሰግድምን አለው። ይህንንም ከፈቀድህ ወር ጋሻ ሳልይዝ እገድለዋለሁ አለው። እንዲሰለመዱት ብሎ እርዳ ሥጋውን እወፋርዶ ስቡን ጸጉሩን ጨርቅ ገለ ጨምር አጠለለት። እያሰሳ መጥቶ እፉን ከፈተ! ስቡን በጋለ እሱሉ ወትአሉ ከእፋ ማለለት! ተሰንጥቆ ሞቷል። ተረፈ ምዕ 1. የይሁን ዘሥሉ አሌ. ምዕራፍ 67 ባቢሎናውያን ጸልተው ተመቅኝተው ንጉሥ ወዳጅህን ወሰትህን እንድናወት ለሦስት ቀን አጥቼ ይጥርልን አሉት። ነገሩዋቸው። በሦስተኛው ቀን በሦስት ሰዓት ዳንኤል መስኮቱን ከፍቶ ሲጸልይ እጥጅ እናርሰ ሲጸልይ አገኙት ብለው ለንጉሡ ነገሩት። የተፈረደበትን ሰው የሚመገብ እናብበት ነበሩ። ወሰደው ጣሉት። በግንቡ ቢሄዱ ላይበሉት አገኙ። ዓይርብሆ ይሆናል ብለው ምግባቸውን አስቀሩባቸው። ነገር ግን ቅዱስ ሚካኤል እፉቸውን ሰለዘጋ አልተናከሉትም።

ነቢዩ ዕንባቆም በኢየሩሳሌም ለአጫጆች ምሳ ይዞ ሲሄድ መልአክ በድ ጸጉሩ ያዘ ምሳውን ለዳንኤል ውሰድለት ግን ባቢሎን ለዳንኤል ወሰድለት አለው። ዳንኤል የት እለ? ባቢሎንንም አላውቃትም አለው። ወዲያው ወዲያውኑ ከዚያ ዳንኤል ወደ ሰጉ ይዞ አደረሰው፤ ዳንኤል ተመግቦ ወጥቷል።

ንጉሡ ደበደበ ነበርና ፈጣሪው እድኖት ይሆን ብሎ ቢሄድ እናብስት እንደደረሱት ከእግሩ ወድቀው እሱ ቀና ብለው እይ። ወብሶ እምላክ ለዳንኤል-የዳንኤል እምላክ ገናና ነው ብሎ ና ወጣ እለው። ባለሟሎቹን ቢያስገባቸው ከአያር ሳይደርሱ በለብላቢቸዋል። ንጉሡም እምና እሕዛብ እንዲያምኑ እዋጅ ነገረ። ዳን 7፥ 1-28

ከዚህ በኋላ ሚጠት እስራኤልን ሲፃ ቀናና ገዛ። ከሚጠትም የበለጠ የሥጋዌ ነገር ተገልጾለት "እስከ ክርስቶስ ንጉሥ ትትሐነጽ መቅደስ" ብሎ ትንቢት ተናገረለ። በዚህም ዕለት ዕረፍቱ ይነበባል።

• መዋዕለ ትንቢቱ ከ 556-538 ዓ.ዓ ገደማ ነው።
የመ.ቅ. መዝ. - ገጽ 208

መጋቢት 25 - ምክረ አይሁድ

በዚህ ዕለት አይሁድ ጌታን አስቀድሞ ነገር አድንተው ፈሪን የእግዚአብሔር ልጅ ሲያደርግ! ሰንበትን ሲሽር! መሬትና እሳትን ሲያቃልል ለንጉሥ ግብር አትስጡ ሲል ለምትነፃ ብለን እስመክረን ለቅለን እንገደለው ብለው ምክር አደንተዋል። (ዕለቱ ረቡዕ)

መጋቢት 26 - ሕጽበተ እግር

እስራኤል ከግብጽ የወጡበትን በግዑ ፍሥሕ! ፋሲካ! በግዑ መሰዋት እያሉ በየዓመቱ እርሻ የሌለው ቂጣ ጋግረው በግን እርደው በመብላት ያከብሩት ነበር። ዘጸ 11፥ 32 ፥ 51

ጌታም በዚህ ዕለት ከደቀመዛሙርቱ ጋር አከበረታል። ደቀመዛሙርቱ በእይቱ ትሬቅድ ናስተዳሉ ለከ ፍሥሐ ትብላዕ-ፋሲካውን ትበላ ዘንድ ወዴት ብናዘጋጅልህ ትወዳለህ? አሉት። ከፊታችሁ ወደአ ሀገር ሂዱ የውሃ ማድጋ የተሸከመ ሰው ታገኛላችሁ ከገባበት ተከትላችሁ ይቤልዎ ለት እይቶኑ ጽርሐ ገብ አበል ፍሥሐ ምስለ እርዳእየ በሉት ያሳያችሁ ብሉ ሊቀርበን ተሐንበገና ያቀብቦ ላኳቸው።

ቢሄዱ የውሃ ማድጋ ተሸክሞ ሲሄድ አገኙት። ሰምን ሽምጽ ነው። ተከትለው መሥዋዕ ከደቀምሁምርቱ ጋር ፋሲካውን የምትበላበት እዳራሽ ወዴት ነው? ብሉሀል እሉ! ይለ እሰው ለምስቱም ነገሩት።

በበጠኝ ሰዓት ጌታ ደቀመዛሙርቱን አስከትሉ ሄደ። ከደርሰ ላይ ማምጃ እንተርባት ያን እያረገጠ ገበታል። ይሁዳ ወደ ጓዳ ቀርቶ ነበር። ስለምን ቢሉ በደብረዘይት ጌታ እሐዱ እምኔክሙ ያገብአኒ-ከናንተ አንዱ እሳልፍ ይሰጠኛል። አምነዖ ሰበ ኢተወልደ ለውእቱ ብእሲ። በዚያም ሰው ዓይወልደ ይሻለው ነበር ብሎት ጌታ ደቀመዛሙርቱ አዝነው መጉ ዘይከውድ አምኔነ ንገረን ዝዴ-የሚከዳ ማነው ገላጭ ንገረን ቢሉት ከዜሬድሮስ ይገደል እንዱን እነን አሳልፎ የሚሰጠኝ ማነው? ተናገር ብሉት በይሁዳ ፊት ምስት ጊዜ ዞር ገከካ ይም የምታሪለ ይሁዳ ወቀልዑ ብሎ መሰጠበት ይህ መሠርይ ብሎ ብሎ ደንገሆ ያናገርናኝ? በማኝ ያማኝ ብሎ ወደ ቤተመቅደስ ሄዶ ከአይሁድ ጋር ይማከር ነበርና ሰለዚህ ነው። መጥቶ ሊገባ ሲል እላልሰኮንደርስ የተባለው ወሰቁ እርሱ ከደቀመዛሙርት ጋር ሊገባ ብቸው ማስጠንት ይህ ነው! እንተ ግን በደም የተመላ ጽዋ ይዘህ! ከእንተተህ እባብ ተወዋጥቶ ሊበዛህ ምላሱን ያወጣበታል! የያዝከው ደም ቢጐተበት ጌታ ስለሚያታልፋ ዐዋኝ ብሉ ምንዛሬን ከነገ በኋላ እስገብተታል።

ከዚህ በኋላ ከግብጽ ተነሥቶ ወበን በህርር ታጥቆ የደቀመዛሙርቱን እግር ሊያጥብ ወኃ በሕልበበት ይዞ ቀረበ! ርሰን ሐዋርያት ነዋና ከበርክ ደጀምራሉ። እግርህን እኔም ለመታብ እላውሉ እኔም እንተ እግዚአ ተሐጽበ እግርየ - አቤቱ አንተ እግሬን ታጥበኛለህ? አለው። የማደርገውን

ዳኛ እንጂ እሁን አታውቀውም አለው። መቼም ቢሆን እግሬን አታጥበኝም አለ። እመ ኢሐፀብኩከ እገሪከ አልብከ ክፍል ምስሌየ - ካላጠብኩህ ከእኔ ጋር እድል ፈንታ ጽዋ ተርታ የለህም አለው። እንዲህማ ከሆነ እጄንም እግሬንም ጨምረህ እጠበኝ አለው። ፈጽሞ የታጠበ ከእግሩ ሌላ እያሻውም አለ። እንተሙሰ ንጹሓን እንተሙ - እናንተ ንጹሐን ናችሁ! ነገር ግን ሁላችሁም አይደላችሁም አለ።
እግር ሲጠርብ ወሰብ ኦኑ እንዝ ሊትትሎ ወእግዚእሎሙ ክሙ መምህራችሁና ጌታችሁ ስሆን እግራችሁን አጥቤሳቸሁ እንደሁ እናንተም የወንድሞቻችሁን እግር ታጥቡ ዘንድ ይገባል። ነገር ግን ከናንተ አንዱ ሰዎች አላፎ ይሰጠኛል አለ። ማን ይሆን? እኔ እሆንን? አሉ ንብበት ቀርጹ ከዐው ወቅት የምስጢረ እሱ ነው አላቸው። ወዲያውም ጉብበቱን ቁርሶ ከአሥራ ሦስት ፈትቶ ንሥኡ ብልዑ ዝ ውእቱ ሥጋየ - ነገ በመስቀል የሚሆን ሥጋዬ ይህ ነው እንካችሁ ብሉ፣ ብሉ ተቀበሉ አቀብላቸው። ጽዋውንም እከብር ለውመ ዝ ውእቱ ደምየ ዘሐዲስ ሥርዓት ዘይትከዐው በእንተ ብዙኃን ለኅድገተ-ኃጢአት - ለብዙዎች የሚፈስ የሐዲስ ሥርዓት ደሜ ይህ ነው። ጠጡ ብሉ ሰጣቸው። ሥጋውን ደሙን በመብሉ በመጠጣ ማድረግ መብላ መጠጥ የሚያሰናከራ ሰብእ እግዚአብሔርን የሚያፋቅር የሚያዋሕድ መሆኑን ለማጠየቅ ነው። ከዚያውም ዘንድ በሰንዱ በወይን ያደረገው ትንቢቱ ምሳሌው ይፈጸም ዘንድ ነው።

ትንቢት - አምፍሬ ሥርናይ ወወይን ወቅብዕ በዝኃ መዝ 4፥7
ቀዳሚ አይሁድ ለሰብአ እከለ ወማይ ወይን ወሥርናይ ሲራ 29፥28
ለዘእይሁድ ወይን ምንት ወሕቱ ሕይወቱ ሲራ 34፥
26 ተብሎ ተነገሯል።
ምሳሌ- እምሳለ አብርሃም ለመልከ ጼዴቅ እንጀራና ወይን አቀርቦ ነበር ዘፍ 14
የሊቃውንቱ አንድ ባለመኃኒት ለማስደረግ እንድም እርሷ ሰውን ነው። እርሱ ሳይተበለ ደቀመዛሙርቱን ብቻ አቀብሏቸው ቢሆን ኖሮ ፍሬ ከሆነ ምሥጢሩን አቀብለው እርሱ ሳይቀበሉ ይፋዩ ነበርና ተቀብለናቸው እቀብሏቸው ሲለ ግን አማሳሎ ይላል ተቀብሉ አቀብሏቸዋል።

ምን ልሳኖ ርትዓን ሊሳናለሁ ቢሆን
ብሉ ብሉ ሚስቲ ማነው ሥጋውን፤
ካንተ በቀር ጌታ ያለም መድኅን
ደምሁን አምስሎ ወጡ ማትሆ
እለከበረም እንዲ ፍቅር እንደቆይ
ታፋ እሞን ዓሉ ምንዳር ይሆን ያስተ
በእንድሎታችን ልጆችሁ ነን እያልን

ነገር ግን እሊሉ በልቶን ርቀን
ከበር ለመታይ መቀበል ለያኔን
ከቀተሞች ናቸው እላለችም ይሆን፤
እሆንም እባክህ ቸር እምላኪ
ዋሌ ነን በጊሉ ዋይ እንዲሆሰብ
እሆን ለመቀበል ሥጋ ደምህን
እለያለሁና ያለሁ መላን

መጋቢት 27 - ስቅለት

ሥጋውን በጎብበት ደሙን በወይን አስታኩቶ ተቀብሉ ሲያቀብላቸው እከርብና (የሰምዖን ዘለምጽ ሚስት) ደር እስናድታ አቀረበችለት። የተናገረው ሲፈጸም ገድ ነውና ጎብስቱን ቆርሶ ከወጡ ጠቀሶ ለይሁዳ ሰጠው። ሰይጣን ከጎብስቱ ጋር ተዋህዶ ልቡ በትኖት ገደደ። ሥጋው ደሙ ሰይጣን ያርቃል እንጂ አያስገባም ነበር። ዳሩ ግን ዕዳ ፍዳ የሚቀበልበት ነውና ሳይበቃ የሚቀበሉ ዕዳ እንደሚሆንባቸው ለማጠየቅ ነው።

በጊ ወይአዚኒ ዘበልዐ እምዝንቱ ኅብስት ወሰትየ እምዝንቱ ጽዋዕ እንዘ ኢይደልዎ ይደዮ መቅሠፍተ በሥጋ ወደሙ 1 ቆር 11፥27

ሂድ ያሰብከውን ፈጽም አለው። ወጥቶ ሄደ። ይሁዳ እንደወጣ ጌታ ዶርውን በያሉ ተናግር በእጁ ዓለ ሕያው ከአደረገው በኋላ ይሁዳን ተከትለህ የሚያደርገውን እይተህ የሚናገረውን ሰምተህ ለደቀመዛሙርቱ ንገራቸው አለው። እየበረረ ወጥቶ ተከተለው። ከቤቱ ንብቶ ከሚስቱ ተኝቶ በጥጋ አሳልፎ ሊሰጠው መከረ። ሄዶም አይሁድን አሳልፎ ብሰጣችሁ ምን ትሰጡኛላችሁ? አላቸው። ሰሞ ሊያሳየው ተስማምተው ሠላሳ ብር ሰጡት። የተነገረበት ትንቢት ተፈጸመ። ምን ተብሎ ተነገሯል ቢሉ ነቢዩ ዕንባቆም ለማስተማር ሲሄድ የይሁዳ አባት ከባልንጀሮቹ ጋር ከደንጊያ ላይ ተቀምጦ ባልንጀሮቹ ሲነሱበት እርሱ ተቀምጦ አለለው። ሲያስተምር ወሉ ሲመለስ ከዚያው ተቀምጦ አገኘው። እንዳይነዳ ኮርቶ እንዳይቀመጥ ፈርቶ ተቸፍፍና አላለው። "ዕብን ዲበ ዕብን ነበር ደንጊያ በደንጊያ ላይ ተቀምጧል! ከዚህም ሰው የሚወለደው ዘእብው እለዱ ዘሊሙ ብእሲቱ ዋጠ - እባቱን የሚሰጥ እናቱን የሚያገባ መምህሩን የሚሸጥ ይወለዳል ብሎ ትንቢት ተናገረበታል። ከቤቱ ገብቶ ለሚስቱ በግድ ካልተነሳሁኝ ብሎ እንዲህ አለኝ ብሎ ነገራት እሷም ደግ ያደረግህ መስለሁ? ታላቅ ሰው ሲመጣ ተቀምጦ ማየት ይገባልን? ብላ
ገጸቻው። ከዚህ በኋላ መፀነሱን እንተው ብለው መክረው ሲኖሩ አንድ ቀን ፈቃደ ሥጋ አሸንፎት ተገናኙ። ይሁዳ ተጸነሰ። በተወለደ ጊዜ በሳጥን አድርገው ከባሕር ጣሉት። ስምዖን አስቆሮታዊ አገኘ ለአደገው።

ካደን በኋላ ያለበት ሀገር ሰዎች በአባት እናቱ ሀገር ላይ ሲዘምቱ እርሱም አብሮ ዘምቶ ነበርና አባቱን ከሰልፍ አገኘ ገደሉ ሰለበው! እናቱንም ከሰረቀ ግርካት በጉብርም አወቃት። አባቱን ይገድላል እናቱን ያገባል ያለው ተፈጸመ። አንድ ቀን ሲጨዋወቱ የዚህ ሀገር ሰዎች ዘመድ ዘመድ አይሰሀምባ? አለችው። ከባሕር ተገኘ ይሉኛል አላት። አንተ ጉደኛው ነህን? ያ ገድለህ የሰለብከው አባትህ ነው እኔም እናትህ ነኝ አለችው።

ከዚህ በኋላ ኃጢአታችንን ያስተሰርያልናል ብለው ከሀቃ ዘንድ ሄዱ። ኃጢአታቸውን ይቅር ብሎ እርሱን ከ12ቱ ሐዋርያት እርሷን ከ36ቱ ቅዱሳት አንስት ቆጠራቸው። ዳሩ ግን ትንቢት እንደተነገረበት በፍቅረ ነዋይ ተስቦ በ30 ብር ሸጠው! ዘአግዚአ-ጌው ያለው ተፈጸመ።

ያም ደግ ተመልሶ መጥቶ ያስቅስ ጀመር። ያየኸውን የሰማኸውን ንገረን አለው። አባይ ሲሰማ ከአይሁድ መቶ ብር ተቀብሏል! እነሱም ሾተል ገመድ ይዘው እየመጡ ነው ብሎ ያየውን የሰማውን ሁሉ ነገራቸው። በከንፈሁ በረሀ ሰማየ ሰማያት ገብተህ እልፍ ዘመን ኑር አለው! በር በር ገብቷል።

ከዚህ በኋላ ወደ ደብረዘይት ወሰዳቸው። በዚህች ሌሊት ሁላችሁ ትክዱኛላችሁ "እቀትሎ ለኖላዊ ወይዘረው አባግዒሁ (ዘካ 13፡7) ተብሎ ተነግሯልና፤ ከተነሣሁ በኋላ ወደ ገሊላ እቀድማችኋለሁ አላቸው። ጴጥሮስ ሁሉም ቢክዱህ እኔ አልክድህም አለ። እማን እብለከ ከመ በዛቲ ሌሊት ትክሕደኒ ዘእንበለ ይንቁ ዶርሆ ሳይጮህ ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ ብሎታል።

ወደጌቴሴማኒ(?) ገብቶ ጴጥሮስን፣ ያዕቆብንና ዮሐንስን ጥቂት እልፍ አድርጎ ለምንቱን ራቅ አድርጎ ይጸልይ ጀመር። ሲጸልይም እ አበዬ እመሰ ይትከሀል ይኅልፍ እምኔየ ዝንቱ ጽዋዕ - ቢቻልስ ይህ ጽዋ ከእኔ ይለፍ ነገር ግን ፈቃደ ዚአከ ይኩን ወአኮ ፈቃደ ዚአየ ያንተ ፈቃድ ይሁን እንጂ የእኔ አይሁን አለ። ይካም ሥጋን እንደተዋሐደ ለማጠየቅ ነው። ወደደቀመዛሙርቱ ቢመለስ ተኝተው አገኛቸው። አንድ ሰዓት እንኳ መትጋት ተሳናችሁን? ትጉሁ ወጸልዩ ከመ ኢትባኡ ውስተ መንሱት - ወደ ፈተና እንዳትገቡ ተግታችሁ ጸልዩ አላቸው። ሁለተኛም ቢመለስ ተኝተው አገኛቸው።

በሦስተኛው ነው እንኳ ወእእርፉ እንግዲህ ዕረፉ አላቸው። ተንሥኡ ንሑር ናሁ በጽሐ ዘያገብአኒ የሚያሲዘኝ ይሁዳ መጥቷል ተነሡ እንሂድ አላቸው። ይህንንም ሲናገር ይሁዳ ሾተልና ገመድ ከያዙ አራት ቤት ጭፍራ ጋር ደረሰ። ማን ተገሥጡ ማንን ትፈልጋላችሁ? አላቸው። ኢየሱስ ናዝራዊ አሉት እኔ ወእቱ እኔ ነኝ አላቸው ገብሩ ድንጋፄ ወወድቁ ዲበ ምድር ይላል - የኋሊት ወደቁ። ሁለተኛም እንዲሁ ሆነ በሦስተኛ የምትፈልጉት እኔን ከሆነ እነዚህን ተውአቸው አላቸው። ይሁዳ ቀርቦ በውስ ረቢ - መምህር ሆይ ሰላም ብሎ ሳመው። እ ይሁዳ በስዒምን ታገብእ ለወልደ እጓለ እመሕያው የሰውን ልጅ በመሳም አሳልፈህ ትሰጠዋለህን? አለው። ሲይዙት ተረባረቡ ወሰ መልሐ ሰይፈ ለሰምዖን ጴጥሮስ ይላል ጴጥሮስ ሰይፉን መዘዘ የማልኮስን ቀኝ ጆሮ ቆረጠው ቀይ እለ! ጌታ አግብእ ለመጥባሕትከ ውስተ ቤታ አለው። ያንንም በእጁ ዳሰ ፈወሰው።

ከዚህ በኋላ እስረው እየደፉ እያዳፉ ወደ ሐና ወሰዱት። ሰውየው የተባለው ሰውሉ በዚህ ጊዜ ጌታን ከሚያስወቃቸት አንዱ ነበር። ልቡን በጣም ረገመው። እንደበግ ከእጅህ ገብቼ ሳለ ለምን ይህን ያህል ከፉ ታደርግብኛለህ? ኋላ ግን ከከፋትህ ትወጋለህ! የበተንከው መንጋንም ትሰበስባለህ አለው።

ሐና ምን እያለህ ታስተምራለህ? አለው። በውኑ በሰወር የተናገርሁት አለን? የሰሙኝን ጠይቅ አለው። አንዱ ጭፍራ "ከመዝኑ ትትዋሠእ ለሊቀ ካህናት" ብሎ ፊቱን ፀፋው። ክፉ ከተናገርሁ መስክርብኝ በጎ ስለተናገርሁ ግን ለምን ትመታኛለህ? አለው። ከዚህ በኋላ ወደ ቀያፋ ወሰዱት።

ጴጥሮስ ከሩቅ እየተከተለ መጥቶ ከሊቀካህናቱ ግቢ ተቀምጦ ነበር። ዓፀፋ ወለት በለሊት "አ አረጋዊ ብእሲ አንተሁ እምገሊላዊ ብእሲ ከደቀመዛሙርቱ አንዱ አይደለህምን? አለችው። ደንግጦ ኢየአምር ለውእቱ ብእሲ - አላውቀውም አለ። ሁለተኛ የማልኮስ ወንድም ኮልቤ - "ከርሱ ጋር በአትክልቱ ቦታ አላየሁህምን?"! እለው አላየኸኝም ብሎ ካደ። ሦስተኛ አንዲቷ መጥታ "አንተኑ ረድኡ ለገሊላዊ ኢየሱስ ቃልከ የዐውቀከ - የኢየሱስ ደቀመዝሙር አሙሆነ ንግግርህ ያስታውቃል" አለችው፤ አላውቀውም እያለ

ከዚህ በኋላ ከሊቀጳስ ተቀብለው ከገንዳ አስረው አራት ከእርባ አትርፈሀ እትገረፍ ትላለችና ሠላሳ ዘመን ገርፈው ዘጋሁኝ እያሉ እየተቀባበሉ አራቱ ጭፍሮች 6666 ጊዜ ገርፈውታል! ሥጋው አልቆ አጥንቱ እስኪቆጠር።

የሾህ አክሊል ጎንጉነው ከራሱ ደፍተው በመቃ ቢመቱት ራሱ በሰባት ጊዜ ተበሳሷል። መስቀሉንም ሦስቱን እንጨቶች ፀ እመልዕ ፀ ወይራ! ፀ ዘይትን እና እራቱ ፀፀ በለስን አንድ ወገን አድርገው ቁመቱ ሰባት ክንድ ከስንዝር! ወርዱ ሦስት ክንድ ከስንዝር አድርገው ሠሩ። ፀ በሰለ ለሰሎሞን ንጉር እሰግለት ብሉት ንለገሶን ከገንብ ውሥተ ዘንቀበት ሳለ ንሰር ከገነት እምጥቶ ገገዐ ላይ ተሉት ገገዐን ሰበር ገለገሶን ከወሰደ በኋላ በአትክልት መካከል ተተክሉ ቆይቶ በተመቅደስ ሲሰራ እንደሰርያ የሚገዛለት 700 አጋንንት ሊቆርጡት ሲሉ እንደእሳት ፈጅቷቸው እርሱም ለመቃብም! ለመድረክም እሳቱን ብሎት ሳይቆርጡ ትተት ከደጃፍ ወድቆ የነበረ የሀገራችን ንግሥት ማክዳ ጥበቡን ልታይ ወደርሱ በሄደች ጊዜ ዘገይ ሰታስበርል ደሙ ቢነተብበት እንደ ፍየል ሰኮና ሆኖ የነበረውን ቀርድ የጣሰላት በዚህም ምክንያት ሰሎሞንና እርሷ በአንድ በአንድ ብር ለብመው ከቤተ መቅደስ ያስቀመጡት ከርሱም በኋላ የተገሙ 28 ነገሥታት ተአምር እያደረገላቸው በአንድ በአንድ ብር እየለበጡት የቆየ ነው። ሠላሳውን ብር ለይሁዳ ሰጥተው ግንዱን ለመስቀል አድርገውታል።

በስድስት ሰዓት ቀይ ግምጃ አልብሰው ገሬ ቀኝ ፊት ኋላ ሆነው እየገፉ እያዳፉ ወስደው በማዕከለ ምድር በቀራንዮ ሰቀሉት። በቀራንዮ መስቀሉም ትንቢቱ ምሳሌው ይፈጸም ዘንድ ነው። ትንቢት "ወገብረ መድኃኒተ በማዕከለ ምድር" ተብሎ ተነግሯል። መዝ 73፡12

ምሳሌም፡- እስራኤል ወና ከደመና እያወረደ ውኃ ከዓለት እያፈለቀ ይህንን እየመገበ ደጋ ደጋውን ሲወስዳቸው "ሐመይ ለእግዚአብሔር ወደ ቤት ደብረ እግዚአብሔር ሠለ-ግዐደ በኀቤም ደዘበዐ ከኩሉ ወያው ገሰ ገዕ" መዝ 77፡19 እንዲሁ-ቀላቀ የሳፍ ከሚባል በረሀ አወርዶ መናውንም ውኃውንም ካቀርበው አብሰው ሰማቸው። ዳሩ ግን እባብ ነፍሳቸውን እየቀደደ ይፈጃቸው ጀመር። ሙሴ ወደጌታ ሲያመለክት እርዌ ብርት መርቶ ቀልላ

ላይ ሰቅለው አይተው ይሳቅ አለው። እንግዲህ ሆኗል። ተራራው የቀራንዮ ተራራው የመስቀል ብርት የጌታ እባብ የሚያሳስብ ቅሉ የኃጢአት በረሀ የሲኦል! እይተው እምነው የዓይ የሐዋርያት የምእመናን! አይተው ያልዋ የአይሁድ የመናፍቃን ምሳሌ።

ሲሰቅሉትም መንፀፊያውን ከቀናን! ወፈሩንና መዶሻውን ለአራት ተከፋፍለውታል። ቀሚሱን ግን ሰፊው በገል የሸፈለት ስፌት የሌለው ሥሪቱ ሲያድግ የሚያድግ ገበሬ ተአምር ነውና ኢንከተተ ወኢንግምድ አላ ንትፋሰስ ዓሰሉ ለዘረከበ ይርከቦ ብለው ዕጣ ተጣጣሉበታል።

ሰቀሉ ምስሌሁ ከሌዊ ፈያት አሐደ እምየሚነ ወአሐደ እምፀጋም ይላል ተወሰን በቀኝ ፋክርስን በግራው ሰቀሉ። "ተኈለቈ ምስለ ጊጉያን" /ኢሳ 53፡12/ ተብሎ ትንቢት ተነግሯልና። ጲላጦስም ከራሱ በላይ በቀረው ሰንዝር ያህል "ኢየሱስ ናዝራዊ ንጉሠ አይሁድ" ብሎ በዕብራይስጥ በጽርዕ በሮማይስጥ ጻፈበት።

በተሰቀለም ጊዜ ሦስት በሰማይ (መሬር) አራት በምድር ሰባት ተአምራት ታይተዋል። በላይ የፈጣሪያችንን ዕርቃን እናያለም ብለው ፀሐይ ጨልሟል! ጨረቃ ደም ሆኗል! ከዋክብትም ረግፈዋል። በምድርም አለቶች ተሰነጣጥቀዋል! መቃብራት ተከፍተዋል! ከ500-1000 የሚሆኑ ሙታን ተነሥተዋል! የቤተመቅደስ መጋረጃ ከሁለት ተከፍሏል። መከራው እጅግ ጽኑ ነው! ሕማማቱንም ሊቃውንት በቁጥር 13 ብለው አስቀምጠዋቸዋል።

እነርሱም
1. ተአሥሮ ድኅሪት
2. ተስሕቦ በሐብል
3. ወዲቅ ውስተ ምድር
4. ተከይዶ በእግረ አይሁድ
5. ተገፍዖ ማዕከለ ዓምድ
6. ተጸፍዖ መልታሕት
7. ተወቅሮ ምራቀ ርኩሳን
8. ተከርዮ ርእስ
9. እክሊለ ሦክ
10. ፀዊረ መስቀል
11. ተቀንዎ በቅንዋት
12. ተሰቅሎ በዕፅ እና
13. ሰቲየ ሐሞት ናቸው።

እኒህን ትኩሳቱን እብርኤል ከመከራው አስታግሱኝ ሳይል በትሕትና በትዕግሥት ተቀብሏል። "እ ትዕግሥት ዘኢከሠተ አፉሁ በሕማሙ በቅድመ እለ ደረግዚዎ" እንዲል ቅዳ. ግር ቁ 126 የሆነ አንዲት ቃል በንኳ አልተናገረም ማለት አይደለምን? ቢሉ

ይምላል ይገዝት ጀመር። ወዲያው ዶሮ ጮኸ "ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ" ያለውን አስታውሶ አምርሮ አለቀሰ።

ጌታም ሌሊቱን ሲደበድቡት አድረው መከራ ሲያጸኑበት ሌሊት ተመሸላቸው። ከሐዋሪ ሰሎሞን ሲደርስ የይሁዳን ዘመድ ልጇን ታቅፋ እንጋኘችት "እይሁድ እኔን ሊፈልጉ መጥተው ቢጠይቁሽ ከርሱ ምን አላችሁ? በያቸው" ብሏት ከዓምዱ ስር አረፍ አለ። አይሁድ ተከታትለው መጥተው "አላየሽውምን? አሏት። በእጇ አመለከተቻቸው። ይዘው እያዳፉ አመጡት። "እንቺ ሴት አትንገሪ ብዬሽ ጥቂት ራሴን እስካሳርፍ መታገሥ አቃተሽ? በዓለም ምጽአቴ እሥነስቼ እስከፈርድብሽ ደንጊያ ሁኚ" አላት፤ ደንጊያ ሆና ቀርታለች።

በነግህ አስፈርደው ሊሰቅሉት ወደ ጲላጦስ ወሰዱት። ይሁዳ እሱ በተአምራት ይድናል እኔም ብሬን እንደያዝኩ እቀራለሁ ብሎ ሸጦት ነበርና ይህን ሲያይ አራት "ኢትትቀጥል ብእሲ ጻድቀ" ያለችውን ተባለሉ ንገሀ ያም አሳልፌ በመስጠቴ መልካም አላደረገሁም፤ ብራችሁን እንኩና ፍቱት አላቸው። እኛማ የፈለግኸውን በተገኘል የፈለግነውን አግኝተናል አሉት። ከእግራቸው በትኖት ሂዶ ከዛፍ ተሰቀለ። ወደኋላ ሸሸችው። ከሌላ ዛፍ ሄደ። ነጎድ እስር ሲታነቅ ሊገጠለጠል በቃል ሰብአዊ" ግረኝ ብትለው ይምርህ የለምን? ነሐ ከመእንገ ጴጥሮስ - እንደ ጴጥሮስ ንስሓ ገባ" አለችው። እርሷን ትቶ ከሌላ ዛፍ ሄዶ ተሰቀለ! ገመዱ ተበጥሶ ከመሬት ወደቀ። ሰውነቱ ቆስሎ በአርባ ቀኑ ሞቷል።

አይሁድም ጌታን ይዘው ከጲላጦስ ሲገቡ ከውጪ ምኩናን በድበት አርግው (መረዋች) ቆመው ነበር። መስሎ ብሎ ሲያያቸው እንደግንድ ተረብርበው ሰገዱለት። ከኢየሱስ ወዳጆች ተመሳጥረው ነው። በእሥር በእሥር ኃያላን ይያዙ እሱ ተያዙ። ሲያያቸው አሁንም እንደሱን አምኘሬው ሰገዱለት። በአሰራ አምስት በአሰራ አምስት አሰያኳቸው። ዘጠናው ስድስቱን ግቀም ተስናቸው ተትተው ወድቀዋል።

ጲላጦስ ፍርሀት ፍርሀት አለው። "ቤው የአይሁድ ንጉሥ ነህን?" አለው። "አንተ ትቤ - አንተ አልህ" አለ። አይሁድ "ራሱን የእግዚአብሔር ልጅ ያደረገ! መሲሕና አራትን ያቀለለ! ሰንበትን የሻረ! ለቄሣር አትገብሩ ያለ ሀሳዊ እንጂ ንጉሥ አይደለም" አሉ።

"ይህን ያህል ሲከሱህ አትሰማምን? "አለው፤ ዝም አለ። "ብዩ ሥልጣን እንተልክ ወሊሕየክ ልገድልህ ወይም ላድንህ ሥልጣን እንዳለኝ አታውቅምን? አለው። "እምእይቲ ለከ ሥልጣን ትትከለኒ ወታሕይወኒ እምእጊትዐ ለከ እምሰማይ ከሰማይ ካልተሰጠህ በቀር ልትገድለኝ ወይም ልታድነኝ ሥልጣን ከወዴት አለህ?"አለው አይሁድን እንጂ አንድ በንኳ በደል አላገኘሁበትም። ገርፌ ልፍታው አላቸው። ከገሊላ ጀምሮ እስከዚህ ድረስ መጣ አይሁድን ሲያውክ የነበረ አይሰቀልም ትላለህን? አሉት። ገሊላዊ ከሆነማ ገሊላ ግዛት የሄሮድስ ነውና ወደርሱ ወሰዱት አለ።

ሄሮድስም ዜናውን እየሰማ ሊያየው ይመኝ ነበርና ደስ አለው። ዳሩ ግን ቢያናግረው የማይናገር ሆነ። እስተእኪዙ ይላል አለከፍቶ "አይቻልም እንጂ ቢቻልስ ሁለት ሞት ይገባዋል" ብሎ ወደ ጲላጦስ መለሰው። ከዚያ በፊት ጲላጦስና ሄሮድስ ተጣልተው ይኖሩ ነበር፤ አሁን ግን በጌታ ምክንያት ተስማምተዋል።


ጲላጦስ ጌታን አዝኖ ሲያየው ሄሮድስ ብዙ እንዳበረታው አውቆ አዘ። "ይህን ሰው ወደኔ ሦስት ጊዜ አመጣችሁት፤ እኔ ግን መርምሬ በንኳ ለሞት ለሚያበቃ ጥፋት አላገኘሁበትም! አሁን ግን ለበዓል አንድ እስረኛ ልፈታላችሁ ልማድ ነውና ገርፌ ልፈታው አላቸው። "አክ ዘንተ አላ በርባንሃ - በርባንን እንጂ ይህን አይደለም" አሉ። በዚህ ጊዜ ከሚስቱ ከአብሮቅላ "ድላ የሰውን ልጅ መከራና ፍርድ አንደበታቸውን ከፍቀዋቸዋልና ከፉ እንኳ እንደተናገረው እወቅ "የሚል መልእክት ደረሰው። አይሁድ በሥራቱ ነው ሲሉ ጌታ ከርሳቱን ተቀብሎ የተጸለውን ደምስሶ "ዋጋሽን በመንግሥተ ሰማያት አከፍልሻለሁ ልጆችሽንም ከሰማዕት አቆጥርሻለሁ" ብሎ መልሶታል።

ይህን አይቶ ጲላጦስ ሊፈታው ፈለገ። እነርሱ ግን እመሕልለው ለዝንቱ ኢኮንከ ወርኅ ለቄሣር - ይህን ከፈታህ የቄሣር ወዳጅ አይደለህም ስቅሎ ስቅሎ - ብለው ይጮኹ ጀመር። ውኃ በሙስሉት አስመጥቶ ንጹሕ እነ እምደሙ ለዝ ብእሲ ጻድቅ - ብሎ እጁን ታጠበ። አይሁድ ግን ደሙ ላዕሌነ ወዲበ ውሉድነ ደሙ በእኛና በልጆቻችን ይሁን አሉ። ይህም ሊታወቅ ዛሬ አይሁድ ሲወለዱ ደም ጨብጠው እንደሚወለዱ ይነገራል።

የትንቢት የፍርሃት ቃል አልተናገረም እንጂ አመሩን ለሚከተሉ አብነት ሊሆን ሰባቱን አጽራሐ መስቀል ተናግሯል።

እነርሱም
1. አምላኪየ አምላኪየ ነጸረኒ ወለምንት ገደፍከኒ
2. አባ ሥረይ ሎሙ ኃጢአቶሙ እስመ ኢያአምሩ ዘይገብሩ ሉቃ23-33 በመላእክት ያመጣዋል። አካሉ ደም ለብሶ እርቃኑን ተሰቅሎ እይተውት ደንግጠው እንዲሽሽ ተነሱ። ቅዱስ ሚካኤል ዝም በል! ቅዱስ ገብርኤል ግን ተቆጥቶ ሊያጠፋቸው ሰይፉን መዘዘ። ሲያውቅ ነው ሰ ደፋሀን መልስ አለው። "ሚካኤል እርመመ ወገብርኤል ተደመ" እንዲል ቅዱስ ያሬድ ቸርነቱን እያደነቀ በለቀው የቤተመቅደስን መጋረጃ ከሁለት ከፍሎ ምድርን ሰንጥቆ ገባ እስከ ምጽአት ሊወርድ ደኖራል። ሰለ ከለውተ ምሕረቱ ለአብ ወንዶቹ አውልድ ወትዕግሥት ለመንፈስ ቅዱስ ዘበጠ ለመንጦላዕተ ምኩራብ ወረሰ ከለዕ ከፍሎ "እንዲል ያሬ አበ ዘእትና ክፍል 9
3. ነዋ ወልድኪ ወነያ እምከ ዮሐ 19፡26 ጌታ በተሰቀለ ጊዜ እመቤታችን ዮሐንስ ንጉድት እየወደቀች እየተነሳች መጥታ ከእግረ መስቀሉ ሆና ስታለቅስ ነፍግ ሐዘት ሲያጠጣኝ በመር ልጅነኝ ብታይ በኃለን ትዋት የለምን? ብላ እናቴ ሆይ ልጅሽ እነሆ አላት! ዮሐንስንም እነሆት እናትህ ልጅ ሁናት ብሎ አደራ አቀበለ። ይህም ለዮሐንስ ብሆን ፍጻሜው ለሁላችን ነው።
4. ኤሎሄ ኤሎሄ ላማ ሰበቅታኒ ማቴ 27፡46 አምላኬ አምላኬ ለምን ተውከኝ [illegible]
5. የዮም ትሄሉ ምስሌየ ውስተ ገነት ሉቃ 23፡43 ዛሬ በገነት ከእኔ ጋር ትኖራለህ [illegible]

አለው። አምላክ ሰው ሆኖ ተሰቅሎ በሞቱ ዓለምን እና ሰላኔም ደመማንትመን መጥቶ ላከኝ አለው። አዳም ነህን አብርሃም ይስሐቅ ያዕቆብ ነህን? አለው። አይደለሁም እጄን በሰው ደም ነክሬ የኖርሁ ሽፍታ ነኝ። ሰባቱን ተአምራት አይቼ አምላክነቱን ተረድቼ ብማፀነው ለዚህ ክብር አበቃኝ ብሎ 5493 ዘመን ተዘግታ የነበረች ገነትን በደመ ማኅተሙ ከፍቶ ገብቷል።



6. አባ አመሐጸን ነፍስየ ውስተ እደከ ሉቃ 23፡46
7. ተፈጸመ ኩሉ ዮሐ 19፡30 በነቢያት የተነገረው በመጽሐፍ የተጻፈው ሁሉ ደረሰ ተፈጸመ ሲል ነው። እኒህን ተናግሮ ራሱን ወደቀኝ ዘንበል አድርጎ ቅድስት ነፍሱን በሥልጣኑ ከክብርት ሥጋው ለየ።

በሲኦል የነበሩ ነፍሳት ዐልካለ ነፍስ ወርዶ የተወጋ ጎኑን ቀኝ ከንፋን አሳይቷቸው ይኸው ተምቶት ቁርባን ሆናቸው ዲያብሎስ በዕብ ሩኩም ጽር ያኖረውን የዕዳ ደብዳቤ አጥፍቶላቸው ስብሐት ለእግዚአብሔር ዘአውረሰ መንግሥቶ ለማያዊት እያሉ እየመሰገኑ ወጥተው ገነት ገብተዋል። "ወንደነ ሥጋሁ ስቁለ ዲበ ዕፀ መስቀል ወነፍሱሰ ወረደት ወበተ ሲኦል ወፈወሰት ነፍሳተ እለሀለው ሆ ወኤወወት ቢኦለ ወአገብዐት ኩሉ ፍጥረታተ "እንዳለ አትናቴዎስ በሃይ.አበ.

ነፍሱ ከሥጋው ከተለየ በኋላ ለንጊኖስ የሚባል ሐራዊ ቀኝ ጎኑን በጦር ወጋው። ወጋና ትክል ደም ወንጌ ሆኖ ፈሰሰ። ደሙን መላእክት በጽዋ ብርሃን ተቀብለው በዓለሙ ሁሉ ረጭተውታል። ለንጊኖስ አንድ ዓይና ነበር፣ ደሙ ቢነጥበበት በርቶለታል። ኋላም ትንሣኤውን አይቶ መሰክሮ ለሰማዕትነት አርፏል። ወዘርአየ ሰማዕ ከነ ወጽድቅ ወእቱ ሰምዑ እንዲል ዮሐ 19፡35

ወነሥኡ ሥጋሁ ለእግዚእ ኢየሱስ ወገነዝዎ በመዋዕል ዘበንዱናት ይላል። በ11፡00 ሰዓት ዮሴፍ ዘአርማትያስና ኒቆዲሞስ ከጲላጦስ አስፈቅደው ሥጋውን ከመስቀል አውርደው ሽቱ እየረበረቡ በሐዲስ በፍታ ገነዙት። ሲገንዙትም ወእንበበ እዕይንቲሁ ይላል ዓይኖቹን ገልጦ አድርጎ ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት እያሉ ገንዙኝ ብሏቸው እንዲሁ እያሉ ገንዘውታል። አከብራችሁ ለግኖቻ እንደከበሩኝ እኔም አከብሬ በመግረጉ ዕንቁ መንበር እናርፍችኋለሁ ብሎም ተስፋቸውን ነግሯቸዋል።

ከዚህ በኋላ በምስተኛ ቀን የሚነግ ነዋና የአልዓዕ እጅም ሙት እንዳነሳ ከነቢያቱ የአንዱ አጽም እንቀው እንዳደሱ ዮሴፍ ለራሱ ባሠራው ሰው ባልተቀበረበት አዲስ መቃብር ቀብረውታል። ዮሐ 19፡41

ለምሳሌ እንደእንገዳ ወደዓለም ቢመጣ
ዕዳንና ወቀቱ ብርሁ ሳይታጣ
ለስታቸች አይሁድ አሉት ሐሞት ጠጣ።
ቅዱና እንዳትቀር በገነም ነፍስ
ለምም በበደለ ሞተ ክርስቶስ።
መስቀል ተሰቅሎ ያልእንገላች ተፋት
ለሕያዋን ለምሳለ እንደምን ይሙት?
ሚስቶቱራስትን ፈርተው መላእክት
አይሁድ በእንጨት ሰቅለው በጦር ሲወጉት
በችንካር ቸንከረው ደሙን ሲያፈሱት
ዕሬታ ደም ብትሆን ወሐያም ጽልመት
በምኩብት ቢረገቀ ብትርድ መሬት
አለገም ቢያገለ እንጂ እሬ ቢል ፍጥረት።
ዓኙ ከፋ. መቃብር ምሕረት የሌላት
በንፋን ጀድቅ ወጣ አልበቃሽ ያላት
መጣላት ጌታዋ ዛሬስ ይውጣላት
እንቺ ተንከራታች ድንገል ያኔ በዛ

በልጅሽ መስቀል መከራሽ ቢበዛ
እንባሽ ጎርፍ ሆኖ ሲወርድ እንደዋዛ
ውበት ደምግባትሽ ሲረግፍ እንደጤዛ
ግንዉ አይሆሽ ያለሽ የቀ ልብ የዛ
እንቺው ቻለሽው እንጂ ልብሽ በገዘፈን ፈቀ።
ጸድቅ ተከንና ኃጥኡ ሲጸድቅ
ሐቀኛ አልቅሶ ወሸታም ሲስቅ
ተማኘው ሲደሰት ሲገድ ሲሳቀቅ
ምን አልሽ ይሆን ነሉ ም ምንተናገሽ ሐቅ?
ምድራዊ ዛም አትበይ መስከራ ሆቀን
ኀዘናውን ማቅናት ማገናት ምውቱን
ያዘጋል እንጂ ያስቅላልን?
ምስጋና ይድረሰው ከብር ይግባው አሜን
በሞቱ ገድለው ዉሾት ሞትን።
ሲኦል ጠም አደረች ኢጋገጉት አፈሩ
ምርኳቸው ተነተቀ ባሻቸውን ቀሩ።

ኢሳ 25፡8 1 ቆሮ 15፡54 1 ጴጥ 3፡18

ሰ- ዕረፍቱ ለአባ መቃርስ ዘየዐቢ

መቃርስ (መቃርዮስ) ማለት ቅዱሱ ለእግዚአብሔር ማለት ነው። ሀገራቸው ሳሱዊር ነው። አባታቸው አብርሃም እናታቸው ማሪያ ይባላሉ። አባታቸው ካህን ነበር። የተወለዱት በብስራት ቢሩብ ነው።

ካህለ መጠን ሲያደርሱ ግድ ብለው ይህ ቀረሽ የማትባል ቆንጆ አጭተው አጋቧቸው። በድንግልና ለመኖር ይሹ ነበርና አመመኝ ብለው ከቤተ እግዚአብሔር ገብተው ከዚያ ሰነበቱ። ሲመለሱ ሙሽራት ሞታ አገኙ። እርሷን በድንግልና ሳለች የወሰዳት እኔም በዚሁ እንድኖር ፈቅዶ ነው ብለው ደስ አላቸው።

ሰባት እናታቸውም ብዙ አልቆዩም ተከታትለው አረፉ። ገንዘቸውን ለድሃ በኋላ ያለውን ሀብት ንብረት ሁሉ ሰጥተው መጽውተው ማዕቀና ተቀብለው ከቤተእግዚአብሔር በዓት ሠርተው ተቀመጡ። ሰይጣን ለምቀኝነት እያርፍምና ግብራቸውን ጠልቶ ሞታቸውን ሽቶ ብዙ እንሳባቸው። ለሀገሩ ባላባት አንዲት የደረሰች ልጅ ነበረችው

እያሉ በዘመኑ ኖሀ ሮማብ "ሐጸ ማየ አይኅ" "ኀትገ ማየ ድምሳሴ" ስትል ቁጣ የወይራ ቅጠል ይዛ እንደተገኘች "ሐጸ ማየ ኃጢአት" "ኀትገ ማየ መርገም" ሲሉ ቁጣ ለምእመናን ያድላሉ።

ሰ. ዕረፍቱ ለቈስጠንጢኖስ ጻድቅ (272 - 337 ዓ.ም)

ሀገሩ በራንጥያ (ቁስጥንጥንያ) ነው። አባቱ ቀንስጣ ይባላል። የበራንጥያ ንጉሥ ነበረ። መንግሥት ለማሻረስ ወደ ሰርቢያኒስ ሔደ። ዕሌኒን ከባህር ተጥላ አግኝቷት ሚስቱ አደረጋት። አረሚ ቢሆንም ቅሉ ከፋት የለውም ነበር። ዕሌኒ ግን አረሚ በመሆኑና ልጇን ልታስጠምቅ ባለመቻሏ ታዝን ነበር። ዳሩ ግን ጌታ ዓምደ ቤተክርስቲያን እንዲሆን መርጦታልና ከእናቱ ትምህርተ ክርስትና እየተማረ ከክርስቲያን ጋር እየተባበረ መንፈሳዊ ሆና አደገ።

አካለ መጠን ሲያደርስ አባቱ ሥርዓተ መንግሥት አውጥቶለት ዘውድ ደፍቶለት በሁለት ዓመቱ አረፈ። በብራንጥያ ሰባት ዓመት ከነገሠ በኋላ ሮማውያን ንጉሥ መክስምያኖስ አገዛዝ አጽንቶብናልና መጥተህ አድነን ብለው ላኩበት። ሲያስበው ውሉ ሌሊት በሕልሙ "በዝ ትእምርተ መስቀል ትመውእ ለጸርከ - ጠላትህን በዚህ ትእምርተ መስቀል ታቸንፈዋለህ" የሚል ጽሑፍ የተቀረጸበት የብርሃን መስቀል አየ። ምን ይሆን እያለ ሲያወጣ ሲያወርድ የታዘዘ መልአክ መጥቶ እንዳየኸው አድርገህ አሠርተህ ያዝ ታቸንፈዋለህ አለው። ከዘውዱ ጀምሮ እስከ ተራ የጦር ዕቃ ድረስ በሁሉ ላይ መስቀል አስቀርጾ ገጥሞ ድል አድርጎታል።

ከዚህ በኋላ ሮምን ጠቅልሎ መግዛት ጀመረ። በዓመቱ "አብያተ ጣዖታት ይትዐፀዉ ወአብያተ ክርስቲያናት ይትረኀዉ" ብሎ አውጀ በመክስምያኖስና ዲዮቅልጥያኖስ ዘመን የፈረሱ የተነከሱ አብያተ ክርስቲያናትን አሠራ፣ የተዘረፉ ንዋያተ ቅድሳትን መለሰ፣ አብያተ ጣዖታትን አፈረሰ፣ ርስት ጉልታቸውን ለቤተክርስቲያን ሠጠ። ይህም በቤተክርስቲያን ታሪክ ለክርስትና እምነት መስፋፋት ከተደረጉ አስተዋጽኦዎች አንዱና ታላቁ ነው።

በኮረ ሰይጣን አርዮስ የተወገዘበት፣ አምስቱ አዕማደ ምስጢር፣ ጸሎተ ሃይማኖት፣ የተረቀቀበት ሌሎችም ድርሳናት የተጻፉበት

የመጀመሪያው የኒቅያውንት ስብሰባ (ጉባኤ) በኒቅያ የተደረገው በርሱ ዘመነ መንግሥት በርሱ ፈቃድና ጥሪት ነው። ሙሉ ታሪክ በክፍል 1. ገጽ 63
በመጨረሻ ስነ በዓል ለማየት ኒቆምድያ ደርሶ ሲመለስ ታመመ በሊቀጳጳሳቱ በአባ ሶል ሲጥሮስ ተጠምቆ በተወለደ በ65 ዓመቱ በዚህ ዕለት ዐርፏል። ቈስጠንጢኖስ ጥምቀት ነዋ ልብስ ናት። ደጋ ብበድል ፍርድ ባጎድል እሳድፋታለሁ እያለ ያስብ ነበር። በፍጻሜ ዘመኑም መጠመቁ ስለዚሁ ነው። ይልቁንም አብያተ ክርስቲያናትን ከማሠራት ክርስቲያንን ከጥፋት ከመታደግ የበለጠ እለን? ደጋ ብበድል ፍርድ ባጎድል ሳልከው ግን ፈቃደ እግዚአብሔር ጠይቀን ሕግ እንሠራልሀለን ብለው ፍትሐ ነገሥትን፣ ገሩም ቅዳሴንና ሕንፃ መነኮሳትን ጽፈው ቢሰጡት እንጂ ሠለስቱ ምዕትን ደጋ ብበድል ፍርድ ባጎድል እናንተ መከራ ተቀብላችሁ የምትገቡባትን መንግሥተ ሰማያትን ልወርስ እችላለሁን መንግሥቴን ትቼ ገዳም ገብቼ እንድኖር አስናብቱኝ እናንተ የወደዳችሁትን እንግሥትቱ ኑሩ ብሉ ሕልቀተ ወርቅን! ሕለተ ወርቁንና አክሊለ ወርቁን ሰጥቷቸው ነበር። ከብፉንም አባ ብሶይ አይተው መስክረዋል። በዓታቸውን ዘግተው ሲጸልዩ ቈስጠንጢኖስ በአካለ ነፍስ መጥቶ ሰላም ለከሙ አ ብዑዓን መነኮሳት አላቸው! እንተም እንጂ በዘመንህ ቀርነ ሃይማኖት ቀሚአና ብፁዕ ነህ አሉት። ከዚያ በኋላ ለደቀመዛሙርቱ ነገሯቸዋል።
ዜና አበው

ደግ እናት ዕሌኒ ዘአምኑቲ ጸንታ
ደግ ልጅ አስገኘች የሚሆን አለኝታ
ሰላም ለጠማው ሕዝብ ለሚሻ ጸጥታ
ታላቅ ሰው እንዲሆን አምላክ መርጦት
ለቤተክርስቲያን መሰሶ ሆኖት።
የሰማዕታቱ ደም እንደገርፍ ፈሶ
ተበጋ ሆኖ አጸግቸው በምድር ተከስጦ

አልቀረም በከንቱ ቈስጠንጢኖስ ንጉሥ
አይተን ደስ ተሰኘን ጠላት ተደምስሶ
መንግሥት የእግዚአብሔር እውቀ መሆኑን
አገለገለት ፈጣሪ አምላኩን።
ሰዎች እንታቢይ ዘመታችን
በሁቶት አገመካ አይጠፉ መሰሉን
በተ ለንሥሪበት ነው የተሰጠን።

መጋቢት 29 - ብስራት (በዓለ ትስብእት)

ታሪኩ በክፍል 1 መጽሐፍ ገጽ 110 ተጽፏል

በዝሙት ጸነሰች። ልጁ ምነው እንዲህ አደረግሽ ብሎ አዘነ። ሰይጣን ለዚሁ ምክንያት አድርጎ መርሟታልና ቤተእግዚአብሔር እጅ ልነሳ ብሄድ አባ መቃርስ እንዲህ አደረገኝ አለች። ተቆጥቶ ሄዶ እጅ እግራቸውን አስሮ ይገርፋቸው ጀመር። ይህን ያህል የምትገርፈኝ ምን በደልሁህ? አሉት። በደልህንማ አንተው ታውቃለህ ብሎ ሥጋቸው እስኪተፈተፍ ድረስ አብዝቶ ገረፋቸው።

ይህም አልበቃ ብሎት በሰንሰለት አስሮ እየጎተተ ሲወስዳቸው ሁለቱ መላእክት በእምሳለ ወራዙት ቀርበው ምን አጥፍተ ነው። አሉት። ልጄን አስነውሮ እኔን አሳፍሮ ነው አላቸው። ይህንንስ እንደማያደርግ እናውቃለን፤ ባይሆን እስክትወልድ ድረስ ልብሷን ቀለቧን ይሰጣል በዋስ አስናብተው አሉት። ማን ይዋሰዋል? አለ። ሕማማቸውን አይቶ ያዘነ አንድ መንገደኛ እኔ እዋሳለሁ ብሎ አስለቀቃቸው።

ከቁስላቸው ሲድኑ መልአኩ መጥቶ ለዚያች ሴት ቀለቧን ልብሷን አትሰጥምን? አላቸው። ቅርጫት እየሰሩ ሸጠው ሲሰጧት ቆዩ። የመውለጃ ጊዜዋ ሲደርስ ምጥ ፀንቶባት አራት ቀን ተጨነቀች። እናቷ ልጂ ጌታን ያስቀየምሽው ነገር እንዳለ አሰቢ። የአባቴን ቁጣ ፈርቼ እንጂ የጸነስኩት ከአባ አይደለም አለች። ያን ከሆነ በከንቱ አስቀይመነዋል አሁንም ሳትሞት እንማጸነው ብለው ሲሄዱ በመንፈስ ቅዱስ ተገልጦላቸው ይህማ ውዳሴ ከንቱ ሊሆንብኝ ነው ብለው ከበዓታቸው ወጥተው ሲሸሹ መልአኩ በክንፉ ነጥቆ ገዳመ አስቄጥስ አድርሷቸው ይህ ቦታ የአንተና ልጆችህ ነው። እንዲህ አድርግ እንዲህ አታድርግ ብሎ ሥርዓት ሠርቶላቸዋል።

አጋንንት እየተፈታተኑ ቢያስቸግራቸው መልአኩ መርቶ ከአባ እንጦንስ አገናኝቸው ሥርዓተ ምንኩስና ተምረው ተመልሰው ኋላም አባ እንጦንስን ገንዘው ቀብረዋል። ከዚህ በኋላ ግን መከራውን በትዕግሥት ሰይጣንን በጸሎት ድል ነሥተውታል። አንድ ቀን አጋንንት ከበዓቱ ደጃፍ እሳት አንድደው ዓሣውን እየታፈኑ ይጥሉባቸው ጀመር። ስመ እግዚአብሔርን ጠርተው ቢያማትቡባቸው እንደ ጢስ ተነው እንደ ትቢያ በነው ጠፍተዋል። ኋላም ጌታ ሰንገድላቸው እንዲገለጽ ብዙ ደቀመዛሙርትን አመጣላቸው፤ ሥርዓተ ምንኩስና አስተምረዋቸዋል።

በዘመናቸው በሀገረ እውሲም ትንሣኤ ሙታን የሚል መናፍቅ ባሕታዊ ተነሥቶ ምእመናንን ሲያስተምር ሄደው ወንድሚ የዘሩት ሲበቅል የተከሉት ሲጸድቅ አላየህምን ብለው በምሳሌ አስተምረው አንድ ሙትም አሥነስተው አሳይተው አሳምነውታል። በመጨረሻም በስግቸው የተግጸነ ከዕፃ ከፍፃ እንደሚድን ተስፋቸውን ተቀብለው በተወለዱ በ97 ዓመታቸው በዚህ ዕለት አርፈዋል።

- የነበሩት በ4ኛው ም.ዓ. ድኑሉከ ነው።

ቅዱስ መቃርዮስ የመንፈስ አርበኛ
በሕሉት ድል ነሥቶ የሰውን ደመኛ።
የንስም ብልጽግና ግለቱን አበበ
በትኅርምት ኖረ በአራዊት ተከቦ።
የጠላት ፈተና መሆኑን ተረድቶ
ሲገርፋት ዝም አለ በትዕግሥት ፀንቶ።

ለአምላክ ዘንድ ከፍ ቢል ከብርና ሞገሱ
የሚያነጋግረው መልአክ ነበር ለርሱ።
ያልጋጠኢቱ ሰውን ማስተየም
የኋላ የኋላ ያመጣል መረገም።
በመልክም እንድትኖር ሳያኝሁ ፍቶ
ፈጽሞ አታስብ ማንንም ልትነቁ።

ኢሳ 41፡16 1 ተሰ 5፡15 2 ቆሮ 13፡7

መጋቢት 28 ሀ. ቀዳም ስዑር

ዐባይ ሰንበት፣ ቀዳም ስዑር ትባላለች። ዐባይ ሰንበት መባሏ ጌታ በጥንተ ፍጥረት ከእሑድ እስከ ዓርብ ሲፈጥር ሰንበቱ በሰባተኛዋ በቀዳሚት አልፈጠረም። ዕረፍባት ሲል ሥራውን ፈጽሞ አርፎበታል። ወአእረፈ እግዚእ እምኩሉ ዘእገበ ይገበር እንዲል ዘጸ 20፡11

5500 ዘመን ሲፈጸምም ከሰማያት ወርዶ ከድንግል ተወልዶ ሰው ሰውኛውን ኖሮ የማዳኑን ሥራ ዐርብ በመልዕልተ መስቀል ፈጽሞ በአዲስ መቃብር አርፎ ውሎባታልና ስለዚህ ነው።

ስዑር መባሏም ደቀመዛሙርቱ ዓርብ ሕማሙን ሞቱን አይተው እዋታለሁ ብሉን ሕማሙን ሞቱን አየን፣ እነሳለሁ እንዳለንስ ትንሣኤውን ሳናይ እንቀራለን ብለው ከምግብ ተከልክለው ሲያዝኑ ውለዋል። ስዑር መባሏ ብትሻር አይደለምን ብለው ሲሰሩባት ተድላ ደስታ ሲያደርጉባት የሚውሉ ቢኖሩም እውነታው ግን እንዳልነው ሕማሙን ሞቱን እያሰብን የምንጾምባት የምናዝንባት ስለሆነ ነው። በንግህ ካህናት የንግህ ተግባራቸውን አድርሰው ገብረ ሰላም በመስቀሉ

ሰ. ትንሣኤ

"ሞተ በፈቃዱ ወተቀብረ በሥምረቱ" ሃይ. አበ. ዘአትና. እንዲል። በፈቃዱ ሞተ በወዱ ተቀብሮ ሦስት ቀን ሦስት ሌሊት በከርሠ መቃብር አድሮ መግነዝ ፍቱልኝ መቃብር ክፈቱልኝ ሳይል በገዛ ሥልጣኑ በዘመነ ማርቆስ እሑድ በመንፈቀ ሌሊት ተነስቷል። "ወተንሥአ በሥልጣኑ - ባሕቲቱ" እንዳለ ቅ.ቄርሎስ

የተቀበረ ዓርብ በሠርክ የተነሣ እሁድ በመንፈቀ ሌሊተ ከሆነማ 3 ቀን 3 ሌሊት በመቃብር ቆየ መባሉ እንደምን ነው? ቢሉ ዕለተ ዓርብ ከሦስት ታከፍሏል። ከነግህ እስከ ቀትር ሰዓቱ አራት ነው። ብርሃን ሆኗል፣ ቀትር ከነ ሌሊተ ወጸልመ ኩሉ ዓለም እንዲ ሉቃ 23 ፡ 44 አንድ ሌሊት። ከዘጠኝ እስከ ሠርክ ሰዓቱ አራት ነው ብርሃን ሆኗል። ሁለተኛ ቀን፤ ሌሊቱ ሁለተኛ ሌሊት፤ ቅዳሚ ተኑ ሦስተኛ ቀን ሌሊቱ እስከ መንፈቀ ሌሊት ሦስተኛ ሌሊት ነው። ያውስ ቢሆን የተቀበረ በሠርክ ነው። እስከዚያ ያለው ስለምን ተቆጠረ ትለኝ እንደሆነ ሕማሙ ሞቱ ቁጥሩ ከዚያው ነውና።

ትንሣኤውን በሦስት ቀን ያደረገው በ2 ወይም በ4 ያላደረገው ስለምንድር ነው? ቢሉ ትንቢቱ ምሳሌው ይፈጸም ዘንድ ነው። ትንቢት - እርሱ ባለቤቱ "እስመ በከመ ነበረ ዮናስ ውስተ ከርሠ አንበሪ ሠሉሰ መዋዕለ ወሠሉሰ ለያልየ ከማሁ ይነብር ወልደ እጓለ እመሕያው ውስተ ልበ ምድር ሠሉሰ መዋዕለ ወሠሉሰ ለያልየ" ብሎ ተናግሯል። ማቴ 12፡40

ምሳሌም ዮናስ ሦስት ቀን ሦስት ሌሊት በከርሠ አንበሪ አድሮ ወጥቷል። ከርሠ አንበሪ የመቃብር ዮናስ የጌታ ምሳሌ ነው። ትንቢቱን ባወቀ ተናገረ ምሳሌውንም ባወቀ አስመሰለ ፍጻሜው ግን ኃጢአትን በምድር፣ መርገምን በመስቀል፣ ሞትን በሲኦል፣ ጥፋትን በመቃብር ማጥፋቱን ለማጠየቅ ነው። "አስተጋፈረ ኃጢአተ በዲበ ምድር ሠሥዐረ መርገመ በዲበ ዕፀ መስቀል ወአብጠለ ሞተ በውስተ ሲኦል ወነሥተ ሙስና በውስተ መቃብር" እንዲል። ሃይ. አበ. መቃብሩን ሲጠብቁ የነበሩ አራት ጭፍሮች መግነዝ ፍቱልኝ

መቃብር ክፈቱልኝ ሳይል በአካለ ብርሃን ሲነሣ፣ መላእክት ከእግሩ እንደሻሽ ተነጽፈው ሲያመሰግኑት ደንግጠው ሲሾኩ ወደ አይሁድ ሄደው ተነሣ አሏቸው። ቢሄዱ መቃብሩን ተከፍቶ አገኙት። ልብሳቸውን እየቀደዱ ይጮኹ ጀመር። 400 ወቄት እንሰጣችሁ ተኝተን ሳለ ደቀመዛሙርቱ ሰረቁት በሉ አሏቸው።

ደቀመዛሙርቱ አይሁድን ፈርተው ተሸሽገው ነበር። ማርያም መግደላዊት ግን ሽቱ ይዛ እንዘ ዓዲሁ ጽልመት ይላል ገና ሳይነጋ ሄደች። ሌሎችም ተከታትለው ከመቃብሩ ደረሱ። ጌታችንን ወስደውታል እያሉ ሲያለቅሱ መልአኩ ለምንት ተኃሥሣሁ ለሕያው ምስለ ምውታን ተንሥአ ኢሀሉ ዝየሰ ስለምን ሕያውን ከሙታን መካከል ትፈልጉታላችሁ? ተነሥቷል ከዚህ የለም፤ ይልቁንስ ተነሥቷል ገሊላ እቀድማችኋለሁ ያላችሁን እስቡ ብላችሁ ለደቀመዛሙርቱ ንገሯቸው አላቸው። ሄደው ተናገሩ። ጴጥሮስና ዮሐንስ እየሮጡ ሄዱ። በደር ለጴጥሮስ ይላል ዮሐንስ ቀድሞ ደረሰ። ነገር ግን ርዕሰ ነውና ከውጭ ሆኖ ጠብቆ ከጴጥሮስ በኋላ ገባ። መግነዙን እንጂ እርሱን አላገኙም፤ በእውነት ተነሥቷል እያሉ ተመለሱ።

ማርያም መግደላዊት ግን የደረሰበትን ሳታውቅ አልሄድም ብላ ቆማ ታለቅስ ነበር። ጌታ ከወደኋላዋ መጥቶ ምን ሆነሽ ታለቅሻለሽ? አላት። ጠባቂ መሰሏት ጌታዬ አንተ ወስደኸው ከሆነ ሽቱ እንድቀባው ያደረግህበትን አሳየኝ አለችው። ማርያም ብሎ ስሟን ሲጠራት ጌታ መሆኑን ተረድታ መምህር ሆይ ብላ እጅ ልትነሳው ቀረበች። ኢትልክፍኒ እስመ ዓዲ ኢዐረገ ኀበ አቡየ ገና ወደ አባቴ አላረግሁምና አትንኪኝ አላት። ይህ ሴቶች ሥጋ ደሙን መቀበል እንጂ ማቀበል እስመቻላቸውን ያጠይቃል። ኋላ ቶማስን ጎኑን ያስዳስሰዋልና። ዮሐ 20፡27 ሄደሽ ለደቀመዛሙርቱ ተነሣ ብለሽ ንገሪያቸው አላት፤ ሄዳ አብስራቸዋለች። ዮሐ 20፡11-17

በእመቤታችንም ያመጣዋል፦ በነግህ ብትሄድ ደንጊያው ተገልብጦ መግነዙ ተቀምጦ አገኘች። ምርር ብላ ስታለቅስ ጌታ ሰማያዊ ግምጃ ተጎናጽፎ እኩሉ እንደ ፀሐይ አብርቶ መጥቶ ብታለቅሺ ብታለቅሺ አትደክሚምን? አላት። አይሁድ መስቀል መግደል እንዳያበቃቸው ሥጋውን ወስደው ገዘን ጨመሩብኝ አገኘሁ ቢሆን በተጽናናው ነበር አለች። በውኑ በጦር የተወጋ ጎኑን፣ በችንካር

የተቸነከሩ እጆቹን እግሮቹን! በእከሊለ ሦክ የተቆራረሰ ራሱን ስታዪ ትጽናኛለሽ? ይልቁንስ እይሁድ በልጅሽ ተማምለውበታል! እንቺ ግን ከኀዘንሽ ተጽናንተሽ ወደ ቤትሽ ሂጂ አላት። ነገሩን የምታውቅ ተመሰላለሁና እባክህ ያለበትን አሳየኝ አለችው። ፍጹም ኀዘኗን አይቶ አይሁድ የሰቀሉት አንቺም የምታለቅሺለት አንድ ልጅሽ እኔ ነኝ አላት። ደስ አላት እናቱ ሆይ እያሁድ መነሣቱን ሊያስተባብሉ ከዚህ ይመጣሉና ምክንያት እንዳያገኙ እንዳይሉ ወደ ደቀመዛሙርቱ ሂጂ ብሏት ሄደለች።
ሳሎ-ማርያም ሉቃ 24:10



ጲላጦስ ጌታ በመስቀል ሆኖ የተደረጉትን ሰባት ተአምራት አይቶ ደግ ሰው አስቀያለሁ ብሎ አዝኖ ሳለ ጌታ በሕልሙ ምኞ የቀረሁ መሰለህን? ግረኝ ብትለኝ እምርሀ የለምን ሲለው አየ። በነግህ አይሁድ መጥተው ሥጋው ተሰርቋልና ጠባቂዎችን አስጠርተህ መርምርልን አሉት። ሲመረምራቸው አንዱ ጴጥሮስና ዮሐንስ ሠረቁት! ሁለተኛው እምራ እንዱ ሁሉ ሠረቁት! በሦስተኛው የሴፍና ኒቆዲሞስ ወሰዱት አሉ። አራተኛውን እውነቱን ንገረኝ ብሎ ቢገሥፀው ከእንቅልፍ ሰንነቃ ከውጋ ነድጓድ ተገሎ እገኘው ፤ ይህንንም ያደረጉ ደቀመዛሙርቱ ይሆናሉ ብለን እንጂ ሲወስዱትስ አላየንም አለ። እራቱንም ከገዙት ቤት እስገብቶ የመቶ አለቃውን ከነጭፍሮቹ አስከትሎ ከመቃብሩ ሄደ። መግነዙን አይቶ ደቀመዛሙርቱ ወስደውትስ ቢሆን ይህንንም ባልተውት ነበር ብሎ መግነዙን ይዞ ያለቅስ ጀመር። እኔስ ጌታ እንደተነሳ ይህም መግነዝ ለጠር እንደሚያበራ እምናለሁ ብሎ መቶ አለቃውን ቢያስለው የጠፋች አንድ ዓይኑ በርታለታለች። ወዲያውም ዮሴፍ ኒቆዲሞስን ጠርቶ አስመሰከራቸው። አይሁድ እነርሱ ከኛ እድል ፈንታ ጽዋ ተርታ የላቸውም! አንተ ተነግ የምትለው ግን ያውልህ ከኑድጓድ ወድቀልሀል አሉት። ከመቶ አለቃው ጋር ተሸከም እምጥቶ ከመቃብሩ አንብቶ ደንጊያውን ንዋየ ጌታቹ ሆይ የአንተ ከብርህ የአይሁድ ሐሰታቸው በዚህ መት ይገለጥ ዘንድ እለምንሀለሁ ብሎ ለመነ። መቱ ተነሥቶ በጌታ ቀኝ የተሰቀለ ጥመስ መሆኑን የጌታንም ክብር መስክሮአል። አይሁድ ፈርተው እየተዋዋሁ ይሸሹ ጀመር ያጌቸው እትልቀቁለቸው ብሎ ሥጋቸው እስኪተሬተፍ ድረስ በንመድ እስገርፏቸዋል።

ወዲያውም ተነግ ብሎ ከሄሮድስ ላከበት። እሱም መግነዙን! ዓይኑ የበራለትንና ከሞት የተነሣውን እያቸው ዘንድ ላክልኝ ብሎ ላከበት። እውነት መስሎት ላከለት። ሰዎቹን በሰይፍ አስመትቷቸው በሰማዕትነት አርፈዋል። እርሱንም በሐሰት ከቀሳር እግልቶ ከሚስቱና ከሁለት ልጆቹ ጋር በሰይፍ አስመትቶት በሰማዕትነት አርፏል። ገብ. ሕማ

ከዚህ በኋላ ከደቀመዛሙርቱ ሁለቱ ቀለዮጳና ኒቆዲሞስ ከኢየሩሳሌም 60 ምዕራፍ ወደምትርቅ ወደ ኤማሁስ የርሱን ነገር እየተጫዋወቱ ሲሄዱ ከወደኋላቸው ተከትሎ ደሀ የምትሉት ነገር ምንድነው? አላቸው። ቀለዮጳ አንተ ለኢየሩሳሌም እንግዳ ነህን? ናዝሬዊው

ኢየሱስን አይሁድ ጸልተው ተመቅኝተው እንደሰቀሉት አልሰማህምን? እኛማ ወልደ እምላክነቱን አምነን ተከትለነው ነበር! ዛሬም በነግህ ሴቶች ወደ መቃብሩ ሄደው ሥጋውን አላገኙም! ተመልሰው መጥተው ተነሥቷል አሉን። ይህንንም ጴጥሮስና ዮሐንስ ሄደው አይተዋል አሉት። እናንተ ዝንጉአን ብትሆኑ እንጂ እሱማ እንዲሞት እንዲነሣ ነቢያት ትንቢት ተናግረውለት የለምን እያለ መጻሕፍትን ይተረጉምላቸው ጀመር።

ከሚሄዱበት ሲደርሱ መሽቷል ከእኛ ጋር እደር ብለው ግድ አሉት። ማዕድ ሲቀርብ ኅብስቱን አንስቶ ባርኮ ሰጥቶ ተሰወራቸው። ወተከሥታ አእይንቲሆሙ ይላል ጌታ መሆኑን አውቀው ወደኢየሩሳሌም ተመልሰው ለሐዋርያት ነገሩ። ወዲያውም ጌታ ከዝግ ቤት እንዳሉ በማይመረመር ጥበቡ ከመካከላቸው ቆሞ ሰላም ለኩሙ አላቸው። ምትሀት መስሏቸው ታወኩ። በጦር የተወጋ ጎኑን በችንካር የተቸነከሩ እጆቹን እግሮቹን አሳይቷቸዋል። በዚያውም ላይ ንሥኡ መንፈሰ ቅዱሰ ለእለ ኀደግሙ ኃጢአት ይትኀደግ ሎሙ ወለእለ ኢኀደግሙ ኢይትኀደግ ሎሙ ብሎ በምድር ያሥሩት በሰማይ የታሠረ በምድር የፈቱት በሰማይም የተፈታ ይሆን ዘንድ ሀብተ ክህነት ሠጥቷቸዋል። ሉቃ 24፡ 1-43

በመቃብር አደር ሦስት ሌሊት ሦስት ቀን
ሳይል መግነዝ ፍቱ አንሥ ደንጊያውን
ብርሃን ተገናዶ ሲነግ መድኅን
ሊያበቅረው አልቻለም ምት ይዞ እርሱን።
አይሁድ እርሱን በቅሎ ደስ ሲላቸው
ከመቃን ቢነግ ፍርሀት ምጣቸው።
በብርሃን ሊቀቅ የሌቀ ደለመት
መላእክት ከሰው ሊያመሰግኑት
መቃን ናቸውና የአይሁድ ሠራዊት

ያገኮራሉ ነበር ተኝተው መሬት።
ግና ወላጆቹ ሃሉ ተደሰተው
በዛ ሥልጣኑ ጌታ እምላክቸው
ከመቃን ተነሥቶ አይተውት በዓይናቸው
እምነቴ በእምላኬ ታላቅ ነው የዳና
ሞቴ በቀብርም እንግልሀፍ።
እግዚአብሔር ጌታ ፈጣሪ
ጓላ እንደታጎዳኝ በት ግብር እዝዘ
እንተን ጌታውን አባቱን መሠለ።

መጋቢት 30 - ዕረፍቱ ለሶምሶን መስፍን

ሶምሶን ማለት ሐዲሱ ለእግዚአብሔር ማለት ነው። ትውልዱ ከነገደ ዳን ነው። አባቱ ማኑሄ እናቱ እንትከይ ይባላሉ። እንትከይ ዕቀተ ማህፀን ሁና ስታዝን ትኖር ነበር። እንድ ቀን እንጨት ስትለቅም የታዘዘ መልአክ መጥቶ ደግ ልጅ ትወልጃለሽ! የወይን ጠጅ

ከመጠጣት ርኩሰም ነገር ከመብላት ተጠበቂ! ለባልሽም ንገሪው! ሕፃኑ ለእግዚአብሔር የተለየ ነውና በራሱ ላይ ምላጭ አያርፍበትም አላት። ለባሏ ነገረችው። ሁለተኛ ሲገለጥልሽ ንገሪኝ አላት። ሁለተኛ ተገልጾ ደግ ልጅ ትወልጂያለሽ አላት። ቶሎኝ ባሏን ለጥራ ብላ ጠርታ አመጣችው። ለርሷ የነገራትን ሁሉ ነገረው። የፍየል ጠቦት አርዶ ሥጋውን አወራርዶ መሥዋዕት አቀረበ። መልአክ በዘንጉ ቢነካው ተቃጠሉለታል! እሱም በጢሱ ዐርጓል። መልአክ አይተው አያውቁም ነበርና ወየልን እንሞታለን አላት። እኛ ከሞትንማ ልጅን ግን ይወልደዋል? አንሞትም አለችው። ወዲያውም ሶምሶን ተፀነሰ።

ተወልዶ ባደገ ጊዜ ኃያል ሆነ። በአሥራ አምስት ዓመቱ ከአባቱ ጋር ወደ ኢሎፍሊ ሄደ። በመንገድ ተሰይቶ ሹር ቢገባ ግሩም አንበሳ አገኘው። በጦጣ መትቶ ገድሎታል። ሲመለስም እስታውሶ ቢያየው አንበሳት በአፉ ውስጥ ማር ሰርተው አገኘ። ማሩን ቆርጦ ከአባት ከእናቱ ጋር ተመግበታል።

በኢሎፍሊ ያያት ቆንጆ ነበረች። አባቱን አጋባኝ አለው። ተስፋ ከተገነረላቸው ከእስራኤል ሴቶች እንጂ ከአሕዛብ ሴቶች አታገባም ብሎ ከለከለው። እርሱ ግን ወድጃታለሁና አጋባኝ ብሎ ግድ አለ። አጭቶ አጋባው። ሠላሳ ያህል ሚዜዎች ተመርጠው ሲያጫዋውቱት ካገኛችሁት ሠላሳ መጎናጸፊያ ሠላሳ ቀሚስ እሰጣችኋለሁ። ካላገኛችሁት ግን እናንተ ትሰጡኛላችሁ ብሎ "እምእለበላዒ ተረክበ መብልዕ ወእምሕረ ሐሉም ተረክበ ጥዑም ከበላተኛ አፍ መብል ተገኘ" የሚል ምሳሌ ነገራቸው። ሦስት ቀን ሲያስቡ ቆይተው የማይሆንላቸው ቢሆን ሚስቱን ጠይቀሽ ንገሪን ብለው አስጨነቋት። ጠይቃ ነገረቻቸው። በተመር ቀርበው ምሳሌህን እንንገርህ አሉት። እሺ አለ። "ከአንበሳ የተፈራ ከማር የጣፈጠ ምን አለ? ከአንበሳ አፍ ማር አገኘህ በሊተህ" አሉት። "እምኢያርሐውክሙ ለዕጐልትየ እምኢረከብክሙ ለምሳልየ - ሚስቴን ባታስጨንቋት ኖሮ ምሳሌየን ባላገኛችሁት ነበር" ብሎ ተናዶ ወደ ጌዳ ወጣ። ሠላሳ ያህል ነጋዴያን ሲያልፉ አግኝቶ ጭንቅናቸውን ሰብሮ መጎናጸፊያና ቀሚሳቸውን ገፎ አምጥቶ ሠጣቸው። በዚህም አዝኖ ወደ ሀገሩ ተመለሰ።

ከሦስት ወር በኋላ የበግ ጠቦት ይዞ ቢመጣ አማቱ ሚስትህንማ ቀረህ ብለን ለሚዜህ ሰርናት። ከወደድህ ታናሿን እንግባ አለው። በዚህ ተመልሶ 300 ቀበሮ ያዘ! 150 ጥራር አዘጋጅቶ እንዱን በሁለቱ ቀበሮዎች ጅራት እያሰረ በእሳት እያቀጣጠለ ለቀቃቸው። ቀበሮዎቹ ደንገጠው ሄደው ሲገቡ ሲሮጡ የኢሎፍላውያንን አዝመራ አቃጠለውት ዋለ።

የሀገሩ ሰው ሶምሶን ያደረገው መሆኑን ሲያውቁ በእጣቱ ፈርደው እማቱን ከሁለቱ ከንብረቱ ጋር ቤት ዘግተው አቃጠለውታል። ሶምሶን ይህን ባታደርጉ ኖር ጠብ ከእናንተ ነበር አላቸው። እርሳ ሆነ ገደለው። ጭንጭናቸውን ሰብሮ በጉተ እጣም ገብቷል። ሄደው እስራኤልን ሶምሶንን ይዛችሁ ስጡን አሏቸው። ነገሩት እጅ እግሩን አስሬችሁ ከሚያ ግሉኝ አላቸው። ግሉት። ሲይዙት ሲወጡ የታሰረበትን በጣጥሶ ተነሣ። የአህያ መንጋጋ አገኝቶ ቢወረውር ባንድ ጊዜ 1000 ሰው ፈጅቷል። ወዲያው ውኃ ጥም ተሰማው። ወደጌታ ቢያመለክት ከአህያው መንጋጋ አፍልቆ አጠጥቶታል። ከጋዛ ሳለ ካደረበት ቤት ሸምቀው ሲጠብቁት መናገሻቸውን እውቆ መዝጊያዎቹ ጋር በመትከሉ ይዞ ከነደረቡ ተሸክሞ ወስዶ ጥሏል።

ከዚህ በኋላ በሴራት ደሊላ የምትባል ሴት ለመደ። ኢሎፍላውያን ወርቅ ብር እንሰጥሻለን ኃይሉ የሚደክምበትን ጠይቀሽ ንገሪን አሏት። ጠየቀችው በሰባት አውታር ብታሥር እደክማለሁ አላት። እሥራ ሶምሶን ኢሎፍላውያን መጡብህ አለችው። በጣጥሶ ተነሣ። አታለልከኝ እውነቱን ንገረኝ አለችው። በሰባት ምራን ብታሥር እደክማለሁ አላት። እሥራ ሶምሶን ኢሎፍላውያን መጡብህ አለችው። ገጣጥሶ ተነሣ። አሁንም ምሽሽኝ ንገረኝ እንጂ አለችው። በዛቱ ቁንዳላዎቹን ከምድር በካስማ መትተው ቢያሲዟቸው እደክማለሁ አላት። እንዲሁ አድርጋ መጡብህ አለችው። ነቅቶ ተነሣ። ከኃይሉም ጽናት የተነሣ ነክማውም የደረሰበት አልታወቀም።

በመጨረሻ እወድሻለሁ ትለኛለህ እንጂ አትወደኝም ብላ ወተሀወከት ነፍሱ እስከ ለሞት ይላል ነፍሱ እስኪትታወክ ድረስ አስጨነቀችው። ኃይሌ በጸጉሬ ነው! እስመ ናዝራዊ ሐዲስ ለእግዚአብሔር የተባልሁ እኔ ነኝ ከተወለድሁ ጀምሮ አልተላጨሁትም አላት። በወይን ጠጅ

አስክራ አስተኝታ ጸጉሩን ቆርጣ ቆርጣ ከጣለችው በኋላ ሶምሶን ኢሎፍላውያን መጡብህ አለችው። ኃይል ተነስቶት መነሳት አቃተው። በዚህ ጊዜ ኢሎፍላውያን ይዘው ሁለት ዓይኑን አጥፍተው እየጎተቱ ወሰዱት። ባቄላ ሲያስፈጩት ኖረዋል።

ጸጉሩ እያደገ ኃይሉ እየተመለሰ ሄደ። አንድ ቀን በዓል አድርገው ሳለ ያን ዕውር አምጡት ያጫውተን አሉ። አንድ ብላቴና እየመራ አምጥቶ ከመካከል አቆመው። ሁለቱን መሰሶዎች በቀኝ በግራ እጁ ይዞ እ እግዚእ እስእለከ አሐተ ሰእለተ ሀየንተ ክልኤሆን አዕይንትየ ትግእ ነፍስየ ምስለ ኢሎፍላውያን ስለሁለቱ ዓይኖቼ ነፍሴ ከኢሎፍላውያን ጋር ትውጣ ዘንድ እለምንሀለሁ ብሎ አንዱን መሰሶ በቀኝ እጁ ሁለተኛውን መሰሶ በግራ እጁ ቢመታው ከፎቅ የነበሩትም ከምድር ያሉትም ሁሉም አንድ ሆነው ጠፍተዋል። በሕይወት ሥጋም ሳለ ካጠፋቸው ጠላቶቹ ያን ጊዜ በሞቱ ያጠፋቸው ይበዛሉ።

መጽ. መሳፍንት ከምዕራፍ 13 - 16 በሙሉ።

• <u>የነበረው በ1300 ዓ.ም ገደማ</u> ነው።

...... //__________

ምዕራፍ 2

ሚያዝያ 1 - ዕረፍቱ ለአሮን ካህን

አሮን ማለት ደብረ እግዚአብሔር ማለት ነው። የሌቀ ነቢያት ሙሴ ታላቅ ወንድም ነው። ሲራ 45፡6 ትውልዱ ከነገደሌዊ ነው። አባቱ ጌታ እስራኤልን ከምድረ ግብጽ ሲያወጣ ሙሴን መስፍን አሮንን ካህን አድርጎ አስነስቷቸዋል።

ኤርትራን ከተሻገሩ በኋላ እስራኤል ሲበድሉ ጌታ በቸነፈር ገሠጻቸው። ሙሴ ወደጌታ ቢያመለክቱ ወንድምህ አሮን ልብሰ ተከህኖ ለብሶ ማዕጠንተ ወርቅ ይዞ የታመሙትን ባንድ ወገን ያልታመሙትን ባንድ ወገን አድርጎ ይጠንላቸው አለው። ወኆሥአ አፋደ ትኑሁ ዘጸሉት ከተረ መዓተ ወእኀሥዐ መቅሰፍተ ይላል እንዳለው አድርጎ ቢያጥናቸው የታመሙት ድነዋል ያልታመሙት ተጠብቀዋል።

ልጆቼ ናዳብ! አብዩድና አልዓዛርም እንደርሱ በክህነት ጌታቸውን ያገለግሉ ነበርና ደቀቀ ቀኀት እስከ ሙቼ ከህነትን ከነልጆቹ ይዞ ሲዝን ደናሬል? ብለው ተመቀኙት። ሙሴን እኛም ከሌዊ ወገን ተወልደናል ሹመን አሉት። አሮን የተሾመ ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው። እናንተም ከእግዚአብሔር አግኝታችሁ ተሾሙ እንጂ እኔ አይደለሁም አላቸው። ይህማ ለወንድሙ ማድላት ነው። ብለው ከሁለት ወቀ የሚበልጡት ልብሰ ተክህኖ ለብሰው ማዕጠንት ብርት ይዘው ሊያጥኑ ገቡ። ጢሱ ሲያርፍባቸው ልብሳቸው ምንም ሳይሆን እነርሱ እሳት እንደለበለበው ገንድ ሆነው ሙሴ አሮን አውጥተው ጥለዋቸዋል። በሙሴም ተነስተው የነበሩ ዳታንና አቤሮን ከነሀብት ንብረታቸው መሬት ውጣቸዋለች። ምክር ሊያደና ወዲያ ወዲህ ይል የነበረ ቆሬም የደረሰበት አልታወቀም ጠፍቷል።

እስራኤል ኃጢአታችንን እያሳሰቡ ይህን ሁሉ መከራ የሚያመጡብን ሙሴ አሮን ናቸው ብለው ሊወግሯቸው ደንጊያ ይዘው መጡባቸው። ከደብተራ ኦሪት ገቡ። ወድያውም የብርሃን ዓምድ ከምድር እስከ ሰማይ ተተከለ። በዚህ ፈርተው ተመለሰዋል።

ከዚህ በኋላ ጌታ ከሁለት ከቤትህ እንዳይጠፋ ምልክት አሳይልሀለሁና ወንድምህ ሙሴ የ12ቱን ነገድ በትራቸውን ሰብስቦ በምሽት ከደብተራ ኦሪት አግብቶ በነግህ ያውጣው አለው። ሙሴ እንደታዘዘው ሰበሰበ። አሮንም የአባቱን የሌዊን በትር አምጥቷል። 12ቱንም በምሽት አግብቶ በነግህ ቢያወጣው የእርሱ ለምልማ አብባ አፍርታ ተገኝታለች። ዘኍ 16፡17 እና 18 (ምሳሌነት አለው። ስንክ 1 ገጽ 95 ተመልከት።)

እንዲህ እያሉ ሐቅለቃዴስ ሲደርሱ እስራኤል ጥም ፀኑ ተሰምቷቸው ውኃ ውኃ ብለው ሙሴና አሮንን አስጨነቋቸው። ደንጊያውን በበትር ሲመቱት ውኃ ፈለቀ። ለወትሮው ንሴብሖን ደግመው ገሥሖ ዘወሀቦሙ እግዚአብሔር . ኪያሁ ሰብሑ - የሰጣችሁ እግዚአብሔርን አመስግኑ ብለው ይሰሟቸው ነበር። አሁን ግን ተናደዋልና ይህን ሳያደርጉ ሳያመሰግኑ ሰሟቸው! እስራኤልም ሳያመሰግኑ ጠጡት። በዚህ ጌታ አዘነ። ታመሰግኑኝ ዘንድ አላመናችሁብኝምና ምድረ ርስት አትገቡም አላቸው። ደኅዉም አልቀረ ሙሴ በሞአብ አሮንም በደብረ ሖር ዐርፈዋል። ዘኍ20፡ 1-29

ሚያዝያ 5 - ዕረፍቱ ለሕዝቅኤል ነቢይ

• የነበረው በ1500 ዓ.ም አካባቢ ነው።

ሕዝቅኤል ማለት ጽኑዕ ጽኑዕ እግዚአብሔር ማለት ነው። ትውልዱ ከነገደ ሌዊ ነው። አባቱ ቡዝ ይባላል! ካህን ነበር። ቁጥሩ ከአራቱ ዐበይት ነቢያት ነው።

እስራኤል ተማርከው ፋርስ ባቢሎን በወረዱ በ30 ዓመት ሀብተ ትንቢት ተሰጥቶታል። ሕዝ 1፡1-3 ከዚህ በኋላ ከሁነትን ከትንቢት

አንድ አድርጎ ይዞ ሃያ ዓመት አስተምሯል። የጌታን ከእመቤታችን መወለድና እመቤታችንም ቅድመ ጸኒስ፣ ጊዜ ወሊድ፣ ድኅረ ወሊድ ድንግል መሆኗን በራዕይ አይቷል። ሕዝ 44: ከምርኮ ከተመለሱ በኋላ እስራኤል አምላካቸውን ዘንግተው በታላቸው አዘው በእጃቸው ሠርተው ላቆሙት ምስል የሚሰግዱ የሚሠው ቢሆን ነሠሻቸው። በዚህ ገድለውታል።

➢ መዋዕለ ትንቢቱ ከ 592 - 570 ዓ.ዓ ነው።

ሚያዚያ 6 - የአዳምና ሔዋን መታሰቢያ

ወይቤ እግዚአብሔር ንግበር ሰብአ በአርአያነ ወበአምሳሊነ ዘፍ 1:26 ይላል ጌታ ከእሑድ ዓርብ ነግህ 21 ፍጥረታትን ከፈጠረ በኋላ አዳምን ከአራቱ ባሕርያተ ሥጋ (ከነፋስ፣ እሳት፣ ውኃና መሬት) ከምስቱ ግብራተ ነፍስ (ለባዊነት ነባቢነት እና ሕያውነት) የ30 ዓመት ጎልማሳ አድርጎ በማዕከለ ምድር በቀራንዮ ፈጠረው፤ ባሕርዩ ባሕርየ መልአክ ወሰብእ ነውና ማዕከላዊ ነህ ሲል ነው።

ሰውም ማለት ሰባት ባሕርያት ያሉት ፍጹም ፍጡር ማለት ነው። ሰባት ቁጥር በዕብራውያን ፍጹም ነውና። እስመ ትልቁ ሰብእ በአርአያ እግዚአብሔር በመፈጠሩ ነው። በፍጥረት ላይ የሰለጠነ ሆኖ መፈጠሩም ፍጹም ያሠኘዋል። "ወሚም ንጉሥ ኩነ ወንቢየ ሳዕለ ኩሉ ዘፈጠረ እንዲል ስንክሳር ይህም ሊታወቅ መላእክት ከእግዚአብሔር ታዘው በየብሱም በባሕርም ያሉትን እንስሳት አራዊት ወደርሱ እያመጡ እሱ ስም አውጥቶላቸዋል። ኩፋ. 4፣ 1-3

ከዚህ በኋላ ወይቤ እግዚአብሔር አኮ ሠናየ ለእጓለእመሕያው ይንበር ባሕቲቱ ለሊ ንግበር ሎቱ ቢጸ ዘትረድኦ ይላል። የሰው ልጅ ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም፤ ረዳት እንፍጠርለት ብሎ እንቅልፍ አመጣበትና ፍጹም ሳይተኛ ፍጹምም ሳይነቃ ከጎኑ

አንድ አጥንት ወስዶ በሥጋ መልቶ የ15 ዓመት ቆንጆ አርጎ ሴትን ፈጠረ። ወአምጽአ እግዚአብሔር ድቃስ ላዕለ አዳም ወኖመ ወነሥአ አሐደ እጽመ እምገቦሁ መልእንተ ነሥአ እጽም ረሰያ ብእሲተ ወአምጽአ ኀበ አዳም አዳምም ዋቀ አጽም እምአጽምየ ወሥጋ እምሥጋየ ይሁች አጥንት ከአጥንቴ ሥጋም ከሥጋዬ ናት ብሎ ሚስት አደረጋት፤ ስሟንም ሔዋን አላት። ሔዋን ማለት እመ ሕያዋን ማለት ነው። ዘፍ 3:20

ይህም የሆነ በዕምንቱ ዓርብ በሦስት ሰዓት ነው። [illegible]
አዳም በተፈጠረ በ40 ቀኑ ሔዋንም በተፈጠረች በ80 ቀኗ ገነት ገቡ። በዚሁ አሴት ወንድ በአርባ ቀኑ ሴት በሰማንያ ቀኗ ርስት ዘውን ማዕነት ይዘው ቤተመቅደስ መግባታቸው፤ ዛሬም እንዲሁ በአርባ በሰማንያ ቀናቸው ለጥምቀተ ክርስትና ቤተክርስቲያን መግባታቸው ስለዚህ ነው። ኩፋ 4፡9-10

በገነትም የታዘዙባቸውን ፍሬ እየተመገቡ 7 ዓመት ከ1 ወር ከ17 ቀን ተቀመጡ። ኩፋ4:16 በዚህ ጊዜም እንስሳት አርደህ ብላን አለበህ ጠማን ሲሉ አራዊትም እጅ ሊነሡ ከአዳም ዘንድ ሄዱ። እርሱም ሁሉን መርቆ ሰደዳቸው። እየተደሰቱ ሲመለሱ ዲያብሎስ ከትዌና ቆይቶ ይህ ሁሉ ደስታ ምን ተገኘቷል? አላቸው። አርደህ ብላን አለበህ ጠማን ብንለው መርቆ ሰደደን አሉት። ጌታችሁ አዳም ምን ይመስላል አላቸው? ከፀሐይ ሰባት እጅ ያበራል አሉት። ያችን ዕፀ ቀርጦ ማን ከእፎ ባደረገልኝ ብሎ አሰበ።

በሌላ ቀን እጅ ሊነሡ ሲሄዱ አግኝቷቸው አስከትሉኝ አላቸው። አይሆንም ብለው ትተውት ሄዱ። አብርል አዝርል የተባሉ ድምፀ መልካም አዕዋፍም ጌታችን አዳም መልከመልካም ነው አንተ ግን መልከ ጥፉ ነህ ብለውት አለፉ። በመጨረሻም የገመል ወገብሬ ታህል የበረቸው አባብ መጣች። አስከትዪኝ አላት። መልክ ጥፉ ነህ አይሆንም አለችው። መልክ ከፉ ካልኖረ መልክ መልካም በምን ይታወቃል፣ በዚያውስ ላይ ካንቺ ከመልከመልካሟ ጋር ሆኜ መልክ ከፉነቴ አይታወቅም አላት። በውዳሴ ከንቱ ተጠልፋ እሺ ብላ አስከተለችው።

ከገነት ሲደርሱ ይህ መንገድ ካላወቁበት ያደክማል፣ እንተዛዘል አላት። እሺ አለች። አዘላት። ጥቂት እልፍ አድርጎ በጽሐ ፍሬ

አይቆት ደግሞ እዚህ ምን አመጣው? እንደውም ካልገደልኩት አላርፍም ብሎ ቤት የሚያህል ደንጊያ አንስቶ ጫነበት። ወተደብተረት ይእቲ ዕብን ላዕለ ርእሰ አዳም ሞተ መዋቲ -ይላል ደንጊያው እንደ ድንኳን ሆኖ ሞቶት ሞተ ቀን ሞት ሊት ቀደምባታል። በምስተኛው ቀን ቅዱስ ገብርኤል እንሥአናት የያዙውን ፍሬ በደመ ለውስ መሠዋት አቀረቡ። ጌታም በገመስ ዕለት ወበ መንፈቃ ዕለት እትወልድ እምወለትከ ወእድኅከ ውስተ መርህብ ወእትበቀል በደመ መስቀልየ ብሎ 5500 ዘመን ሲፈጽም የልጅ ልጅ ከምትሆን ከእመቤታችን ተወልዶ በመስቀል ተሰቅሎ ደሙን አፍስሶ እንደሚያድነው ተስፋ ሰጥቶታል። _ ቀሌምንጦስ

አዳም ይህን ተስፋ ካገኘ በኋላ እያረሰ በምድረ ኤልዳ ተቀመጠ። ኩፋ 5:6 ሚስቱ ሔዋንን በግብር አወቃት፤ ቃኤልን ወለደችለት፤ ሁለተኛ ሩሐ አቤልን ወለደችለት። መንደለ በቃኤል መዋት በኤልዳ ተጀምሯል። በዕድሜ 1 ሺ 130 ተመልክቶ። አዳም በኤልዳ ሞት ምክንያት 4 ዕዓጓ ዘመን አዝኗል። ኩፋ 5:12 ከዚህ በኋላ መልአኩ መጥቶ ናሁ ወለድከ አሜላ ተገለጦ ለዛሩ ልጅ አለው፤ ከገነት ተደናና ወንድ ልጅ ተወለደለት ስሙን ሴት አለው። ምትክ ማለት ነው። በዚህ ጊዜ አዳም የ230 ሔዋን የ215 ዓመት ዕድሜ ሰዎች ነበሩ። ከሴትም በኋላ ብዙ ወንዶችና ሴቶችን ወልደዋል።

ጊዜ ዕረፍቱ ሲደረስ አዳም ልጁ ሴትን ባለሞት እንድጠርኩቸው ልጆችህን አምጣ አለው። አምጥቶ በፊቱ አቆማቸው። ዓይኖቻቸውን እያየ ያለቅስ ጀመር። እርሱም አባታችን ከእኛ እንዴት ትለያለህ እንዴትስ ከእኛ ትገባለህ? እያሉ አለቀሱ። እግዚአብሔር ይባርካችሁ ብሎ ባረካቸው መረቃቸው። ሴትንም ልጄ ፈጣሪህን እንዳታስቀይም አውቅ ታሕል በእግዚአብሔር ዘንድ የተናቀ ነውና አንተ ከርሱ ልጆችህ ከልጆቹ እንዳትተባበሩ ተጠንቀቅ አላ ግን ምድር በንፍር ውኃ ትጠፋ ዘንድ አላትና ሥጋዬን በቤተመቅደስ አስተምጠው ብሎት በ930 ዓመት ዓርብ በጠዋት ሰዓት ዐረፈ። ዘፍ5:5

ሥጋውንም መላእክት እያዩአቸው ሼቱ ቀብተው ገነዘው ዕጣን ወርቅ ከርቤውን አድርገው በቤተመቅደስ አኖሩውታል። በጥፋት

ወኃ ጊዜም ኖኅ ከመርከብ ይዞት ገብቷል። ሲሞትም ይዞት ወጥቶ ለሴም ሰጠው። ሴምም ከዛም ወገን የተወለደ መልከጼዴቅን ከመንፈቅ አስፍቶ በማዕከለ ምድር ቀራንዮ አስመልቶታል። ጌታም በቀራንዮ መሰቀሉ ትሑ ስለዚህ ነው።
• የአዳም መዋዕለ ሕይወት ከ5500 - 4570 ዓ.ዓ ነው።

[illegible]

ማቴ 3:2 ሉቃ 13:30 ? 15: 11

ሉ· ቀዳማይ ትንቢት (ሊደምን)

ቀዳማይ ትንቢት የተባለ ዕለት ርዕስ ቀንም ነው። ስለዚህም በቤተክርስቲያን እለት እለት ድረስ ያለውን ጊዜ ዘመን ትንቢት ብለ የመሠረቱ ሊሆን በተለይ ከትንቢት ጀምር እለት ለምንተኛው ቀን እሑድ ድረስ ያሉትን ዕለታት ለዩ ለዩም ስያሜ እንደ እንድ ዕለተ ያስጠራቸዋል።

የሰሎታው ለምሳ እንደሚከተለው ነው

ዕፃ - አብርሃም

ማዕዶት - አልዓዛር

ዋሜሉ - አዳም

ዓርብ -

ቅዳሜ - እንስት

እሑድ - ሊደምን (ቀዳማይ ትንቢት)

ተባርኮ ዘአርከኪ ጹርኒ ተራኸ ደረሰ እዘዴኝ አላት። አዘለችው። ከእክፋ ተዋሕዶ እያከለፈለፈ ወሰዳት።

አዳም መላእክት አሊፋት አስተምረውት ነበርና ሲጸልይ አገኘው። ቀርቦ በሐሰ እ አዳም ንጉሠ ሰማያት ወምድር - የሰማያትና የምድር ንጉሥ ሰላም ላንተ ይሁን ብሎ ሰላምታ አቀረበ። እርሱ ግን ፍለጥ እርዊምድር የምድር እንጂ የሰማይ ንጉሥ አይደለሁም ወግድ አለ። ወደ ሔዋን ቢሄድ ሥራ ፈትታ እግሯን ዘርግታ አገኛት። ድል እንደሚነሳት አወቀ። ቀርቦም በሐሲ እ ሔዋን ንግሥተ ሰማያት ወምድር አላት። ለካስ የሰማያትም ንግሥት ነኝ ብላ ደስ አላት። በእንተ ምንት ይቤለክሙ እግዚአብሔር ኢትብልዑ እምኩሉ ዕፀው ዘውስተ ገነት ካሉ እንጨቶች ሁሉ እንዳትበሉ እግዚአብሔር ያዘዛችሁ ለምንድር ነው? አላት ያዘነ የተቆረቆረ መስሎ። ኧረ ዕፀበለስንም አትበሉ ያለን ሞትን እንዳንሞት ነው አለች። ሰእመ በላዕከሙ እምኔሁ ሞተ ትመውቱ እንዲል ዘፍ 3:3 አኮ ሞተ ዘትመውቱ አላ አምላክ ትከውኑ - አምላክ ትሆናላችሁ እንጂ አትሞቱም ወበልቶ የእምር እግዚአብሔር ከመ ሶበበላዕክሙ እምኔሃ ይትከሠታ አዕይንቲክሙ ወትከውኑ ከመአምላክ ፋሩ ግን ከርሷ በበላችሁ ጊዜ አይኖቻችሁ እንዲገለጡ እንደ አምላክም እንድትሆኑ እግዚአብሔር ያውቃል ለዚህ ነው አላት። ወሕፍተኖ ከመትብላዕ አምወእቱ ዕፀ ይላል አስተመጃት። በልታ አዳምን አበላቸው። እስከዚህ ጊዜ ድረስ ልብሰ ብርሃን ተጎናጽፈው ሳይተፋፈሩ ይኖሩ ነበረ። በዚህ ጊዜ ግን ጸጋቸውን ተገፈፉ፤ ተፋፍረው በበለስ ቅጠል ሥጋቸውን ይሸፍኑ ጀመር። እባብ ከአራዊት ሁሉ የተረገመ በሆዱ የሚሳብ አፈር የሚመገብ የሰው ልጅ ራሱ ራሱን የሚቀጠቅጠው እንዲሆን ፈረደበት። አዳምና ሔዋንንም በሞተ ሥጋ ሞተ ነፍስ በርደተ መቃብር ርደተ ገሃነም ፈርዶ ከገነት አስወጥቶ በደብር ቅዱስ አኖራቸው። ተመልሰውም እንዳይገቡ "ወአዘዘ ለኪሩቤል ወሱራፌል ዘውስተ እሳቸውም ሰይፈ እሳት እንተ ትትመያየጥ ከመይዕቀቡ ፍኖተ ዕፀ ሕይወት"(ዘፍ 3:24) ይላል። ሰይፈ እሳት የያዙ ኪሩቤል እንዲጠብቋት አድርጓል።

ከዕለታት አንድ ቀን አዳም እግዚአብሔርን ያህል ጌታ ከገነት ያህል ቦታ ባገኘ ምክንያት እጣሁ ብሎ ሔዋንን ፊት ነሳት፤ ደንግጣ ሸሸች። ቅዱስ ገብርኤል መተተስምን አበረርጓት? በርሷ ምክንያት እግዚአብሔር ጌታዬን ገነት በታዬን አጣሁ አለ። በርሷ ምክንያት

ዘታጣም መታረቂያህ እርሷ ናትና ታረቃት አለው። እርሱ ግን ኢትክዕኒ ናዛቲ - በፍፁም መታረቂያዬ አትሆኝም ብሎ አይታረቃት ቀረ። ከዚህ በኋላ በጸሎት ጊዜ ሲጸልይ መልአኩ አዳም የተማኝን ጸሎት እግዚአብሔር አይሰማም ምን ያረግልሀል አለው። እሱ ታርቆ አምጥቷታል።

ሔዋን ከጌታ መታረቅ ሽታ አዳም እግዚአብሔር ማረን ብንለው ይምረናልና ሰባኤ ይዘን እንስምነው አለችው። እርሱም አንቺ እያልሽ ምን ይሆናል አለ። ከእንግዲህ ከፊታድህ አልወጣም አለች። ከዚህ በኋላ "ምትዋዎን (ምጽዋዕን) ለአንበት ለሚሕቲቶን" የምትል ጸሎት እንድትሠራ አውቀው እጅግም ሳይራራቁ እጅግም ሳይቀራረቡ ለየብቻቸው ሆነው ከባሕር ገብተው ይጸልዩ ጀመሩ። በመላ አምስተኛ ቀን ዲያብሎስ እንግዲህም ሊታረቁብኝ አይደለምን ብሎ መልአክ ብርሃናዊ መስሎ አዳም ጌታ ምሬሀለሁና ውጣ ብሎሃል አለው። አንተ ማነህ? አለው መልአክ ብርሃን ገብርኤል ነኝ አለው። እርሱም ከዚህ በፊት የፍጡር ቃል ሰምቼ ተጉድቻለሁና አልወጣም አለ። ወደ ሔዋን ሄዶ አንቺ ሔዋን ባልሽ አዳም ቀድሞ አትወጣ ያለውን በልቶ ሊሰግድ ታርቂሀለሁ ውጣ ቢለው አልወጣም አለ እኔ ምን ገዶኝ ለራሱ ይብሰው እንጂ አላት። አንተ ማነህ? አለችው። መልአክ ብርሃን ገብርኤል ነኝ አላት ወጥታ ሄዳ አዳም ጌታ እንኳ በ35 ቀን በ1 ቀንስ ይምር የለምን ውጡ ካለንማ እንውጣ እንጂ አለችው። እርሱ ግን አይሆንም የፍጡር ቃል ሰምቼ አልወጣም አለ። እኔስ እኔ ስለሱ ብዬ ወጥታ ሄደች። መልአኩ እትለያት ብሎት ነበርና እርሱም ወጥቶ ተከትላት ከእግሬ ገነት ሲደርሱ ሰይጣን እኔ ማንኝ አውቃችሁኝ? አላቸው መልአክ ብርሃን ገብርኤል ነኝ አላልሁምን? አለው። ምን ገብርኤል ነኝ ባላጋራችሁ ነኝ እንጂ ብሎ ገሠሠ ሙሉን ቢያሳያቸው ደንግጠው ወደቁ። በምስተኛው ቀን ቅዱስ ገብርኤል አስቀመጣቸው ሲሄዱም ምግቡን እንዲመስሉት በገነት ያሉ አዕዋፍን አዞለት ሂዷል።

አዕዋፍም በእፋቸው በእግራቸው አንድ አንድ ሁለት ሁለት ዘላ የወሰዱ 12 ዋሻ ሞሉለት። ከአዕዋፍም አብርል አዝርል የሚባሉ አዳም በገነት ሳለ ቋንቋቸውን ለምዶ ነበርና እንዲድ ሲባቡ ብሶቱ ተመልሶት ፍሬ ስንቁን ይዞ እየርጠ ተከትሏቸው እሎላ ከእግረ ገነት ደረሰ። ዳሩ ግን ገነት በእሳት ተቀጽራ ነበርና እነሱ ላይ ላዩን ሄደው ሲገቡ እርሱ መግቢያ አጥቶ ከዚያው ቆሞ ቀረ። ዲያብሎስ

በዚህ ዕለት የሚደረሰው ምስጋና ከዕለተ ትንሣኤ ምስጋና ጋር አንድ ዓይነት ነው። ታሪኩም - ጌታ የተነሣ ዕለት ደቀመዛሙርቱን ከዝግ ቤት ገብቶ ሰላም ለኩሙ ብሏቸው ጊዜ ከአሥራ አንዱ ሐዋርያት አንዱ ቶማስ የተባለው ዲዲሞስ ከነርሱ ጋር አልነበረም። ሲመጣ ርእየነሁ ለእግዚእነ ጌታን አየነው አሉት። ሉሩ ወመሁሩ እንደሚላቸው ያውቃልና እኔስ እጄን ብላው ሲያስተምሩ እኔ በግሆ ሊለ ነውን ብሎ እመኔርእኩ እደዊሁ ወእኔሬ ገቦ ቀኖተ በችንካር የተቸነከሩ እጆቹን እግሮቹን ካላየሁ - ወእመ ኢወሰይኩ አፃብዕየ ውስተ ትንፋኑ ወኢገሠሥኩ በችንካር የተቸነከሩ እጆቹን እግሮቹን በጦር የተወጋ ጎኑን ካልዳሰስኩ አላምንም አለ።

ወእምድኅረ ስሙን መዋዕል ይላል በስምንተኛው ቀን ቶማስ ባለበት በዝግ ቤት ገብቶ ሰላም ለኩሙ አላቸው። ቶማስ ጎኑን ካልዳሰስኩ ብሎ ነበርና ሁን እጁን ወእዴከ ወስት ገቦየ ወግሥሥ እጅህን አምጣና ወደጎኔ አግብተህ ዳስሰው ናፍቆ አላ እመን እመን እንጂ አትጠራጠር አለው። ቢዳስሰው ከእሳት እንደገባ ጅማት ከምትርትር አለ፤ እግዚእየ ወአምላኪየ ጌታዬ አምላኬ ሆይ አለ። እስመ ርኢከኒ አመንከኒ ብፁዓን እለ እንበለ ይርእዩኒ የአምኑ - ንዑዳን ክቡራን ሳያዩኝ የሚያምኑብኝ ናቸው ብሎ ፈወሰታል። ይህች ጎኑን የዳሰሰች እጅ ዛሬም ሕያዊት ሆና በሕንድ አገር ከታቦቱ ጋራ ትኖራለች። በዓመት በእመቤታችን በዓል (በአስተርእዮ) ሊያተ ሲገቡ ቀድሳ ታቆርባለች፤ የሚሾመውን ወጥታ ቀኝ እጁን ትይዘዋለች። እንዲሁ እያለች እስከምጽአት ድረስ ትኖራለች። ትር፡ ወን

ሰ. ማርያም ግብጻዊት

ሀገሯ እስክንድርያ ነው። አባት እናቷ ሲያርፉ በደግነታቸው ይቀና የነበረ ሰይጣን እርሷን ፍቅረ ዝሙት አሳደረባት። 27 ዓመት በሴት አዳሪነት ኖረች። ጌታ ሊያድናት ቢወድ ማስተዋልን ሰጣት። አንድ ቀን ቅዱሳን መካናትን እጅ ሊነሱ የሚሄዱ መንገደኞች አገኘች ተከተለቻቸው። መርከብ ሲሳፈሩ እርሷ ገንዘብ አልነበራትምና ሥጋዋን ፈቅዳለት ተሳፍራ ተሻገረች።

ኢየሩሳሌም ከመድረሷ እግዚአ ምሕረትን ሊገቡ እርሷ መግባት ተሳናት። ከስዕለ ማርያም ሥር ወድቃ በታላቅ ቃዲታ እመቤታችን ዋስ ሆናት ገብታ ተሳለመች። ደስ ብሏት እመቤቴ በሥጋ እንደተዋረድኩ በነፍስም ዋስ ሁኚኝ እድን ዘንድ የማደርገውን አሳታውቂኝ ብላ ተማጸነች እመቤታችንም በበኣት አድሪ ከበቀ ተሰደርክ ወደ ዮርዳኖስ ገዳም ኑሪ አለቻት።

ከመንገድ ወጥታ ስመ እግዚአብሔር ጠርታ ጥቂት ጣንቲም አገኘች፤ ሁለት ኅብስት ገዝታ ያን ይዛ ዮርዳኖስን ተሻግራ የሰው ድምፅ ከማይሰማበት በረሀ ገብታ 47 ዓመት ኖረች። የያዘቻው ሁለት ኅብስት ምን በልታ ትኖር ነበር? ቢሉ በበረሀ ምን ይገኛል እንደበግ ሣር ነጭታ ውኃ ተጎንጭታ ትኖር ነበር።

ከዚህ በኋላ ዞሲማስ የተባለ መነኩሴ እመቤታችን አነሳስታ ልካው ቢሄድ ከሩቅ አያት። ዕርቃኗን ነበረችና ተነሥታ ሮጠች። እሱም በረከት ቀረብኝ ብሎ ተከትሏት ሮጠ። ጥቂት ከተሯሯጡ በኋላ መለስ ብላ አ ዞሲማስ ለአመፈቀድከ ከመ ትትናገር ምስሌየ ወግር ሊተ ጸርቀ ዘእትከደን በቱ እስመ አነ ዕርቃት - ከኔ ጋር ልትነጋገር ከወደድህ ዕርቃኔን ነኝና የምለብሰው ጨርቅ ጣልልኝ አለችው። መደረቢያውን ጣለላት። ያን ለብሳ መጥታ እጅ ተነሣሱ። ከዚህ በኋላ ታሪኳን ነግራ በዓመት ሥጋውን ደሙን አምጥተ እንዲያቀብላት ተማጽና ተሰናበተችው።

በዓመቱም ሥጋውን ደሙን አምጥቶ አቀበላት። የዛሬ ዓመት በዚህ ጊዜ መጥተህ ጠይቀኝ አለችው። ቢሄድ ዐርፋ ሥጋዋን አንበሳ ሲጠብቀው በራሷም እ ዞሲማስ ቅበራ ለማርያም - ቅበራት የሚል ተጽፎ አገኘ። እሱ ሥጋዋን ሲገንዝ አንበሳ መቃብሯን ቆፍሮለት ቀብሯ ተመልሷል። "[illegible] ... [illegible] አንበሳ [illegible]።" እንዲል ይሬድ።

• የገበረችው በ5ኛው ም.ዓ ድኅረ ልደተ ክርስቶስ ነው የቤ/ክ መዝ. ቃ አማርኛ

[illegible]

• "ንስሐሰ ትሬሰዮ ለዘአበሰ ከመ ዘኢአበሰ፤ ወለዘማዊ ከመ ድንግል"
"ንስሐ የበደለውን ያልበደለ፤ አመንዝራውንም እንደ ድንግል ታደርጋለች"
አረጋዊ መንፈሳዊ ድር 26 እና 29

ሚያዝያ 7 - ዕረፍቱ ለኢያቄም ጻድቅ

የናኪር! ሳዶቅ ተብሎም ይጠራል።

ትውልዱ ከነገደ ይሁዳ ከቤተ ዳዊት ነው። አባቱ ቅስራ ይባላል። ከነገደሌዊ ወገን የሆነች ሐናን አግብቶ በይሁዳ ከተማ ይኖር ነበር። ነገር ግን ሐና ፅንተ ማኅፀን ሆና ልጅ አጥቶ ብዙ ዘመን ሲያዝን ኖሯል። ኋላ ግን ጌታ ጉዟን አይቶ ጸሎቱን ሰምቶ ልምላሜ መቶት ከተሰየመ በኋላ በበሰራት መልአክ እመቤታችንን ሰጥቶታል። እመቤታችንም በተወለደች ጊዜ ታድሶ እንደ መዓ ዓመት ኑሮባዓ ሆኖ እጅግ ደክሞ ሳይሰማው ኖሮ በዚህ ዕለት ዐርፏል። ያረፈውም እመቤታችን ገና በቤተመቅደስ ሳለች ነው። ነገ ግር

[illegible]

ሉቃ 18:7 ሉቃ 21:36

ሚያዝያ 15 ፀዓተ ነፍሱ ለዮሐንስ መጥምቅ

ዜና ዕረፍቱ በክፍል 1 ገጽ 15 እንደተገለፀው ንጉሥ ሄሮድስ ኢይከውንከ ታወስበ ብእሲተ እኁከ ሬልለ ብሎ ቢገሥፀው ዐቢይ እስመትቶታል እንተቀም ከንፍ አብቅላ ኦ ሄሮድስ አይኮውንከ ታወስበ ብእሲተ እኁከ ሬልለ ብለው ቢሉ ሄዳለች። ... ጋር ... ባለቤት ፀንቶት እስተምሬ አላት። 15 ዓመት እስተምሬ ... ዕለት ዐርፋለች። • ያረፈችው 945 ዓ.ም ነው።

ሚያዝያ 23 - ዕረፍቱ ለቅዱስ ማር ጊዮርጊስ ሊቀ ሰማዕት

[illegible]

[illegible]

[illegible]



[illegible]

ማቴ 10 : 39 ራእ 2 : 10

አላቸው። ይህስ አይሁን ባይሆን ከገደሉኝ ወይም ብላችሁ እናምናለን አሉ። ከከተማ አውጥቶ በወር ወግቶ ገደሉው። ይህን አይተው ወእግዚአብሔር ስም አምነው ተጠምቀዋል። አምራውን ከገደሉብትና ከመሀል ከተማ ሁሉት አብያተክርስቲያን ሠርተዋል።

በዚህ ጊዜ የፋርሱ ንጉሥ ዱድያኖስ ሰባ ነገሥታት ሰብስቦ ሰባ ጣዖታት አቁሞ ይሰግድ ያሰግድ ነበረ። የአባቱን ምስፍና ተቀብሎ ልምግ ብሎ እጅ መንሻ ይዞ ብላቴኖቹ አስከትሎ ቢሄድ ሃይማኖታቸውን ካዱ ለጣዖት ስገዱ ብሎ አውጆ ሕዝቡም ለጣዖት ሲሰግዱ አገኘ።

ለአምላኩተ እግዚአብሔር ቀናዒ ነውና አዘነ። ወርቅ ብሩን ለነዳያን መጽውቶ ብላቴኖቹን አሰናብቶ ነገሥታቱ ከተሰበሰበበት ገብቶ እኔ ወልቱ ክርስቲያናዊ ወእእምን በእግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ እለ። ዱድያኖስ ሦስት ዓመት ሙሉ ሃይማኖታችሁን ካዱ ለጣኦት ስገዱ ልል እንዲህ ያለኝ አንድ እንኳ የለም። ለመሆኑ የማን ልጅ ነህ? ሀገርህስ ዴት ነው? አለው። ከኔ ጋር ምን ኀብረት አለህና አባቴን ሀገሬን ትጠይቀኛለህ? አለው። ሌሎች ያወቁት ነበርና የዮርንቶስ መስፍን ልጅ ነው አሉት። አንተማ የእኛ ነህ በ10 አውራር ላይ እሾምሃለሁ የኔን አምላክ አክብረን አምልክ አለው። ሸመት ሸልማትህ ላንተ ይሁን እኔ አምላኬ ኢየሱስ ክርስቶስን እልክደም አለ። ተቆጥቶ በእንጨት አስቅሎ ሥጋውን በመቃን አስተፋተፈው። ረጃጅም ችንካሮች ያሉበት የብረት ጫማ አጫምቶ ሂድ አለው። ችንካሮቹ አገሮቹን በስተው ወጡ ደሙ እንደ ውኃ ፈሰሰ። አጥንቱ ደቀቀ። መሄድ አቅቶት አንገብሶ ሄዷል። "ሰዓም ለመከዎድክ ወእግዝእ ሐዲን ዘተቀድሩ! እስከሠርክ ድቡተ ሰብ በእንክ ሰገሬ" እንዲል። መከራው በዚህብት እ እግዚእየ ኢትግድፋ ለፍስየ እስከ አስተገፍር ለዝንቱ ልሉ ይህን ከሁሉ አስከስፍረው ድረስ ነፍሱን አትውሰድ ብሎ ወደጊታ አመለከተ። ቅዱስ ሚካኤልን ልኮ ፈወሰታል። ሂድ ንገር አ ልለው አለው። ወሰ ችንካር አስቸንከር ዉላት አስተክሎ እናቱን በመዶሻ እስቀጥቅጦ በሆዱ ላይ የደንጊያ ምሰሶ አሳስሮ እንዲያንከባልሉት አደረገ። የግዶሞት ሆነ ሥጋውን በመጋዝ አስተለትሎ ጨው ነስንሰበት! ሥጋው ተቆራርጦ ወደቀ። ከዛፍ ቤት ትተውት ሄዱ። በመንፈቀ ሌሊት ጌታ በእጁ ዳሰ አስነስቶ ገና ስድስት ዓመት ስለ ስሜ ትጋደላለህ ሦስት ጊዜ ትሞታለህ። በአራተኛው ታርፋለህ አለው።

ሲነጋ ከንጉሥ ሄዶ አንተ ከሀዲ እፈር አምላኬ አዳነኝ አለው። በሥራይ የሚያጭንፍልኝ ባገኝ ቢቀን በወርቅ እመላለታለሁ አለ። አትናስዮስ የተባለ መሠርይ መጥቶ ንጉሥ ሺህ ዓመት ንገሥ ጠላትህ ይደምሰስ አለው። በምን እውቀሃለሁ አለው። ላም አስመጥቶ በጆሮዋ ቢያንሾኳሹክባት ከሁለት ሰንጥቃለች። ለጊዜው እርሱንም እንዲሁ የሚያደርግለት መስሎት ደስ

እለው። ሆድ በተብሶ አገጅቶ ቀራርጦ የሚገድል መርዝ ቀምሞ አስጣተ ሰደጣን ደገኛ ሰጠው። ስመእግዚአብሔር ወርቶ ቢጠጣው እንደጠራሪ ደምቀ እንደአበባ አሸብርቆ ተገኝቷል። ወንጻቱ ማረኝ ብሎ ከእግሩ ወደቀ። መመለሱን አይቶ የቀመባትን መሬት በእግሩ ረግጦ ውኃ አፍልቆ ወደጊታ ቢያመለከት ሐዋርያው ቀግስ በእካለ ነፍስ መጥቶ አጥምቆት ተር 23 ቀን እንገቱን ለሰይፍ ሰጥቶ በሰማዕትነት ዐርፏል።

እሱን ግን በመንኰራኩር አስፈጭቶ ከንፈት ትድጓድ ጥሉት ደንጊያ አትሞበት ተመለሰ። ጌታ የተፈጨ ሥጋውን በእጁ ዳሰ መንፈሱን መልሶ እንሥቶታል። እግሬ መንገዱን እሕዛብን እያስተማረ ከንጉሥ ቀረበ። አንተ መስዋት አፈር አምላኬ ከሞት አነሳኝ አለው። ተበሳጭቶ በብረት አልጋ አስተኛ ከበታቹ እሳት እንድያነድበት አደረገ። እሳቱም ደመ ቢነጥበበት እሳቱም ድርገም ብሎ ጠፍቷል።

ከዚህ በኋላ ክርስቶስ አምላክ ነው ትላለህ ምን አድርጎ ታሳየናለህ? አሉት። የሉመሰዎትን ዕፀው አድርቆ የደረቁትን አለምልሞ! ከሞቱ 430 ዘመን የሆናቸው ሙታንን አሥንቶ አሳይቷቸዋል። በረሀብ በጽም ይመታ ብሎ የሚላክ የሚቀመስ ከሌላት ደሃ መበለት ቤት እንዲታሰር አዘዘ። ከምሰሶው ጋር አሠሩት። ረሀኝ አብሬኝ አላት። የምትሰጠው ብታጣ ወደደጅ ወጣች። ስትመለስ የታሰረበት መሰሶ ለምልሞ 15 ክንድ ያህል ከጣሪው አለፈ! ከልባ እንጀራ የተመላ መሶብ ተቀምጦ እንሉ ዘይቱ በየዕቃው መልቶ አገኘች። ናሁ አምላክ ገሊላውያን ተመሊሉ ሰብእ ወረደ እምሰማይ ወቦአ ውስተ ቤትየ የገሊላውያን አምላክ ሰው መስሎ ከሰማይ ወርዶ ከቤቱ ገብቷል። አለች። አገለጋይ እንጂ እርሱን እይደለሁም አላት። ጆሮው የማይሰማ ዓይኑ የማያይ እግሩ የማይናገር ሐንካስ ልጅ ነበራት። ስው እንዲያየው ሸሽጋ ታኖረው ነበር። አምጣያ ዊትን ብታስነካው ዓይኑ ሸርቶለታል። ጌታዬ ጆሮውንም እፉንም እግሩንም ፈውሰው አለችው። ይህ ጊዜው ገና ነው አላት። እርሱንም ቅዱስ ሚካኤል ክእሰር ፈቶት መበለቷን ከአልጂ አጥምቶ እያስተማረ ወደንጉሥ ተመለሰ።

ንጉሥ ዱድያኖስ የሚያደርገው ጠፋው። በመንኰራኩር ፈጭታችሁ ደብረ ይድረሰ ወስዳችሁ ንፉት አለ። ፈጭተው ወስደው ቢነፉት ሥጋው ያረፈበት ግር ቅጠሉ ደንጊያው እንጨቱ ሁሉ ጊዮርጊስ ቅዱስ ሰእግዚአብሔር እያሉ አመስግነዋል። ጌታም ያስተ ቸ ከሞት አንሥቶታል ጭፍሮቹን ተከትሎ አምላኬ ከሞት አስነሳኝ አላቸው! ደንግጠው ከእግሩ ሥር ወደቁ።መሬቱን ከእግሩ መትቶ ውኃ አመንጭቶ ቅዱስ ዮሐንስ አጥምቋቸዋል።

ከዚህ በኋላ ንጉሥ ልሽምሁ ልሸልምሁ ለእዩሱን ስገድ አለው። ከሾምከኝና ልሽልምከኝ ልላ ምን እሻለሁ እሺ እሰግዳለሁ አለ። እንኪያስ እስከዛሬ ባስከፋሁህ ይቅር

ሚያዝያ - 27 ዕረፍቱ ለፊቅጦር ሰማዕት

ሀገሩ አንጾኪያ ነው። አባቱ ጉርማኖስ እናቱ ማርታ ይባላሉ። የቅዱስ ፋሲለደስ የእህት ልጅ ነው። ንጉሥ ኑማርያኖስ ተንባላትን ሊወጋ ሲዘምት እርሱም አብሮ ዘምቷል። በመርነቱ ንጉሥ ሞተ። ፊቅጦር በተሰለሊበት ጠላት ድል ነሥቶ ድንበር አስፍቶ ወደከተማ ቢመለስ የንጉሡ ሬረስ አትራቢ የበረ አገሪልል (ዲዮቅልጥያኖስ) የንጉሥን ሴት ልጅ አግብቶ መንግሥት ወርሶ አገኘ። በዚህ አገሬ ከፋም በጣም ሳይገናኙ ብዙ ጊዜ ተቀመጡ። ኋላ ግን ዲዮቅልጥያኖስ አብያተ ጣዖታት ይትራዋም ወአብያተ ክርስቲያናት ይትዐፀዋ ብሎ ሃይማኖት ሲያስክድ ለጣዖት ሲያሰግድ የወንድሞቹን መንግሥት መንጠቁ እንሱት ደገም እንዲሁ ይለናለን ብሎ ሊማለው ሰይፍ መዞ ቢሄድበት ሸሽቶ ወደሟጀት ገባ። እርሱንም ቅዱስ ፋሲለደስ ስለ ክርስቶስ ሌንሞት እንጂ ሌንድል አይገባም ተው አለው። ንጉሥም በአማላጅ በአዓላጅ ታረቀው።

እሱም እኛ ከምድሞት እንደበቀ ከዚሉት ሳይለይ ሲኖር ቀምድያኖ ከሁሉት ልጆቹ ጋር ክርስቶስን አልክድም ለጣዖትም አልሰግድም ብሎ በሰማዕትነት ሞተ። ንጉሥ ቀብር ከአከሉበት ሥጋዎ ከአደባይ ወድቆ ዋል አደረ ይህ ፊቅጦር ከወደቱበት አንሥቶ ቀብሬቸው። መሳፍንቱ በዚህ ምክንያት ከንጉሥ አማሉት። ወርቅ ምላው እንዲህ አደረገህ አለው የወደቀን ማንሳት የሞተን መቅበር ምን ተፋት አለው ይልቁንስ አንተ አስከመቼ እንዲህ ስትል ትኖራለህ? አለው። ወገኖቹን ፈርቶ በድብቅ ለቀን እንደፈረስ አስበቀም ወደ እስክንድርያ አጋዘው። ሹሙ ሀርሚኖስ ፊቅን አስከሰት ድረስ አስገረፈው። ሥጋዩ ቢፈርስ ወደእ ጌታ ያጋጀለትን መካ ፅ ረፍት አለው። ጌታ እንጂ ሎጥቶት ሀገር ብዙ ከስር በአንድ ምት የዘለዓም ሕይወት ይሰጣል ብሎ በተቀበት የሚጋደል ሆነ። ያም በደንጊያ እየተገር በአሳት አስተከሎ የግደሞትበት ዝሆን ወደ እንዲናው ላኩው። ቢያጤናት ተሬትቶ ቢጋድለት ተነሥቶ ያገኙታል። በችንካር ቸንከረው ሰቅለው ተዉት። ይህን ታይ የዐረች የ15 ዓመት ብላቴና እለይ እለይ እለል እለል አለች። ምነው ሰዋት ሰው ዋይ ዋይ ይባለለታል እንጂ እለል ይባላልን አሏት። መላእክት ሰማያዊ አክሊል ሲያቀዳጁት አየሁ አለች። እንግዲህማ ብዙዎችን ሊያሳገበን አይደለምን ብለው በሰይፍ መትተውታል።

• በዛሬም. ዓድ-ኢ-ሎ መጃመሪያ ላይ ነው

ፊቅጦር ምዕመኑ ለአምላክ ክርስቶስ ተወለደ ሕግም እርሱ ጊዮርጊስ ከታላቅ ጋራ ከሚረር ተዋሊ መሞትን መረጠ ስለድድቅ ተሰለ። እንደፈረሰ በልብል በለንም አቶን በአምነቱ ጽናት መሰከረልን የሊያስስ ክርስቶስ አምላኩስነን። አመሻችቶ በጥቀ ለችንካር እጆቹን አበዐ አለቀስ የሌታ ሥታዩን ሰለሰው ልጅ ብሎ የተቀበለውን። ሞቱ ለደረት ሰው ነውና ሕይወት መላእክት ዘመሩ ሻድታን ተደሰቱ እለል እለል አለች ሕጻም ከፊቱ

ሚያዝያ 30 - ዕረፍቱ ለማርቆስ ወንጌላዊ

ማርቆስ ማለት ንህብ! አንበሳ! ከሆነ ማለት ነው። ንህብ የተባለ ንህብ ሁሉን እንደተቀሰም እርሱም አስቀድሞ ከጌታ ኋላም ከሐዋርያት ሰለተማረ ነው። አንበሳም የተባለ አንበሳ ዓሁምን እንደሚሰብር እርሱም በአምሳለ ዓሁም በአምሳለ ጣዖት ተሠርተው ሲመለኩ ነበሩ የግብጽን ጣዖታት አዋፍቷልና ነው። ካህን የተባለም ወእምጽኡ ማሬ ዘድዮስ ባለው ሄዶ ነው። ሐዋ 14፡13 ቀዳሚ ስሙ ዮሐንስ ነው። ሐዋ 12፡12 ቀተፋም ከ72ቱ አርድዕት ነው። አባቱ አርስጦቡሎስ እናቱ ማርያም ይባላሉ። ይህች ማርያም ሉጊታ ያመነች ወንጌልን የተቀበለች ጌታም ካረገ በኋላ ቤቷን ለሐዋርያት በተጸሎት እድርጋ የሰጠች እነርሱንም በተሐልኩ ያገለገለች ከ36ቱ ቅዱሳት አንስት አንዷ ናት። ሐዋ 12፡12

ጌታ ካረገ በኋላ ሐዋርያትን እየተከተለ ይማር ያገለግል ነበር። በርናባስንና ጳውሎስን ተከትሎ አንጾኪያ ወርዶ አስተምሯል። ሐዋ 12፡25

ከዚያ በኋላ ቅዱስ ጴጥሮስን ተከትሎ ሮም ወረደ። ቅዱስ ጴጥሮስም ከፍሎምንት መድረሱን አውቆ ጽጽስና ሾሞ ከሀገረ ሰብከቱ ግብጽን ከፍሎ አስተምር ብሎ ሠጠው። እሱም ወደ ግብጽ ሲሄድ ከከተማው በር ሲደርስ የጫማው ጠፈር ተበጠሰበት። እንያኖስ የሚባል ጫማ ሰፊ አግኝቶ ሰፋልኝ ብሎ ሠጠው። ሲሰፋ እጁን ወግቶት አሀ ታአስ ብሎ ጮኸ አሐዱ እግዚአብሔር ማለት ነው። የጠራኸውን ታውቀዋለህ አለው። ሌሉ ሰምቼ እንጂ ያስተማረኝ የለም አለው። ፈታዴን አይቶ አስተማረው። ከነቤተሰቡና ከጎረቤቶቹ አምኖ ተጠምቀዋል።

"የሀገሩን ሰርዶ በሀገሩ በሬ" እንዲሉ አንያኖስን ጳጳስ ቀኖት አድርጎ ያስተምር ጀመር። ሕዝቡም ትምህርቱን ሰምተው ተአምራቱን አይተው አመኑ ተጠመቁ። ካመኑም ዘንድ ጣዖታቱን አፈራርሰው አብያተ ክርስቲያናት ሠርተዋል።

ከወተ ማየቱ በጠላትነት ተነሱበት። ምዕመናን አባታችን ልናጣህ አንችልም ቀጣቸው እስኪበርድ ወደሌላ ሄደህ ቆይ አሉት። እረኛ የሌለው መንጋ እንዲደሆነ እንያኖስን ኤጲስቆጶስ ሾሞ ቀስ ዲያቆን አድርጎ ሾሞላቸው በበርቃና በእትራብያ ባለ 5 አውራር እየሰበከ ቅዱስ ጴጥሮስን ለመጠየቅ ወደሮም ሄደ። ከዚያ ሆኖ ወንጌሉን በላቲን ሮማይስጥ ጽፎታል። ዘመኑም በአብነት መጻሕፍቶቻችን ጌታ ካረገ 11ኛ ሲሊፍ 12ኛ ሲጀመር ቀላውዴዎስ ቄሳር በነገሠ በ4ኛ ዓመት (45-46 ዓ.ም) ነው።

ዕመማመ ቃላት ግን በ60 ዓ.ም ተወለዶ ተጽፏል።
ቀዳት ዓመታትን ቆይቶ ቢመለስ ምእመናን በዙሪው አገኘቶ ደስ አለው ገዳሙ የሰለው በኋላ የተሰለው ደሴቱ ቢያይ ደስ እንደሚለው በዓል ትንሣኤን ከዚኣ ጋር ሊያከብር እኒያ ዓመታት መመለሰን ለምተው ሊማሉት መጡ ምእመናንም ለብሶችን ቸቸ አሉት ናዋሪስ ጌር ይባላል ነበሮ በአንተ አሞገሁ ዮሐ 10:11 እንዲል መልካም እረኛ ነፍሱን ስለበጎቹ ይሰጣል የሰማን እዉነትም አሳሽም አለ። እንደ ፋም በአንተ ጉዞድ አስረው በሬዐ ስለሬዐ ቢጎትቱት ሞቱ። ሥጋው በእሾህ ተቆራርጦ። ወደ ጌታ ቢያመለከት ለርሱ ተገለጸ ሥጋዬን እሰጥ ለመናዉን ለምቹ ቀርኖቹ መጣ። ስለ ተቀበለው መከራ ከብርሃን ክ12ቱ ደቀመዛሙርት እንድ አድርጌሃለሁ። በሰማይ የተገለጹትን እምርሐለሁ። ብሎ ቅድሰት ነፍሱን ከሥጋው ለይቶ በክብር እትርገት በሰባልት መላእክት አሳርጓታል። በዚህ ጊዜ የ68 ዓመት እረጋዊ ነበር። በሙት እንደአባቱት መቃብሩን ፍጹሙዶርቀ ቀብረው በነገሥ በ11ኛ ዓመት እንደ መነ ቃለ ግን በ67 ዓ.ም ነው።
እኒያም ሥጋውን እናቃጥለን ብለው እንጨት ሲረበርቡ ዝናብ ሊያርከፈከፍ ቃላት ነጐድጓድ ሆነ ምድር ተናወጸ ልሳይም በርዳን ከበለታቸ ምን መጣብን ብለው ሸሽተዋል ኋላ ግን ምእመናን በርኖ መብራት ተወር አግኝተው ቀብረውታል። [illegible]



ምዕራፍ 3

ግንቦት 1 ልደታ ለማርያም እግዝእትን

እመቤታችን በፈቃደ እምላክ በባበሬተ መልአክ ነሐሴ 7 ቀን ተጸነሰች። በማኅፀንም ሆና ብዙ ተአምራት አድርጋለች። ሁሉቱን ለአብነት ያህል እናያለን።

1 ሐና በርሲባ የምትባል አንድ ዓይና አክስት ነበረቻት ልትጠይቃት መጥታ ሳለ እግዚአብሔር በቸርነት ጎበኘሽ ብላ ማኅፀናን በዳሰሰችበት እጇ የጠፋ ዓይናን ብታሸው በርቶላታል። ሌሎችም እንዲሁ ሆዷን እየዳሰሱ ድነዋል
2 ሐና የምትወደው ሳምናስ የሚባል የአጎቷ ልጅ ሞቶ በቤተሰብ ልማድ የእልቃውን ሸንኮር ይዛ ስታለቅስ ጥላዋ ቢያርፍበት ሙቱ አፈፍ ብሎ ተነስቶ በሳም ለኪ ኦ እምሔውቱ ለዘገብረ ሰማየ ወምድረ ሰማይና ምድርን የፈጠረ የአምላክ እናቱ ሐና ሰላም ላንቺ ይሁን ብሎ መስክሮ ተመልሶ አርፏል።

ከዚህ በኋላ አይሁድ ለምቀኝነት አያርፋምና ቀድሞ ከእኒህ ወገን የሆኑ ዳዊትና ሰሎሞን አርባ አርባ ዘመን ገዙን አሁን ደግሞ እዚህ የወለዱት ሊገዛን ነውን ብሎ በጠላትነት ተነሡ ቅዱስ ገብርኤል እያቄምን ሐቅል ሊባኖስ ይዘሀት ሂድ አለው ይዟት ሄደ። ጊዜዋ ደርሶ ነበርና በዚህ ዕለት ነቢያት ትንቢት የተናገሩላት ምሳሌ የመሰሉላት እያቄም ቴክታ በጥሪቃ በጤሪቃ እምሳል እያቄምና ሐናም በርግብ አምሳል ያዩአት እመቤታችን ተወለደች። በሊባኖስ መወለዷም ሰሎሞን ንጊ እምሊባኖስ መርዓት ንጊ እምሊባኖስ መኃ 4:9 ያለው ይፈጸም ዘንድ ነው።

የተወለደችው በ 16 ዓ.ዓ ነው።

መዝሙር ርጉሩ ድንግል ማርያም
ወልዳ የመሰችን የማሰምን ስም
ለመላእክት አንተ እናት ናት ዓለም።
ከጠርቅ ናትና እምሳል የሌላት
ድንግል ተወለደች በመልአክ ብሥራት።
ድንግል በትወለድ በአምላክ ቃልኪዳን
የሊባኖስ ጋራ ተመላች በብርሃን
ሐሤት አደረጋን በፍሰሐ ደስታ
ምስጋና እቀረብን ለአምላክ በዐልልታ

የድንግል መወለድ ከእያቄም ከሐና
በወጣትነት የኖርን ተስፋችን ነውና።
ዘመድም ባታጣ ወለጅ ቢኖራት
ሐና ምትወልደበት አልተገኘም ቤት።
እንዲገ ቤት በረቱን አላሁድ ነዋዋት
በደብር ተወለደች የአምላክ እናት
አዘቋ ሰሎሞን ቢያይ ትንቢት
ንጊ እምሊባኖስ እንትየ መርዓት
ብሎ እንደዘመረ እንዳወደሳት።

መኃ 4:9

ግንቦት 5 እረፍቱ ለኤርምያስ ነቢይ ከ626 - 515 ዓ.ዓ

ኤርምያስ ማለት እግዚአብሔር የሚያውቀው ኅሩይ እምከርሠ እሙ ማለት ነው። ቀጥሩ ከአራቱ ሀበይት ነቢያት ነው አባቱ ኬልቅያስ ይባላል በዓናቶት የሚኖር ካህን ነበር። ከኢዮስስ ዘመን መንግሥት እስከ ሚጠተ እስራኤል ድረስ አስተምሯል።

ንጉሡ ኢኮንያን ይባላል ሦስት ወር እንደነገሠ ናቡከደነጾር ከፋርስ መጣ እሱን እሥሮ ሕዝቡን ማርኮ ሲሄድ ወንድሙ ናታን ከመንገድ ቆይቶ እኔ ብታነግሠኝ እስራኤልን አስገዛልሁ ነበር ብሎ ሹሞት ለመነ። ስሙን ባትከዳኝ ሲል ሴዴቅያስ ብሎ ከምርኮ በቀሩት ላይ ሹሞት ሄዷል። እርሱም 8 ዓመት ሲገብር ኖሮ ትጽሩን ካበፋ እንባውን ካዳና በኋላ አልገብርም አለ። አስቀድሞ በሞአባውያን መንፈቅ ያህል አስከበበው ኋላም እርሱ ሁለት ዓመት ከበበው። ወደ እግዚአብሄር አመልክትልኝ ብሎ ወደ ኤርምያስ ላከ ከሕዝብህ ጋር ትማረከለህ አለው እንተማ በጉ ተናግረህልኝ አታውቅም ብሎ እጅ እግሩን አሥሮ ከጥልቅ ጉድጓድ አስጣለው። ጌታ ቅዱስ ሚካኤልን ልኮ በአቤሜሌክ አድሮ አውጥቶታል። ኤር 38: 7- 11 እስራኤል ረሀብ የሚጎዳቸው ቢሆን ንጉሣቸውን በምክንያት እናድናለን ብለው እንደ ሞተ ሰው ገንዘው በአልጋ አድርገው ዋይ ዋይ እያሉ ይዘውት ሲወጡ ናቡከደነጾር የሰውን ብዛት አይቶ ምንድር ነው ብሎ ጠየቀ። የእስራኤል ንጉሥ ሞቶ ሊቀብሩት ይወስዱታል አሉት እሱንማ አጥቤ ገንዤ ልቀብረው ይገባኝ ነበር። ያም ባይሆን ልሳመው አምጡት አለ። አስመጥቶ መገነዙን ፈትቶ ቢያየው ቁልጭ ቁልጭ ይላል። ምነው ሳምንህ ከዳኸኝ አሁንስ እንጂ እኔን ከዚህ አስቀምጠህ ወዴት ልትሄድ ነበር አለው ገዝ አለ መሳፍንቱን ፍረዱኝ አላቸው እችላለሁ ብሎ አይዋጋ ወይ አልችልም ብሎ አይገባ ሞት ይገባዋል አሉ ፍርድ አላወቃችሁም ሞቱ ለብእሲ ዕረፍቱ ሞትማ እረፍት ነው ብሎ ሰባት ልጆቹን በሰይፍ አስመትቶ እሱን ሁለት ዓይኑን አውጥቶ በፈረስ ጭራ አስሮ እያስጐተተ ባቢሎን አወረደው ሚን ባቁላ ሲፈጭ ከወፍጮ ስር ልቡ ፈርሶ ሞቷል።

ለኤርምያስ አቤሜሌክና ባሮክ የሚባሉ ምድያማውያን ደቀመዛሙርት ነበሩት ከዚያ በፊት የምርኮን ነገር ሲናገር እየሰሙ ኢታርአዩ መዐተ ወብድወታ ለኢየሩሳሌም የኢየሩሳሌምን ጥፋት አታሳዩኝ እያሉ ያለቅሱ ነበር። ጊዜው ሲደርስ ባሮክን መቃብረ ነገሥት አስጠብቀው አቤሜሌክንም ለድውያን የምንቀባው አጽቀ በለስ አምጣ ብሎ ላከው እርሱ ግን ከሕዝቡ ጋር ተማርኮ ፋርስ ባቢሎን ወርዷል።

አቤሜሌክ በለሱን ቆርጦ በሙዳይ አድርጉ ሲመለስ ከጥላ ስር እረፍ አለ ወዲያውም እንቀላፍቶት ተኛ በተኛ በ66 ዓመቱ ነቅቷል ሲነሣ ጥለው ከተኛበት ጊዜ ጥቂት እልፍ ብሎ ነበርና ዘገይቻለሁ ብሎ ፈጥኖ ሲሄድ ቢሞክር መንገዱ ጠፋው። ቀኖ ሊመለከት መልአኩ በአምሳሉ አረጋዊ ከተራራ ሲወርድ አየ። ሂዶ እይቱ ሀለው ኤርምያስ ወአጋውዮ እነ ኤርምያስ ወዴት አሉ አለው። አንተኑ ነሃ ለኢየሳሌም ለኢየሳሌም እንግዳ ነህን እነ ኤርምያስ ያሉ ባቢሎን በስደት ኢየሩሳሌምም ከጠፋች 66 ዓመት አለው አራት ሽማግሌውን አክብር ብዛኛለች እንጂ ጆጆ ጀጆዋ ብለህ በወደድሁ ነበር ለድውያን የምንቀባው በለስ አምጣ ብሎ ልኮኝ ይኸው ቅጠሏ አልጠወለገም ደግሞ ይንጠፈጠፋል አለው እንተን ከመከራው ሠውሮህ ነው ብሎ በወራቱ አስረድቶ ወስዶ ከባርክ አገናኘው እንተት ለአንንተ ተቃቅፈው ተላቅሰዋል። ኋላም ቀኖና ቢገቡ እስራኤል ከምርኮ ሊመለሱ አራት ዓመት እንደቀራቸው ተገለፀላቸው ይሆን ጽፈው በጽቀበለሱ ጋር ታዞ ቢመጣ ንስር እንገት ላይ አሥረው ላኩለት።

ኤርምያስ ሰው ሞቶበት ሊያስቀብር ሲሄድ ከፈረስ ግንብ አጠገብ አስክሬኑ አሳርፎ ሳለ ንስሩ በሰሙ ጠርቶ ማለለት ነገሩንም እንዲረዳለት ሙቱን በእግሩ ረግጦ እንስቶታል ሙቱም በወረቀቱ የተጻፈውን መሰከር ተመልሶ አርፏል። ጽሁፉም ከምርኮ ለመመለስ አራት ዓመት ቀርቷልና ከሕዝብ የተጋባችሁ ተፋቱ ያላገባችሁ ተጠበቁ የሚል ነበር። ብዙዎቹ እግዚአብሔር የተናገረውን እያስቀር በለው ያገቡ ተፋቱ ያላገቡትም ተጠበቁ። የቀሩት ግን ሚስቶቻችንን እንፈታም ከሀገራችንም አንቀርም አሉ። አራት ዓመት ሲፈጸም ኤርምያስ በፈቃደ እግዚአብሔር እስራኤልን በባበር ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ። እኒያም ከኋላ ከኋላ ተከተሉት። ሁነና አቤሜሌክ ሊቀበሏቸው ወጥተው የእሕዛብን ሴቶች አይተው ምነው እንዲህ አደረጋህ አሉት ሚስቶቻችንን ግን አፋቱን ዘረ-ችንንስ ግን ነሥተን ብለው መጡ ለዓቸው ኃያሉን መርጠው ለዳዋቸዋል። ከዚያም ቢመለሱ ንቃችሁን ጠልታችሁን ሂዱችሁ የለምን ብለው አባረሯቸው። ዮርዳኖስን ሳይሻገሩ ሀገር አቅንተው ተቀመጡ። ምድሪቱንም ሠመርናሃ /ወደድናት/ ሲሉ ሰማርያ ብለዋታል።

ከምርኮ ከተመለሱ በኋላ ኤርምያስ የፈረሰውን ቤተመቅደስ አሠርቶ ንዋያተ ቅድሳቱን አስናድቶ ዳግመኛ እግዚአብሔርን በድለው ይሆን የመሰለ መከራ እንዳያገኛቸው ሲያስተምራቸው ቆይቶ በዚህ ዕለት ሕዝቡን ሰብስቦ የሥጋዌን ነገር ሲናገር የአምላክን ልጅ አምላክን አየሁት ሲሉ ብለው በደንጊያ ወግረው ገድለውታል። ተረ.ኤር 11:54 ዕብ 11 37

ግንቦት 7 ዕረፍቱ ለአትናቴዎስ ሐዋርያዊ

አትናቴዎስ ማለት ሞት ሕልፈት የሌለበት ሕይወት ማለት ነው። ሐዋርያ የተባለው አንድ ቀን ከጴጥሮስና ከጳውሎስ መቃብር ሄዶ ሰላም ለክሙ ብፁዓን ሐዋርያት እያለ ሲጸልይ ለከ ይበሉከ ሐዋርያ አንተንም እንጂ ሐዋርያ ይሉሀል የሚል ጽምጽ ሰለሰማና እንደሐዋርያት መከራ የተቀበለ የተሰደደ በትምህርቱ መናፍቃንን ተከራክሮ የረታ በተግባሩ በድርሰቱ ለቤተክርስቲያን ዓምድ ሰለሆነ ነው።

ሀገሩ ሙሩፍ ነው። አባት እናቱ አረማውያን ነበሩ የአባ እለ እስክንድሮስ ደቀመዝሙር ነው። የአረማዊ ልጅ ከሆነማ እንደምን ደቀመዝሙሩ ሆነ ቢሉ አንድ ቀን እለእስክንድሮስ በመንገድ ሲሄድ ይህ አትናቴዎስ ከሕፃናት ጓደኞቹ ጋር እሱ እንደ ሊቀጳጳስ ሆኖ ጓደኞቹ እንደምእመናን ሆነው አጥምቀን እያሉ እያጠመቃቸው ሲጫወቱ አይቶ ቆሞ ይመለከታቸው ጀመር። ተከታዮቹ አባታችን ከሕፃናት ምን ቆም ነገር ይገኛልና ቆመህ ታያቸዋለህ አሉት እንዲህ መስሏቸሁልን እኒህ ሕፃናት የሚሰሩት ኋላ ጌታ ለአድርጎ የሚሰራውን ነው ይህ ብላቴና አባቱ በሕፃንነቱ ይሞታል እናቱ እምነታ ትሰጠኛለች እኔም ቀጥሎ የሚሾም እሱ ነው አላቸው።

ይኸውም አልቀረ አባቱ በዘመኑ ረሀብ ሞተ እናቱ እንደወደደህ አድርገው ብላ እምነታ ሰጠችው እያስተማረ አሳድጉ ከቢታቸ ሾመው። እርሱ ካለፈ በኋላ በርሱ ቃል በመንበሩ ሾመውታል 20ኛ ሊቀጳጳሳት ነው። ተሹሞም ሳለ ብዙ ተግሣጽ

ጽፋል ብዙ ድርሰት ደርሷል። ከብዙውም እንዱ የቅዳሴ እግዚእ ለውጥ ሆና በሰንበት በክረምትና በደብረታቦር የሚቀደሰው ቅዳሴ ነው ብዙ ሕሙማንን ፈውሷል፣ በለበሰው ልብሱም ሙት አንሥቷል። ከትሁትናውም ብዛት እንገዱ ሲመጣበት እንደ ብላቴና ዝናሩን ነጥቆ ወገቡን ታጥቆ እግር ያጥብ ነው።

ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ ዘየበቢ እርፎ ልጁ ቆስጠንጢኖስ ዘይንእስ ነገሠ። የአርዮስ ወዳጅ የነበረ አውሳብዮስ ሄዶ ንጉሥ ብዙ ስለነበሩ አሰውጥተውት እንጂ ይአርዮስ ሃይማኖት እውነተኛ ነበረች። አለው እሱም ነገሩን ተቀብሎ አትናቴዎስን ከመንበሩ አስወጥቶ ሰደደው 7 ዓመት በስደት ኖሯል። ተሰዶም በብሔረ ዐረብ ሳለ ዐረባውያን እምልክ የሚፈጽሙበት ምክራብ ማየት ነበረ። ቆሞ ሲያየው ቆይቶ ወደ ጌታ ቢያመለክት የሰው እጅ ሳይነካው ፈርሶ የኮረት ክምር ሆኖ ምን መጣብን እያሉ ሲታወኩ ነገሩ ከወደእግዚአብሔር የተደረገ መሆኑን አስረድቶ አሳምኖ አጥምቋቸዋል ቀሳውስት ዲያቆናትንም ሾሞላቸዋል። ስንክሳር

ከሰባት ዓመት በኃላ ቢያከራክሩኝ እከራከራለሁ ቢገድሉኝም እሞታለሁ እንጂ እስከ መቼ በስደት እኖራለሁ ብሎ ከንጉሥ ቀረበ። በግዛ እጁ ይሙት ብሎ አውሳብዮስን በአዲስ መርከብ የምርቶ ምግቡን ቀዛፊውን ስተቶ እሱን ግን ምግብ ቀዛፊ ሳይሰጠው በነቀዘ መርከብ አድርጎ ወደ እስክንድርያ ላካቸው አውሳብዮስ መርከብ ተሰብሮበት ሰጥሞ ቀርቷል። እሱ ግን መላእክት መንፈሳዊ ምግብ እየመገቡት በአዲስ መርከብ አሳፍረው አድርሰውት ወደ መንበሩ ተመልሷል።

ከዚህ በኋላ አርዮሳዊው ቆስጠንጢኖስ ዘይንዕስ ሞቶ ዩልዮስ የተባለ ከሀዲ ነገሠ ሊገድለው ሲያስፈልገው ሸሽቶ ገዳሙ እኮሚያ ገባ መጽሐፉ ግን ሞት ፈርቶ ሰማዕትነት ጠልቶ አይደለም ወሰብ ይሰድዱክሙ እምዛቲ ሀገር ጉዩ ኀበ ካልዕታ ማቴ 10:25 ያለውን አስቦ እርሱም እኔን ገድሉ በኋላ ምክንያት የብዙኃን ደም ፈሰሰ እዳ ፍዳ እንዳይሆንበት ብሎ ነው። እሱም እልቀየም ሞተ ምእመናን አባታችን ጠፋብን ብለው ለአባ እንጦንስ ነገሩ ገዳሙ እኮሚያ አለላችሁ አላቸው በእጀብ አምጥተው ወደ መንበሩ መለሱት ከዚህ በኋላ በሰላም ሲያስተምር ቆይቶ በተሾመ በ47 ዓመቱ በዚህ ዕለት አርፏል:

ሊቀ አትናቴዎስ ደገ ሐዋርያው
ለቤተክርስቲያን የጸና ዓምድ ነው
ርእሰ ሰላሳት ነበር ስሙ ሊቀን
ቀናዒ እገር እሐው የአንገራዊን
ያሰደ ሰራት በዓለ ያስተራሳን
እስኪ ልብ በሉት ትሕትናውን
በመናፍቃን ምክር ቢሰደድ ከገር
ዞር እስተማረ ወገኑን በዐር
ነፍሱን ለሚያረክስ በጸሎቱ ትምህርቱ
ከሕይወት መንገር ወጥተው ሜሔዱቱ
በብዙ ከው እዳች የአምላክ ታቦት
የቦሁ ማንደ አርዮስ ክህደት ዓልመዐቀው
አድቀንን ሊያሸግ ሥጋቸውን ቀርጦ
ኋላም እንዳያውክ ንብረው እቀጥቶ
በምስራር ምሥራቅ አትናቴዎስ ሲለ
ከሥሩ ካለው ገዘው ቀረርጦ
አሉ እንደአባቶቻችን ያሉረገ ትሁትና
ፈለን ማናፈድ ከቀ ያደርጋልና

1ሔዋ 5 6

ግንቦት 8 ዕርገት

የተነገረው ትንቢት የተመሰለው ምሳሌ ይፈጸም ዘንድ ጌታ በተቀበረ በሶስተኛው ቀን በሰንበተ ክርስቲያን መግነዝ ፍቱልኝ መቃብር ክፈቱልኝ ሳይል ሙስና መቃብርን አጥፍቶ ተነሥቷል ተነሥቶም አርባ ቀን ለሐዋርያት መጽሐፈ ኪዳን አስተምሯል። ንባቡ ሥርቶ ያስተማራቸው ሰባት ቀን ነው። በትንሣኤ በእግዚአብሔር ግብርና በጥብርያዶስ ወንዝ ሣልሳ ለእግዚእነ እንዘ ያስተርእዮሙ ለአርዳኢሁ እምድኅረ ተንሥአ እሙታን እንዲል ዮሐ 21: 1 በየቀኑ ግን ለአንዱ ለሁሉቱም ሳይገለጽላቸው አያውልም አያድርም ነበር። በ40ኛው ቀን እንትሙሰ ንበሩ ሀገረ ኢየሩሳሌም እስከ ትለብሱ ኃይለ እምአርያም ከሰማይ ኃይል እስክታገኙ ድረስ በኢየሩሳሌም ቆዩ ብሏቸው እስከ ቢታንያ አውጥቶ እስከ በትርያርክስት ያለውን መንገድ በአንብሮተ እድ ሾሟቸው በርኳል። ሉቃ 24 50

ከእርባ ገቶ ብሎ በ39 ከፍም ብሎ በ41 ያላደረገው በ40 ቀን ያደረገው አዳም በ40 ቀን አግኝቶ ያጣትን ልጅነት እንደመለሰ ለማጠየቅ ነው። ማረጉም ከእመቤታችን በነሣው ሥጋ ነው። ስለምን ቢሉ ተለየ ተለወጠ ባሉት እንዳይመቻቸው አንድም ቅዱሳን ማረጋቸውን ከት መንግሥት በማያት መግቢታቸውን ለማጠየቅ ነው ዐርገ ከመ ያለቡ ዕርገተ ጻድቃን ንጹሐን እንዲል መቅ ወን

ክርስቶስ እየሰለ የከብር መድኃኒት
ከሞት በተነሣ በአርባ ዕለት
መላእክት እጀበው እያመሰገኑት
በደመና ዐረገ በታሳ አብርሃት
ከድንግል ማርያም የነሣውን ሥጋ
ለውሎ ጌታ አረገው አክብሮ በጋ
በእጁ ባርኳቸው ሐዋርያትን
ጌታ ወደ ሰማይ ሲያረግ በሥልጣን

ጠብቁ አላቸው መንፈስ ቅዱስን
ቅዱሳን መላእክት ለርሱ እየሰሙሩ
ጌታ በክብር ሲያርግ ቆመው የክብሩ
ያዩ ሐዋርያት ምንኛ ደስ ብሉ
በሰብቡን ሳንቀር ከሞት ተነስተን
ወደ በማይ መንግሥት ግሬጋችንን
በርሱ የክብር ዕርገት ከሞቀን ተረዳን
እርሱ በርን ለኛ አብቶት ሆነን

1 ተሰ 4 17

ግንቦት 9 ዕረፍታ ለቅድስት ዕሌኒ /ከ 255 328 ዓ.ም/

እየሩሳዊት የሮሓ ሴት ነች። ተርቢኖስ የሚባል ባል ነበራት ነጋዴ ነበርና ለንግድ ሄዶ ሶስት አራት ዓመት ኑሮ ሲመለስ ባልንጀሮቹ ከማዕበል ከጥገድ ድነን እንደወጣን ሚስቶቻችን ሌላ ወንድ ሳይለምዱ ብናገኛቸው መልካም ነበር አሉ። በሃይማኖት የጸናች ከዝሙት ኃጢአት የራቀች መሆኗን ያውቃልና እኔስ እንኳን ከማዕበል ተርፍሁ እንጂ ሚስቴን በዚህ አልጠረጥራትም አላቸው ያንተ ሚስት ፍጥረቷ ከሴቶች ልጆች አይደለምን ሴት ተንቱንም ምክንያተ ሰሒት አይደለችምን አሉት በፍጹም አታደርገውም አለ እንዱ እሁን እኔ ቀድሜ ሄጄ ለምጃት ለምዳኝ ብመጣስ አል እሱም ባይሆንልህ ቢሆንልኝስ ጥሪቴን እሰጣለሁ ጥሪቴን እሰጣለሁ ተባብለው ተወራርደው ሄደ።

ከቤቱ አትሪቢያ ደርሶ ከተርቢኖሳዊት አገናኙኝ አለ። በንኳ ሰው በሐይ አይቷት አያውቅም እሉት አገልጋይን አስጠርቶ እመቤት ዕሌኒን ላነጋግራት እፈልጋለሁ ንገሪልኝ አላት ገብታ ብትነግራት ሬት ነሳቻት ተመልሳ አልሆነልም አለችው። ገንዘብ ልስጥ ይላል በይልኝ አላት ነገረቻት ተቆጥታ በያዘችው መታቻት። ድጋን እያዘራች ወጥታ አይሆንም ሰልሀ እንጂ ብለሀ አስመታችኝ አለችው እንኪያስ ይሆን ገንዘብ ላገኘ ልብሽ ሁሉቱ የሚተዋወቁበትን ነገር አምጥተሽ ስጪኝ አላት። ይሆንንስ

እደርግልሀለሁ አንተም ነጋድያን መጡ የብስ ሬገጡ ብለህ አስወራ አለችው አስወራ ኀብኢ ነጋድያን መጡ የብስ ሬገጡ እየተባለ ነው ሰውነትሽን ታጠቢ ሽቱም ተቀቢ አለቻት። ስታጥባት ከእንገቷ ያሠረላትን ዕንቁ ረስታው ገባች። ወስዳ ሰጠችው ከመደብር ሄዶ ለምኞት ለምዳኝ መጣሁ ብሎ የያዘውን ዕንቁ አሳየው እውነት መስሎት ልመርምር ሳይል ጥሪቱን አስረክቦ ባዶ እጁን ገባ።

ዕሌኒ ግዙሉን መቆጣቱን አይታ ወንድሜ ምን ሆነሀል እንደወትሮህ ደስ አላለህም አለችው ይህን ያህል ዘመን የደከምሁበት ጥሪቱን ግዕዘል ሲወስድብኝ ምነው አላዝን አላት ይሆን እግዚአብሔር ያየነውን ቢነሣን ያላየነውን ይሰጠን የለምን በዚያውም ላይ ከዘመዶቻችን ተበድረን እንደወትሮህ ነግደህ እንጥራሳን አለችው። እኔስ እበድራ በኖርኩበት ሀገር ተበድሬ አልኖርም እንቺን ግን ሁሉ ይወድሻል እንዳልሽው ሆንሽ ኑሪ ብሎ በንገሩ ይወርፋታል። ተነሥቶ ሲወጣ እኔስ ካንተ ተለይቼ ወዴት እቀራለሁ ብላ ተከተለችው።

ግዮን አስጠርቦ ይዞ መርከብ ተሳፍረው ሲሄዱ አንቴ ምነው ሳምንሽ ከዳሽን ሰውድሽ ጠላሽን አላት አንተን ጠልቼ ማንን ወድጃለሁ አንተን ከጄ ማንን ለመድሁ አለችው እንኪያስ ይህንን ለእገሌ ማን ሰጠው አላት ሠራተኛዋ መጥታ ነገረችኝ አይሆንም አልኳት ኋላ ገላዬን ስታጠብ ረስቼ ገብቼ ነበር እሷ ወስዳ ሰጥታው ይሆናል እንጂ እኔስ መልኩን እንኳ አላየሁትም አለችው አድርገሽው ከሆነ ሥራሽ ያጥፋሽ አላደረግሽውም እንደሆነ ሥራሽ ያውጣሽ ብሎ በማዕበሉ ከቶ ከባሕር ጣላት ማዕበል እየገፋ ወስዶ ጽንፈ በራንጥያ አደረሳት የበራንጥያ ንጉሥ ቀንስጣ ከባህር ዳርቻ ቆሞ ነበር የነጋዴዎች ወርቅ ይሆናል ብሎ አስወጥቶ ቢከፍተው ቀልዋ ቀልዋ ስትል አገኛት ወሰዷን አይቶ አላዋቂ ነውና የክርስቲያን እመቤት ማርያም አንቺ ነሽ? አላት የክፉኝ የቤት እመቤት እንጂ የርሷን የእግሯ እጣቢም አልሆንም አለችው ሥርዓተ አሕዛብ የሚያስተምሯት ሽቱ የሚዘግቡላት ደንገጡሮች ሰጥቶ መንፈቅ ያህል የጠራ የሰሰለ ሲመግባት ቆይቶ በመንፈቁ ተገናኛት ልጅ ወለደች። ስሙ ቁስጠንጢኖስ ተባለ እናቱ ከባሕር ተገኝታለችና ሐመልማል ማለት ነው።

እስከ አራት ዓመቱ ነገሬ ሃይማኖት እያስተማረች አሳደገችው ጥምቀት ግን አባቱ አረማዊ ነበርና እንዳይጣላው ብላ

አላስጠመቀችውም ወደ ሀገሯ ይዛው ከተመለሰች በኋላ እድጉ እካለ መጠን ሲያደርስ ጥበቡን ኃይሉን ሰምቶ አምጥቶ አንግሦት በሁለት ዓመት አረፈ እሱ በበራንጥያ ዲዮቅልጥያኖስ በሮም ተከታትለው ነገሡ። የዲዮቅልጥያኖስ ንጉሥና እንደምነው ቢሉ ቀዳሚ ሰው ነገሬ ነው ሀገሩ ፋዐዮ ግብጽ ነው ከሮሙ ንጉሥና ከኡማርያኖስ ቤት የፍየል እረኛ ሆኖ ሲያገለግል ይኖር ነበር። ንጉሡ እንጥርብያ፣ ፍንጥርብያ፣ የሚባሉ ሴቶች ልጆች ነበሩት ታላቂቱ እንጥርብያ ድምፁ ነበርና ሲያንጐራጉር በገና ሲደረድር እየሰማች በሐጸሙት ተነደፈች አባቷ ጠላት ተነሥቶበት ዘምቶ በዚያው ሲሞት ሰሙ መንግሥቱን ዲዮቅልጥያኖስ ብላ አግብታ አነገሠችው ከሰምንት ዓመት በኋላ ታናሸቱ ፍንጥርብያም ቢትወደዱ መክስምያኖስን አግብታ በእንጻኪያ አነገሠችው።

ዲዮቅልጥያኖስ በንገሥ በ20 ቁስጠንጢኖስ በንገሥ በ19 መክሰምያኖስ በንገሥ በ 8 ዓመት ዲዮቅልጥያኖስ በአባ ቢንያሚን ምክንያት አብያተ ጣዖታት ይትራነዋ አብያተ ክርስቲያናት ይትአጸዋ ብሎ አዋጅ ነገረ። አብያተ ክርስቲያናት ተቃጠሉ፣ መጻሕፍት ተቀነጸሉ፣ ምእመናን በግፍ ታረዱ ተሰደዱም ኋላ ግን ዲዮቅልጥያኖስ ዓይኑን ታውሮ ተሰቃይቶ ሞቷል። /ገድ. ጊዮ/ መክሰምያኖስም እርሱ ድል ነስቶታል። እንደምን ቢሉ ከሞት ከበደት የተረፉ ምእመናን መጥተህ እድነን ብለው ላኩበት። ይህን ሲያወጣ ሲያወርድ ሌሊት በራእይ «በዝ ትእምርተ መስቀል ትመውዕ ለጸርከ» የሚል ጽሑፍ የተረጸበት መስቀለ ብርሃን እየ ምን ይሆን እያለ ሲያሰላስል የታዘዘ መልአክ መጥቶ እንዳየኸው ምስል አሠርተህ ያዝ ታሸንፈዋለህ አለው። ከዚውዱ ጀምር እስከ ተራ የጦር ዕቃ ድረስ መስቀል አስቀረጸ። ከዚህ በኋላ መክሰምያኖስ መጣብህ ብለውት ቢገጥመው አሸንፎታል። መክሰም ያኖስም ሲሸሽ የቴብር ወንዝ ድልድይ ተሰብሮበት ሰጥሞ ቀርቷል። ከዚህ በኋላ ሮምን እንጻኪያን ጠቅሎ የሚገዛ ሆነ በዓመቱም /በ313 ዓ.ም/ አብያተ ጣዖታት ይትዐጸዋ አብያተ ክርስቲያናት ይትራኀዋ ብሎ አዋጁን በአዋጅ መልሶታል።

ዕሌኒ ቀድሞ ልጅ ሳለ ደገኛ ሃይማኖተኛ ይሆንላት ዘንድ ብፅዓት ገብታ ነበርና በዘመኑ ቀጦ ሃይማኖት ስለቆመ ደስ ብሏት ብጽዓቷን ለመፈጸም በ327 ዓ.ም ኢየሩሳሌም ወርዳ መስቀሉን

ከተቀበረበት አስወጥታ አብያተ ክርስቲያናት አሠርታ በዓመቱ /በ328 ዓ.ም/ በዚህ ዕለት አርፋለች።

> ዲዮቅልጥያኖስና መክስምያኖስ በ305 /6/ ዓ.ም መንግሥታቸውን በፈቃዳቸው ለቀው ነበር፣ ቁስጠንጢኖስም የተዋጋው በመክስምያኖስ ተተክቶ ከነበረ ሌላ መክሰምያኖስ ነው የሚል ታሪክም ይነገራል።

ግንቦት 11 ቅዱስ ያሬድ

ያሬድ ማለት ሙራድ ማለት ነው። ብሒረ ሙላዱ አክሱም ነው ትውልዱ ከዘርዐ ሌዋውያን ነው። አባቱ አዳም እናቱ ታውክልያ ይባላሉ። አባቱ ካህን ነበር የተወለደው በ505 ዓ.ም ነው ለትምህርት ሲደርስ ይስሐቅ ለሚባል መምህር ሰጡት ከሱ ፊደል አጥንቶ መዝሙረ ዳዊት ሊማር ለእናቱ ወንድም ለርሱ አጐቱ ወደ ሆኑት ወደ መምህር ጌዴዎን ሄዶ እንዲት ቀለም እንኳ ሳያጠና ሰባት ዓመት ተቀመጠ።

አንድ ቀን ቀለም አጥፍቶ መምህሩ ተቆጥተው በበትር ገረፉት የፀብ አይደለም «ወኢትዘብጥ አሐደ ዘእንበለ ሕጻን በእንተ ትምህርት ወንተሙዝ ከመ በዝንቱ ይትዐቀብ» /ፍት.ነገ.11ከ1/ እንዲል ለተግሣጽ ነው። ሸሽቶ ሲሄድ መንገድ አድክሞት ዋዕየ ፀሐይ ተሰምቶት ከዛፍ ጥላ ሥር ተቀመጠ። ትል ዛፉ ላይ ለመውጣት ሽታ ስድስት ጊዜ እየወጣች ስትወድቅ በሰባተኛው ወጥታ ስትሄድ አየ እኔስ እስከመጨረሻ ብተጋ ትምህርቱ ይገለጽልኝ የለምን ብሎ ተመልሶ መምህሩን ይቅርታ ጠየቀ ከዚህ በኋላ ጌታ ኀሊናውን ንጹሕ ልቡናውን ብሩህ አድርጎለት ባንድ ቀን ብሉይ ሐዲስ ወስና ተገኝቷል።

ከጊዜያት ባንዱ ጌታ ሶስት አዕዋፍ ከገነት ልኮለት በቃል ሰብአዊ ሲያነጋግሩት ተመስጦ መጣበት ጌታ በመንበረ ጸባዖት ሆኖ በቃለ አቅርንት በበብሐተ መላእክት ሲመሰገን ሰማ። ጸሎ ንጉሡ ካህናቱ መሳፍንቱ ለጸሎት ተሰብስበው ሳሉ በሶስት ሰዓት ከመላእክት የሰማው ተገልጾለት ሃሌ ሉያ ለአብ ሃሌ ሉያ ለወልድ ሃሌ ሉያ ለመንፈስ ቅዱስ ቀዳሚሃ ለጽዮን ሰማየ ሣረረ ወበዳግም አርአያ ለሙሴ ዘከመ ይትገበር ግብራ ለደብተራ ብሎ

በዜማ አመስገኗል። ከዚያ በፊት በዜማ ምስጋና የለም ነበርና ሁሉም ተደንቀው ሲሰሙት ወለዋል። ይህን ድርሰቱንም ከእርያም የሰማሁት ነው ሲል አርያም ብሎታል። በሚያዜምም ጊዜ ያሰለ ያደርጋው የዐዋ የወረደው ሁሉ በተመስጦ ይሰማው ነበር። አዕዋፍም ከበር ንዑድትን አውቀው ግዕዝ ፀሐይ እንዳይሰማው በክንፋቸው ይጋርዱት ነበር።

ንጉሥ ዐፄ ገብረ መስቀል ከፍቅር የተነሣ ከቤተ መንግሥታቸው ያኖሩት ነበር አንድ ቀን ከፊታቸው ቆሞ ሲያሰማቸው ተመስጠው ሳይታወቃቸው በያዙት ጦር እግሩን ወጉት እሱም በተመስጦ ያደርስ ነበርና ለጊዜው አልታወቀውም ኋላ ግን ተሰማው የደምህን ካሳ ምን ልስጥህ አሉት ወርቅ ብር አልሻም ወደ ገዳም እንድሄድ ያሰናብቱኝ አላቸው። መስየቀን ባየወዱም ሰመ እግዚአብሔር ጠርተው ምለውለት ነበርና አሰናበቱት። ወደቤተክርስቲያን ገብቶ እጁን በታቦት ጸፃን ላይ ዘርግቶ ቅድስት ውብዕት ሰብሕት ጣዐርኩት ክብርት ወልዕልት አንቀጸ ብርሃን ማዕረገ ሕይወት የሚለውን የእመቤታችንን ምስጋና ንባቡንና ዜማውን ሰተት አድርጐ ተናግሮታል። በዚህም ጊዜ እንደ ከንድ ያህል ከመሬት ከፍ ብሎ ታይቷል። ከዚህ በኋላ ደቀመዛሙርቱን አስከትሎ ተከዜን ተሻግሮ በጸለምት ከገዳማት ሰሜን በአንዱ በደም በሉት ተወስና ኑሮ በዚህ ዕለት ዘገብረ ተዘክሮ ወተዘከረ ጊዴዎን መምህርየ ወተዘከረ አዳም አቡየ ምንት እንከ እበሉ ብሎ ጌታን ጠይቆ ጌታም በተሰፋህ ያመነውን በቃል ኪዳንህ የተማጸነውን እስከ 10 ትውልድ ድረስ ምሬልሀለሁ ብሎ ተስፋውን ነግሮት ተሠውሯል።

የድርሰቱንም ነገር ከዚህ ይናገሩታል። የቅዱስ ያሬድ ድርሰቶች አምስት ናቸው እነርሱም ድጓ፣ ጾመ ድጓ ፣ምዕራፍ፣ ዝማሬና መዋሥዕት ናቸው።

1. ድጓ - እስትጉቡዕ /የተሰበሰበ/ ማለት ነው። ከብሉይም ከሐዲስም ከአዋልድም ይጠቅሳል፣ የጌታን የእመቤታችንን፣ የነቢያት የሐዋርያት የጻድቃን የሰማዕታትን ክብር ይናገራል ድርሰቱን በዮሐንስ ጀምሮ በዮሐንስ ፈጽሞታል። ዓለም በዘመነ ዮሐንስ ተፈጥራ በዘመነ ዮሐንስ ለማለፏ ምሳሌ ነው። ዮሐንስ፣ አስተምህሮ፣ጸመድጓ፣ ፋሲካ ብሎ በአራት ወበዶት ከፍሎች ከፍሎታል። በአራቱ ወቅት መሠረተ በአራቱ ወንጌላውያን ምሳሌ ለዚህም በ22 ሰንፍቀረት አምሳል 22 አርእስት ሰጥቶታል።

ከእነዚህም 12ቱ ምልጣን አላቸው 10 ሩ ግን ምልጣን የላቸውም ምልጣን ያላቸው «ብዙኃን ወተባዝኑ» የተባሉ የሐጋውያን፣ ምልጣን የሌላቸው በተፈጥሮአቸው ፀንተው የሚኖሩ የደናግል ምሳሌ ነው።

2. ጾመ ድጓ — በዐቢይ ጾም የሚደርስ ነው ዘወረደ፣ ቅድስት፣ ምኩራብ፣ ደብረ ዘይት፣ ገብር ኄር፣ ኒቆዲሞስና ሰሙነ ሕማማት ተብሉ በሰምንት ተከፍሏል።
3. ምዕራፍ፡ ምዕራፍ — ማለት ነው የደረሰው በጠለምት ነው ምዕራፍ ዘዘወትር ምዕራፍ ዘዐቢይ ጾም፣ ብሎ በሁለት ከፍሎታል መሠረቱ መዝሙረ ዳዊት ሲሆን በውስጡ ብዙ ንዑሳት ክፍሎች አሉ።
4. ዝማሬ — ምስጋና ማለት ነው። ዝማሬና መዋሥዕትን በደብብ ጉንደር ዙር አባ በሚባል ቦታ ደርሶታል። ኅብስት፣ ጽዋዕ፣ መንፈስ፣ አኰቴትና ምሥጢር ብሎ በአምስት ከፍሎታል። አምስት ከፍል መሆኑ ኀብስት ሥጋውን ጽዋዕ ደሙን ያመለክታልና የአምስቱ አዕማደ ምሥጢር የአምስቱ ቅንዋት ምሳሌ ነው።
5. መዋሥዕት - ምልልስ፣ ሰዋሰው ነፍስ፣ ማለት ነው ለአዕርገ ነፍስ በፍትሐት ጊዜ የሚደርስ ነውና ያስ ይሁን ለሙት ድርሰት ዳርሶ ማዝንን ከማን እግኝቶታል ቢሉ ከዳዊት ይሏል። ዳዊት ለሳኦልና ለናታን ጥጥም ገጥሞ አልቅሶላቸዋል። 1ኛ ሰሙ 1፡ 17- 27 በዘመነ ሐዲስም ዮሐንስ
ኢኢስቆልስ ዘዳግሰቆ ለሞተ ሰው ድርሰት እያደረሰ ያዝንላቸው ያለቅስላቸው ነበረ ድርሰቱ ግን የኔግ ጀግናው የኔግ ሳተናው ሸሽ ተብሏሽ የሚል ሳይሆን በሞቱ ሞትን ያጠፋ ጌታ እምላክ ከሞተ ነፍስ ከርሠ ገሃነም

እንዲያድነው ለሕይወት እንዲያበቃው የሚለምን ጸሎት ነው።
እስከ ... ድረስ የተገለጹት ድርሰቶቹ እምስቱ ጸዋትወ ዜማ በመባል ይታወቃሉ።
ከዚህ ሌላ የውዳሴ ማርያም፣ ቅዳሴ ማርያም ምን ዜማ የደረሰ እሱ ነው። ማይከራህ በሚባል ቦታ ሳለ እመቤታችን ቅዱስ ኤፍሬምን ከቂሳርያ አባ ሕርያቆስን ከብህንሳ በደመና ጠቅሳ እርሱ ካለበት አምጥታ አንተ ውዳሴዬን አንተ ቅዳሴዬን ነገራችሁት በዜማ ያድርሰው ብላቸው ነገረውት ውዳሴዋን ከሰኞ እስከ ቅዳሜ ያለውን በአራራይ የእሑድን በዕዝል፣ቅዳሴዋን በግዕዝና በዕዝል፣ አድርሶታል። ከዚህም አያያዘ 13 ቱን ቅዳሴያት ሁሉ በዜማ አድርጓል። ቅኔንም አምልቶ አስፍቶ ባይናገረው እንጂ ደራሲው እርሱ ነው። ዜማውም ሶስት ዓይነት ነው፣ ግዕዝ ዕዝል አራራይ፣ ግዕዝ የአብ ዕዝል የወልድ አራራይ የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ነው።



ለቤተ ክርስቲያን ያሬድ በጥበብ
የምታቀርብለት ዕጣን ነህ ክቡብ።
መዝሙርና ቅኔ ያወረሰሽን ሁሉት
ንድፍ ሳያገኘው ብልና ጥንት
ይኸው ዛሬም አለ እንዘምርለት
እሱ መጣም አያልቅ እይጉድልም ቅንጣት
የእሱም ልጆች ሁሉ ቢከራከሩት
ምድራዊ ስትሆን ሥጋን የለበሽ
እይተገኘ ደስ አለን በማኅሌትህ
ከመላእክት ጋር ተባብሎ ከበርህ።
ቤተክርስቲያንን እንዳስገነህት

የማያረጅ ካባ ተውም ማኅሌት
ለእምላክህ ስትዘምር እያሸበሸብህ
በዋዕየ ፀሐይ እንዳይነካ ሥጋህ
የሰማይ መላእክት በክንፍ ጋረዱህ።
ልብን የሚመስጥ የሚደመጥ
ያሬድ ግንተ መዝሙር ኢትዮጵያም ኩሩች።
እንደ ቅዱስ ያሬድ በጥዑም ዜማው።
ፈጣሪ አምላክን እናገልግለው።
ሃሌ ሃሌ እያልን እናመስግነው።
ለዚህ ነውና የተፈጠር ነው።

3ኛ መቃ 2፡11 ሃይ አበ ዘአትና /ዮሐንስ ዘ ፈጠር ለእጓለ እመሕያው ከመይትለአክ ቢአምላከ መላእክት/

ግንቦት 12 - ዮሐንስ አፈወርቅ /ከ344 /ገ/ - 404 /ገ/ ዓ.ም/

ዮሐንስ ማለት፡ ፍሥሐ ወሐሤት ፣ ርኀራኄ ማለት ነው። ሀገሩ እንጻኪያ ነው። አባቱ አስፍኒዶስ /ሰፋንዮ/ እናቱ አትናስያ ይባላሉ። አቴና ወርዶ ጥበብ ሥጋዊ ከተማረ በኋላ ጥበብ መንፈሳዊ ሊማር ቅዱስ ባሌልዮስ ከነበረበት ገዳም ገባ። «ወከነ ቢሲቱ መጠነ ቢሲተ ያፍ» ይላል እፍኝ ንብበ ከነጋሥ እስከ መመገብ ድረስ ደርሶ ብዙ ትሩፋት ይሠራ ጀመር።

እርሱ ካለበት ገዳም ሲሊኩስ የሚባል ደገ ባሕታዊ ነበር። ሐዋርያው ጴጥሮስና ዮሐንስ ከበዓቱ ገብተው ጴጥሮስ መራኁት መንግሥተ ሰማያት ዮሐንስ ወንጌል ሲሰጡት አይቶ እንዲህ ያለ ራዕይ አየሁ ብሉ ነገረው። ምን ይሆን ብሎ ይህን ሲያወጣ ሲያወርድ ውሎ ሌሊቱን ሰበገድ ለጸሎት ሲተጋ የታዘዘ መልአክ መጥቶ ከፊቱ ቆመ። ደንግጦ ወደቀ፣ መልአኩ እንሥቶ ጌታ አላዐና የእንጻኪያው ሊቀ ጳጳስ የሚልህን አይሆንም አትበል አለው። በማግሥቱ የእንጻኪያው ሊቀጳጳስ መጥቶ ቅስና ልሹም አለው። አይሆንም አለ። ኋላ ግን መልአኩ የነገረውን አስቦ ተሹሟል።

ከዚህ በኋላ ቀስተንተንያ ወርዶ አንድ ቀን ምእመናን ቅዳሴ በሚያስቀድሱበት ሥጋውን ደሙን በሚቀበሉበት ጊዜ ፀሐይ ከእንዲት ሴት ላይ ጨረሯን ፈነጠቀችባት፣ እኢስቆጶስ ንስጥሮስ ነው። ልጄ የሠራሽው ኃጢአት ምንድር ነው? አላት ከፍቅረ ቤተክርስቲያን የተነሣ የመንፈት ጊዜዬ ሳይፈጸም መጥቻለሁ እንጂ ሌላ ከሰው የተለየ የሠራሁት ኃጢአት የለም አለችው። በልቡ

የጌታን አምላክ ወልደ እምላክነት የእመቤታችንን ወላዲተ አምላክነት የእመቤታችንን ወላዲተ አምላክነት ይክድ ነበርና ድንግል ማርያም እምላክን የወለደች ብትሆንስ ለሴቶች ይህን የደም መፍሰስ ባላተረጓቸው ነበር ብሎ ዕርቃኗን አስቅሎ ክርስቶስን አምላክ ወልደ እምላክ ድንግል ማርያምንም ወላዲተ አምላክ የሚል የተረገመ ይሁን እያላቸሁ ትፋብት አለ። እየሄዱ ይተፋብት ጀመር። «ወሀሎ አሚሃ ዮሐንስ ጠርዐጠር» ይላል ዮሐንስ ከዚያ ቆሞ ነበረ በተራው ቀርቦ እኔስ ወልደ እግዚአብሔር እንዲህ ባለማገኖ ከእመቤታችን በኅቱም ድንግልና እንደተወለደ አምናለሁ ብሎ። የሴቲቱ እድፈት ሳያስጸይፈው የእመቤታችንን ንጽሕና ቅድስና እያሳበ አካሏን ቢስም ከአፉ ላይ እንደ ወርቅ ተቀስሞበታል። በቤተ መቅደስ የነበረች ስዕለ ማርያምም «ለምእመናን ትምህርቱ እንደማር የጣፈጠ ለከሀዲ ግዙቱ እንደ ጦር የጸና እንደ ሰይፍ የተሳለ በእውነት አፈወርቅ ልሳነ ወርቅ» ብላ በቃል ሰብአዊ መስክራለታለች። «ሰላም ለዓመ ኃፍረተ ትከት ቅድመ መዋዕለ ንጽሕ ሰብኪ፣ ተአምረ ፍቅርኪ ያርኢ ወያስተኀፍር ዘዘኪ፣ማርያም ሰዐሊ ለዮሐንስ ጽጌ ትንግሂ፣ ወደሰቶ ወአእኩተቶ ቅድመ ገጸ ኩሉ ጉባኤ፣ አፈወርቅ እንዘትብል ጊዜያተ ከልኤ። እንዲል ደራሲ።

ከዚህ በኋላ በፈቃደ እግዚአብሔር በእንጻኪያ ሊቀጳጳስነት ተሾመ። ተሹሞም ግሰ ብዙ ተግሣጽ ጽፏል ብዙ ድርሳናት ደርሷል። ንጉሡ አርቃዲዎስ ይባላል። ወዳጁ ነው። ሊጠይቀው ሄዶ ሳለ መምህር አንተን ሳገኝህ ነገሩ ይጠፋኛል ነገሩን ሳገኘው አንተን አጣሀለሁ፣ ከልቤ ሲወጣ ሲወርድ የሚኖር ነገር አለ፣ ወንጌላዊ «ኢያእመራ እስከ እመ ትወልድ ወልደ ዘበኩራ የበኩር ልጇን እስክትወልድ አላወቃትም» /ማቴ 1፡ / ያለው። ከወለደች በኋላ ወንዶች ሴቶችን በሚያውቁበት ግብር አውቋታል ማለት ነውን አለው። ይህስ አይደለም ጌታን ጽንሳ ሳለች ሥጋዌ በብዙ ኅብረ ትንቢት የተነገረለት በብዙ ኅብረ አምሳል የተመሰለለትን ጌታ እንደጸነሰች ለማጠየቅ መልኳ እየተለዋወጠ ይታየው ነበረ፣ ከወለደችው በኋላ ግን በአንድ ኅብረ መልክዕ ታይታዋለችና ስለዚህ ነው ብሎ ተረጉሞለት በዚህም ጊዜ ከግድግዳ ላይ የነበረች ስዕለ ማርያም ካለችበት መጥታ ሦስት ጊዜ በራሱ ላይ ዞራ «ሠናየ ተናገርከ ዮሐንስ አፈወርቅ ዮሐንስ ልሳነወርቅ» ብላ አወድሳው

ከቦታዋ ተመልሳለች። ንጉሡም ለመታሰቢያ ሁለት ልሳናተ ወርቅ አሠርቶ በግራ በቀኝ አድርጎላታል።

በዚህም ላይ ንጉሡ አርቃዲዎስ ንግሥቲቱ አውዶክስያ ልጅ እየወለዱ ይሞትባቸው ነበርና ሴት ልጅ በወለዱ ጊዜ እንዳትሞትባቸው ብለው እርሱን እንዲያጠምቃት ለሊት ሲሄድ መልአከ ሞት ከመንገድ ተገናኘው ወዴት ትሄዳለህ? አለው። የአርቃዲዎስን ልጅ ነፍሷን ከሥጋዋ ለይተህ እምጣ ብሎኝ ላመጣ እሄዳለሁ አለው። ቆየኝ ላጥምቃት ብሎት ሄደ። ካጠመቃት በኋላ ረስቶት በሌላ መንገድ ተመለሰ። የካህናት የመዓረጋቸውን ደንነት ለማጠየቅ /17/ ወዲያ ወዲህ ሳይል 10 ዓመት ቆሞ ቆይቷል። «እምን አፋሁ ዘወርቅ ሰሚእ ግዘተ፣ እንበለ ይዕርግ ላዕለ ወእንበለ ይረድ ታሕተ፣ መልአከ ሰማይ ቆመ ዐሠርተ ዓመተ» እንዲል አርኬ።

በአሥረኛ ዓመቷ ለባልታዉች ልጃቸውን መርቀልን ብለው ላኩበት ቀድሞ በሄደበት መንገድ ሲሄድ መልአከ ሞትን ቆሞ አገኘው ። ምነው ከዚህ ቆመሀል? አለው። አንተ ቆይ ካልከኝ ጊዜ ጀምሮ ወዲያ ወዲህ ሳልል ቆሜአለሁ አለው። አትፍቻለሁ ሂድ የታዘዝከውን ፈጽም አለው። ከዚያ ሲደርስ ሞታ ሲላቀሱ አገኘ። ነገሩን ነግሮ አጽናኗቸው ተመልሷል።

ንግሥቲቱ አውዶክስያ መፍቀሬተ ንዋይ ነበረች። በዓመት 3 ጊዜ የምታፈራ ለከተማ ቅርብ የሆነ ርስት ያላት መበለት ነበረች ርስቷን ነጠቀቻት። መጥታ ለርሱ ነገረችው መልሺላት አላት አልመልስም አለች። ርስተ ምድር ነጥቀሽ ርስተ ሰማይ ታገኚ መሰለሽ? ብሎ ከቅጽረ ቤተክርስቲያን እንዳትገባ ሥጋውን ደሙን እንዳትቀበል ከምእመናን እንዳትገናኝ አወገዛት። እርሷም በበኩሏ እሱ በነውር ምክንያት የሻረቸውን ሲኖዶስ ቀኖናት በብዕለ ታሥሮ ይጋዝ ብለው እንዲፈርዱበት አደረገች። ታሥሮ ወደ ደሴት አጥራክስያ ተጋዘ። የሮሙ ንጉሥ አርቃዲዎስ ዜና ገድሉን ስነ ጽድቁን እየሰማ ሲያደንቅ ይኖር ነበርና ባትመልሰው ጠቡ ከንቱ ነው ብሎ ከአርቃዲዎስ ላከ። መልሱ ብሎ አስመለሰው ያች ግን በድጋን አስጠብቃዋልና ሁለተኛ እሥራ አጋዘችው በዚያው አርፏል። እሷም አልተጠቀመችም እሱ ካረፈ በኋላ ጽኑ ደዌ አደረባት። ከመቃብሩ ሄዳ በድያለሁ ይቅር በለኝ እያለች ብዙ መከራ ተቀብላ ተፈውሳለች።

ዮሐንስ አፈወርቅ ሊቀ ሊቃውንት	ቀም ሲመበክ የድንግልን ክብር
መጺብ ተኔፅማ ምዑር ደግ አባት።	ድንግል በሥጋ አድራ በድንቅው
እውነተኛ መምህር ልቅ አበተ አያደለ	አሊመርቅ ብዙ አመሰነቸው
ንጉሥትን ያመተ ደምን በድላ።	እንዳልቀየመት ነሥተ መብቅት
በእግዚአብሔር ፊት በትክክርላት ነዉ	በምት ዋል ከሚሊ የደፃን ጠብቅት
በጣዖት መልአክ ያጠፋት ለርሱ።	ካምኝነን ሁሉ ጉሥዲ በበጡናት
ታሉ የዋሌስ ትምህርት እውነ	ይዛልያል ሊሉ መዋር ክበደት
አያታሉ ፈቸዉ መጥፋታያን።	ጌታ እንዳልካ አመንትን ተርክብ።
በበዓት መልሕ አንዳች ላያዊር	የቶፉን መንፈስ አለር ...

አባ አፋሲ - /ከመስኝ ቅዱሳን/

ሐ. ፍልሰተ ሥጋሁ ለአቡነ ማር ተክለሃይማኖት

ዜና ዕረፍታቸው በገጽ እንደተገለጸው ጌታ በ57 ዓመት ደቀመዛሙርትህ በቤተክርስቲያን እንዲቃጠሉ ሥጋህን ወዲያ ያፈልሱታል ብሎ ነግሯቸው ነበረ። ጊዜው ሲደርስ 19 ቀን ለአባ ምርኔት ለአባ ሕዝቅያስ ተገልጸው ጌታዬ የነገረኝ ተስፋ ሊፈጸም ጊዜው ደርሷልና በሩቅም

በቅርብም ያሉ ደቀመዛሙርቶቹን ሰብስበህ በ12 ሥጋዬን አፍልሱ፤ እኔም ከቅዱስ ሚካኤል ጋር እመጣለሁ፤ ምልክት ይሆናችሁ ብሎ ቦታነ መብራቱን አጥፉ እኛ ስንመጣ ይበራል አላቸው። እንዳሉትም ደቀመዛሙርቶቻቸውን ከሩቅም ከቅርብም ሰብስበው በዚህ ዕለት ሥጋቸው ካረፈበት ከመካነ አበው ቢገቡ እንደ ፀሐይ ሲያበራ አገኙት ... ቤተመቅደስ ከቅዱስ ሚካኤል ጋር መጥተው ከመንበሩ ተቀመጡ፤ ሲመጡም የጠፋ መብራቶች በርተው ተገኝተዋል እኒያም በዕልልታ በደስታ አጽማቸውን ከእንጦ መንበር አኑረውታል። ታሪኩ የተፈጸመው በ1349 ዓ.ም ቀን ነው።

ግንቦት 14 አባ ጳኩሚስ /ከ290 - 346 ዓ.ም/

ሀገራቸው ጽርዕ ነው። በገዳመ ላውናስ በ 6 ሺህ መነኮሳት ተሹመዋል። ቀን ለማስተማር ለእንግዶች ሌሊት ለበሽተኛ ለሌሎች ያገለግላሉ ይኖሩ ነበርና ሰኮሌ ማገገር መላእክት ተበልፀው። በሌሊታቸው ጥቂት ትምህርት ነበረባቸው። አንድ ሌሊት ሲበግዱ

ላባቸው የቆሙበትን ምድር አራሰው ጌታ ተገልጾ አሁን ይህ ሁሉ ስግደት ይህ ሁሉ ጸሎት ለማን ብለህ ነውሕ አላቸው ጌታዬ ላንተ ብዬ ነዋ አሉት በማግሥቱ በችንካር ተቸንክሮ በመስቀል ተሰቅሎ ታያቸው። ጌታዬ አሁን ደግሞ መስቀል ለማን ብለህ ነውሕ አሉት ላንተ ብዬ ነዋ አላቸው። ይህ ሁሉ ትናንት በተናገርኩት አይደለምን ደግ አላደረግሁም ብለው ተጸጽተዋል። በሚሔዱበም ጊዜ ከትና ሲልል በዓይነልበና ይታያቸው ነበር አንድ ቀን ዓይናቸው በመጸደሁ ነበር እሉ። የታዘዘ መልአክ ነጥቆ ወስዶ ጸድቃንን በገነት ሲያመሰግኑ ኃጥኣንን በሲኦል ዋይ ዋይ ሲሉ አሳያቸው። ከዚህ በኋላ መላ ዘመናቸውን በስጋ ሰበ... ሲያገኙ ሲያስቀምጡ ኖረዋል። ጊዜ ዕረፍታቸው ሲደርስ ጌታ ገዘኸሀን እየሁለሁ ለመናገሥም ሰማሁለህ በስምህ የተማጸነውን ሁሉ ከሞተ ነፍስ ከርደተ ገሀነም አድኅለሁ ብሎ ተስፋቸውን ነግሯቸው በዚህ ዕለት ዐርፈዋል።

ግንቦት 16 ኢያሱ ሲራክ

ኢያሱ ማለት መድኃኒት፤ ሲራክ ማለትም ጠቢብ ማለት ነው። ሲራክ የጥበብ ስሙ ነው አባቱ አልዓዛር ይባላል። መጽ ሲራ 5:1 ጌታ ጥበብ ገለጸለት የጥበብ ሁሉ መገኛ ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው ዝም ሳይፈጠር ጥበብ ከርሱ ጋር ነበረች ብሎ ስለጥበብ ተናግሯል። ሲራ 1:1 ከመሳፍንት ሙሴን ከነገሥታት ዳዊትን ከነቢያት ኤልያስ ኤልሳዕና ኤርምያስን አብነት አያደረገ ታላቅ የጥበብ የምክር መጽሐፍ ጽፏል መጽሐፉም ከ 46ቱ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት አንዱ ነው።

ከምርኮ መልስ ከ 470 ዓ.ዓ ወዲህ የተነገ መሆኑን መጽሐፉ ያመለክታል

ግንቦት 17 ኤጲፋንዮስ ኤጲስቆጶስ /ከ 315 - 403 ዓ.ም/

ወላጆቹ አይሁዳውያን ነበሩ አባቱ ሞቶ እናቱ እርሱንና እኅቱን የምታሳድግበት አጥታ ስትቸገር እርሱ ያላቸውን አንድ አህያ ሊሸጥ

ይዞ ሲሄድ ከነዳና ፊላታዎስ የሚባል ደግ ሰው አገኘው። ዋጋውን ሲነጋገሩ አህያው ዘሎ ከላሊቱን ረገጠው ፣ ወድቆ ፊላታዎስ የክርስቶስ ኢየሱስን ስም ጠርቶ ቢጎትተው ተነሣ። አህያውንም ወድቆ ቢለው ወድቆ ቀረ። ኤጲፋንዮስ በሰው የወደቀውን የምታነሣበት የቆመውን የምትጥልበት ኢየሱስ ማነው? አለው። ኢየሱስን ለቤዛ ብዙኃን ከሰማያት ወርዶ ከድንግል ተወልዶ ዕውር ሲያበራ ሙት ሲያስነሣ ወገኖቹ አይሁድ ጸልተው ተመቅኝተው ሰቅለው የገደሉት አምላክ ወልደአምላክ ነው። አለው ይህን በልቡ አኑሮ ባየው እየተደነቀ ወደ ቤቱ ተመለሰ።

ከዚህ በኋላ ባለጸጋ አጐት ነበረው እሱንም እኅቱንም ወስዶ አሳድጎ ሀብቱን አውርሷቸው ዐረፈ። አንድ ቀን ከአባ ሉክዮስ ጋር በመንገድ ተገናኝተው እየተጫዋወቱ ሲሄዱ አንድ ችግረኛ ሰው እግዚአብሔር ጠራቸው። አባ ሉክዮስ ወርቅ ብር የለውምና የለበሰውን አውልቆ ሰጠው። ወዲያው መልአክ ከበረዶ የነጻ ልብስ ሲያጎናጽፈው አይቶ አባቴ አምላክህን አመልክ ዘንድ ሃይማኖትህን አስተምረኝ አለው። አስተምሮ አጥምቆታል። ከፍጹምነትም እንደሚደርስ አውቆ መዓርገ ምንኩስና አስተቶታል በዚህ ጊዜ የ17 ዓመት ወጣት ነበረ። ከዚህ በኋላ በጾም በጸሎት ተወስና በትኅርምት የሚኖር ቢሆን ሀብተ ፈውስ ተሰጥቶት ሕሙማንን የሚፈውስ ሆኗል፤ ሙትም አንሥቷል።

መምህሩ አባ ኢላርዮን መንፈስ ቅዱስ ገልጾለት ጌታ የብዙኃን አባት እንድትሆን መርጦሀልና፤ ቆጵሮስ ሂድ ተሾምልን ሲሉህ አይሆንም አትበላቸው አለው። ከበዓቱ መውጣቱን ከመምህሩ መለየቱን ባይወድም ፈቃደ እግዚአብሔር ነውና ሁለት ብላቴኖች አስከትሎ ሄደ። ጌታም ለቆጵሮስ ኤጲስቆጶስ ሁለት ብላቴኖች ያስከትለ ሁለት የወይን ዘለላ የያዘ ኤጲፋንዮስ የሚባል ገዳማዊ ወደ ገበያ ይመጣል እሱን ሹመው አለው። ቢሄድ ሁለት የወይን ዘለላ ይዞ ሁለቱን ብላቴኖች አስከትሎ ሲገበያይ አገኘው ኤጲፋንዮስ የምትባል አንተ አይደለህምን አለው። አዎን አለ ጌታ ያዘዘኝ አለና ተከተለኝ ብሎ ወስዶ ሾመው። በሶስተኛው ቀን ቅስና ሰጠው ኋላም እርሱ ሲሞት ኤጲስቆጶስነት ተሹሟል። ተሹሞም ሳለ ብዙ ድርሳናት ደርሷል ብዙ ተግሣጸት ጽፏል።

ንግሥቲቱ አውዶክስያ የአንዲት መበለት ርስት በመንጠቋ ምክንያት ዮሐንስ አፈወርቅ አውግዞ ከማኅበረ ምእመናን ለይቷት

ነበርና የሃይማኖት አባቶ ሳይፈርዱኝ በቦንቱ አውግዞኛልና መጥቶ እይልኝ ብላ ላከችበት ሄደ፣ ተይ ያለሽን ተቁመ አላት ይሆንልሽ አለተውም አለች እንግዲያውስ የፎቀሰሰሽን ቃል ልታከብሪ በተገባሽ ነበር አላት ይሆንን ካልከማ አብያተ ክርስቲያናትን አሰግቼ አብያተ ጣዖታትን አስከፍታለሁ አለችው። ከርሱ ዘንድ ሄዶ ወንድሜ ጥቂት ጊዜ ምእመናን ከመከራ እረፉ ስንል በዚህ ምክንያት ደግሞ መከራ ሊመጣባቸው ደግ ነውን ተወው አለው። ርስተ ምድር ነጥቃ ርስተ ሰማይ ታገኛለችን አይሆንም አብያተ ጣዖታትንም ብታስከፍት ለርሷ ይበሰታል አለ።

ተመልሶ ከንጉሡ ሊሰናበት በገባ ጊዜ ኤጲፋንዮስ ዮሐንስ አፈወርቅን ከሹመቱ ሻረው ከመዓረጉ አዋረደው ብላ በሉለት አስወራች።

ዮሐንስ ሊሰናበት ሲሄድ ምነው እንዲህ አደረግኸኝ? አለው ኧረ ምንም አላደረግሁብህም አለ። መሄድግ ትሄዳለህ ከመንበርህ ግን አትቀመጥም በመንገድ ትሞታለህ አለው። እርሱም በበኩሉ መመለስግ አይቀርም ትመለሳለህ ነገር ግን ሁለተኛ ተጋዝ ትሞታለህ አለው። የጠብ አይደለም የዮሐንስ ሞት ለኤጲፋንዮስ የኤጲፋንዮስ ሞት ለዮሐንስ ተገልጾላቸው ነው እንጂ ይገባም አልቀረ ዮሐንስ አፈወርቅ በፅርቅ ከተመለሰ በኋላ ሁለተኛ ተጋዞ በዚያው ዐርፏል። ኤጲፋንዮስም ጥቂት ቀን ተጓዞ ባደረበት ከመንገድ በዚህ ዕለት ዐርፏል። 11 ቀን ተጉዞው በ28 ደፈሱ በየደማናት አፈሰ በመንገድ ዳጎ የሚሬቸው ሁለት ሊያቀናት እናስቀብርም ብለው መቃብር ከአክሱም 40 ቀን ተቀመጡ ይሁንንም ያሉ ቀን ሲቆይ መገዘው አልተለውምም ነበር። ኋላ ግን አንድ ሊያቀን ቢግዘው እኒያን በተአምራት አጥፍቶ ተቀብሯል።

ክብር መንፈሳዊ ኤጲፋንዮስ	አምላኩ ክርስቶስ ነውና ብርታቱ።
ሥግን ባለጸጋ ለመንፈስ ቅዱስ	ከሞተ በኋላ ሥጋው ሞቶ በድን
ገር በልጅነቱ በመቃትሉ	ጸድቃን የመሰሉ ተገዝዋቸን
በበጊዜ ተተኖ በዘም በመንቱ	ተጋዥ ልሳኑ ትምህርት እንዲሆን
በማደጉን አጻዑ ቢጋዘም ጉልበት	ሬሣዊ ተሳለቀን እንዳይገን እንዳ
ያሳዘቅ ነበር ሕዝቡን በሰሐበቱ	አይወጅነዉና ይቅርብ ተገኘል

ምሳ 10 :29 ፣ 12: 2

ግንቦት 18 በዓለ ጰራቅሊጦስ

ጌታ በሚያርግ ጊዜ ደቀመዛሙርቱን እንትሙሰ ንበሩ ሀገረ ኢየሩሳሌም እስከ ትለብሱ ኃይለ እምአርያም ሉቃ 24:49 ብሏቸው ነበር። ተናጋር የማያስተር ምሉ የሚያደርሱ ነውና ዓረገ በ10ኛው ከተነሣ በ50ኛው ቀን ጰራቅሊጦስን ለያላቸዋል።

ጰራቅሊጦስ ማለት መንፈስ ጽድቅ መንፈስ ሕይወት ኀሥሮሮ ናዝራዊ አስተንፋስ አጽናኝ ሕይወት አጽናኝ አስትንፋስ ማለት ነው ስለምን ቆይቶ በ10ኛው ቀን ላከላቸው ቢሉ በ10ኛ መዓርግ የነበረ እኛ ነበርንና ወደ ክብራችን ወደ መዓርጋችን እንደመለሰን ለማጠየቅ ነው ዓሥረኛም 10ሩን ቃላት ሲጠብቁ መንፈስ ቅዱስ የሚሰጥ መሆኑን ለማጠየቅ ነው።

"ወአስተርአየዎሙ ልሳናት እሳት ከፋላት ከመ እሳት ዘይትከፈሉ" ይላል በአምሳለ እሳት አድርባቸዋል። ወዲያውም የሚያውቁት ቋንቋቸው የማያውቁት ተገለጸላቸው ቀድሞ ከሚናገሩት ከቡሉይ ይለቅ ቋንቋ ሌላ 71 ቋንቋዎች ተገለጸውላቸው ምሥጢር የሚተረጉሙ ሆነዋል። ከአይሁድ ወገን እኩሌቶቹ ይህ ነገር ምን ይሆን? እሉ እኩሌቶቹ "እሉሰ ጸበ ዳግሎ - ጉሽ ጠጅ ጠጥተው ሰክረው የሆነ ያልሆነውን ይቀባጥራሉ "እሉ። ቅዱስ ጴጥሮስ ሀሳባቸውን አውቆ እኮ ከመትትሌሙሁም አንተው ሰክራን እመንኒቁ ዘትብሉ ሰከረዋል የምትሉ እናንተ እንደምትጠረጥሩአቸው አይደለም እስመ ነገህ ብሔሩ ወበዚሁ ሠለስቱ ሰዓት - ጊዜው ገና ሰዓቱም ሦስት ሰዓት ነውና፤ ዳሩ ግን እሰወጥ እምነመንፈስየ ላዕለ ኩሉ ዘሥጋ (ኢዩ 2: 28) ተብሎ የተነገረ ትንቢት ይፈጸም ዘንድ ይህን ያደረገ እናንተ ጸልታቸሁ ተመቅኝታችሁ የሰቀላችሁት ክርስቶስ ኢየሱስ ነው እኛም ነቢያት ትንቢት የተናገሩለት ምሳሌ የመሰሉለት አምላክ ወልደ አምላክ ለመሆኑ! ከሙታን ተለይቶ ለመነሣቱ ለማረጉ ዳግመኛም ለመምጣቱ በምስጋና ለመምጣቱ ምስክሮች ነን አላቸው ምንተ ንገብር እንግዲህ አሁን ምን እናድርግ አሉ "ንስሑ ወተጠመቁ በስመ ኢየሱስ ክርስቶስ ከከፋታችሁ ተመለሳችሁ በስሙ ተጠመቁ አሏቸው "ወተወሰከ በይእቲ ዕለት መጠነ ሠለስ ምእት ነፍስ " ይላል ሶስት ሺህ ሕዝብ አምነው ተጠምቀዋል። ሐዋ 2:1-41 ይህ የተፈጸመ በ33 ዓ.ም በዚሁ ቀን በዕለተ እሑድ ነው። ዕለቱን ሲታወጉት ሀብተ መንፈስ ቅዱስ የተመጠበት፣ ወደ የሀገራቸው በተመለሱ ጊዜ በአሕዛብ መካከል የሚያስተምሯቸውንና የሚመሰክሩላትን 3000 ምእመናን ያገኘችበት ዕለት በመሆን የቤተክርስቲያን የልደት ቀን ሲሉ ጠርተውታል።

4. ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን ሲቀበሉ እመቤታችን ከሌሎች ቅድሳት አንስት ጋር አብራቸው ለሌሉት ትተጋ ነበር ሐዋ 1:14፤2:1

በገዐተ ክርስቲያን ከብርት ልዕት ናት	አዝነው ተደነቀ ለዘለፈቻቸው
መንፈስ ቅዱስ ለሰው የተሰጠበት	በክርስቶስ አምነው በሙ... ተጠምቀው
ጌታ ጉዞተቸው በቅዱስ መንፈስ	የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ ተቀብለው
ሐዋርያት ወኑ ከብልጹቶ ታደሱ	ከነበር ከፉ ሥራ ከክፉት ርቀው
ምሥጢር ለመተርጎም በሙቀት ንጽሙሉ	በፍቅር በአንድነት መከሩ ታግሠው
ሃይማኖታቸውን በገዳዝ መስክሩ	በዓ እየሙ ቢነሙን ተናግረው
የአይሁድን ገልምጫ ቀትንም አለፈሩ	ወንጌልን በአንድነት በሥራ መከለሡ
ለቤተክርስቲያን የሐዋርስ ሰብከት	ለአምላክ ታምነው ኖሩ በመጣ ለድሚያቸው
ምቱት ሺህ ነፍሳትን አተረፈላት	ለምእመናን ሁሉ በጐ አብነት ሆነው።
ተመለሱ ብሉ ሊተርባ ሲመክሩቸው	
ሲገሠጸቸውም በዙሩ ሥራቸው	
ከአይሁድ መካከል የወጡትረዋቸው	

ግንቦት 19 ኢስድሮስ ሰማዕት

ሀገሩ እንጾኪያ ነው ። አባቱ በድላእን እናቱ ሶፍያ ይባላሉ። እግዚአብሔርን የሚፈሩ ሰውን የሚያከብሩ ደጋጎች ነበሩ። በድላእን የንጉሡ ዲዮቅልጥያኖስ ሲቀሐራ ነበረ። ዲዮቅልጥያኖስ በንጉሥ በ20 ዓመት ሃይማኖታቸውን ካዱ ለጣኦት ስገዱ እያለ ምእመናንን ይፈጃቸው ጀመረ። በድላእን ፈጣሪዬን ክጄ ለጣኦት ሰግጄስ አልኖርም ብሎ ሚስቱንና ሁለት ልጆቹን ይዞ ከአድባራት ባንዱ ተቀመጠ። ዲዮቅልጥያኖስ አስፈልጎ አምጥቶ በሰይፍ አስመታው ኢስድሮስ በዚህ ጊዜ የ12 ዓመት ልጅ ነበረ። ይህ ምንም እያውቅም ብሎ ከእናቱና ከእኅቱ ጋር አጋዘው።

እሥራ ስምንት ዓመት ሲሞላው በሌላ ሰፍራ ያለ ዐባዊ ኢራንራን ልብስ ወኢመክርከሙ ትትመየጡ እምሃይማኖትከሙ አልተመለስክምን አለው ፈጣሪውን የከዳ ለጣኦት የሰገደ ይመለስ እንጂ እኔማ ፈጣሪን እውቄ ሃይማኖቴን ጠብቄ የምኖር ነኝ አለው። ከግንድ አስቅሎ ሥጋውን በአስዋጠብርት አስተፈተፈው እናቱ አንተ ርጉም አንተ ጎሰም እያለች ደሙን እየታፈነች አረጨችበት። እኅቱም አርምያ ትባላለች በደንጊያ ፊት ፊቱን ትመብዋ ጀመረች። ሰይፍ ጃገራው ሁለቱንም በሰይፍ መታቸው። እሱንም ጉን አስቀድሶ በእሳት አታጥሎ ሰማይ አስዋፍ ለምድር አራዊት ፈት ይሁን ብሎ ከዱር አስጣለው። ጌታ ከሞት አንሥቶ ከንጉሡ ፊት አቀረበው ከሠራዊቱ 800 አመን በአመላከ ለኢስድሮስ አያሉ አንገታቸውን ለሰይፍ ሰውነታቸውን ለእሳት ሰጥተው በሰማዕትነት አርፈዋል።

እሱንም ከብረት አልጋ አስተኝቶ ከበታቹ እሳት አስነደደበት እሱንም ከሞት በኋላ ተነሥቶ መጣ ከዚህም በኋላ የወፍጮ ደንጊያ በአንገቱ አሳስሮ ከባሕር አስጣለው፣ ደንጊያው ሠጠመ እርሱ ወጣ።

በመጨረሻ ሥቃዩ ይጸናበት ብሎ ግንድ ላይ በችንካር አስቸንክሮ ተወው። ጌታ በስምህ የተማጸነውን ምሬልሀለሁ አንተ ከገባበት መካነ ዕረፍት አስገባልሀለሁ ብሎ ተስፋውን ነግሮት ከ 17 ዓመት ተጋድሎ በኋላ በዚህ ዕለት ዐርፏል።

➢ ከታሪኩ አንጻር መዋዕለ ሕይወቱ ከ292- 329 ዓ.ም መሆኑ ነው።

ሰማዕቱ ኢስድሮስ ላለ ቃል ፍጹም	አንገቱን ለሰይፍ ለችንካር እጁን
የመልካም ዛፍ ፍሬ ጣፋጭ ነው መልካም	ኢስድሮስ ለአምላኩ በአሕዛብ ፊት
የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክነቱን	እንደ ቅዱስ ጊዮርጊስ ሲቀበል ሰማዕት
ሰግለም ሲመሰክር ሊያስተምር እምነትን	እስከ ሞት ድረስ ነው የታመነለት
በምቶች አይደለም ሳይቀምስ መከራን	የሰማዩን መንግሥት የክብርም መውረሻ
እንደ ሐዋርያት መተቶ እንጂ ነፍሱን	በርሱ መታመን ነው አስከመጨረሻ

ማቴ 40 22፣ 2413

ግንቦት 21 ደብረ ምጥማቅ

ከመሳሳ ሰሰቱ የእመቤታችን በዓላት አንዱ ነው። ደብረ ምጥማቅ በምኔተ ገምኑዲ አትሪብ የምትገኝ ቦታ ናት። እመቤታችን በስደት ሳለች ጌታ በዚህ ቦታ በስምሽ ዐቢይ ቤተክርስቲያን ይታነጻል ስሙንም ደብረ ምጥማቅ ይሉታል ብሎ ነግሯት ነበር። ይኸውም አልቀረ። በዚሁ ቦታ በእመቤታችን ስም ቤተክርስቲያን ታንጾ ስሙ ደብረ ምጥማቅ ተብሏል።

በዚህም ዕለት እመቤታችን ከፀሐይ ሰባት እጅ አብርታ ከጉልላቱ ላይ በመንበረ ብርሃን ተቀምጣ መላእክት ሊቃነ መላእክት ከበው ሲያመሰግኗት፣ ነቢያት ሐዋርያት ጻድቃን ሰማዕታት እጅ ሲነሡ ታይታለች። እስከ አምስት ቀንም ምእመናኑን አረማውያኑን አንድ ወገን አድርጋ ስትባርክ ሰንብታለች። ከዚህ በኋላ ምእመናንም አረማውያንም በየዓመቱ እኒህን አምስት ዕለታት በደብረ ምጥማቅ ተሰብስበው የሚያከብሩ ሆነዋል።

ግንቦት 24 ሀ. ዕንባቆም

ዕንባቆም ማለት ጠቢብ ለባዊ ማለት ነው ትውልዱ ከነገደ ስምዖን ነው ወአብበለ ተብሊስ ከመ ይለድ ምሳሌ ለአለ የእጽዳ ይላል ንፍሮ ቀቅሎ ለአጫጆች ምሳ ይዞ ሲሄድ ቅዱስ ሚካኤል ሰድሎ ዘንተ ምሳሌ ለዳንኤል ዘሀሉ ውስተ ጉበ ግቤ ግብ ብሊሉን ግቢሉን በጉድጓድ ለተጣለ ለዳንኤል

ሥብድለት አለው፡፡ ፀገኤል ወዴት አለ በቢሉንንም አላውቅም አለ ወንሥእ በአሐቲ ሥዕርተ ድግሁ ይላል እንዲት ጠጉሩን ይዞ አድርሶት ሳይከፍት ገብቶ ሚግቦት ሳይከፍት ወጣ፣ መልሶ እንደመጣው መልሶታል ተሬ. 45

ከዚህ በኋላ እስራኤልን ሲያስተምር ቆይቷል የጌታም ሰው መሆኑ ተገልጦለት እግዚአብሔርን እምቴማን ይመጽእ ወቅዱሱ፣ እምደብረ ፋራን ወእም አህጉረ ይሁዳ እግዚአብሔር ከቴማን ይመጣል ቅዱሱም ከፋራን ተራራ ከይሁዳም ሀገሮች ብሎ ትንቢት ተናግሯል፡፡

➢ መዋዕለ ትንቢቱ ከ 609-606 ዓ.ዓ

ለ. በአተ ግብጽ

ጌታ ተወልዶ 2 ዓመት ሲሆነው ሰብአ ሰገል እጅ ሊነሡ እጅ መንሻ ሲሰጡ "አይቴ ሀሎ ዘተወልደ ንጉሠ አይሁድ እያሉ ቢመጡ ሄሮድስ መንግሥቱን የሚቀናቀነው መስሎት" ሊገድለው አስቦ ሕፃናቱን ሰብስቦ ብሎ ባሰበ ጊዜ ቅዱስ ገብርኤል ለዮሴፍ "ንሣእ ሕፃነ ወእሞ ወሑር ብሔረ ግብጽ" አለው፡፡ ማቴ 2:13 እመቤታችን ደንግጣ ለዋለ ለደረሰችላ ሰሎሜን ልጇን አዝላ የሴፍ ሰሎሜን አስከትላ ሻሽት ጀምራ በዚህ ዕለት ያደረ ጉባድ ትዘታለች፡፡

... ደርሰው ወንዙን ተሻግረው ካለፉ በኋላ ጌታ በአንዱ ... እያለ ሲሄድ ከአንዱ ደንጊያ ላይ አሥረ እግሩ ተቀረፀ፡ ... በዚህ ቦታ በስሙ ወቢይ ቤተክርስቲያን ይታነጻል ... ብዬታል፡፡ ንዳው አስቀድስንም ከፋቅ አላይቅ በዚያ ... ላይ እንደመሳሰከተ ለማይ በገድልና የሚያንዳዳሉኝ ... ብዬታል፡፡

በማቀቢያው ወደ ምድረት ሲደርሱ የዮሴፍን በትር ከሁለት ሰብሮ ከመሬት ተከሎ ጥዑም ውኃ አፍልቆ አስምሎ ጥዑም መዓዛ ያላቸው ልዑም በለሳን /በለ ሰን/ ይባላል፣ ለሜሮን ተምቀት መቀደሻ ይሆናል፡፡ ብዬታል፡ አስመናይን ከሚባለ ቦታም ሲደርሱ እንጨቶችና ተራሮች ለሃሰፀዋዕታል፡፡ "ምዕረ ትትፌሣሕ ሰበ ተገዘን ለሕጻን ወሊቱ፣ ርእያ ዘገብረ ተአምረ ውስተ ደወለ ግብጽ አመብእቱ፣ እንፈርዐ አድባር መበሥ ሉዓ እንዘ ጻሕ፡፡

➢ የእመቤታችን መዋዕለ ስደት ከ 02 - 05 ዓ.ም ድረስ ነው ሙሉ ታሪኩን በዚህ መጽሐፍ ክፍል 1 ከገጽ 38 - 41 ተመልከት፡፡

ግንቦት 25 ቅድስት ሰሎሜ

ሰሎሜ ማለት ሰላማዊት ማለት ነው፡፡ ለእመቤታችን የአክስት ልጅ ናት ማጣት አያቷ ነው፣ ማርያምን ሶፍያንና ሐናን ወልዷል ማርያም ሰሎሜን፣ ሶፍያ ኤልሳቤጥን ሐና እመቤታችንን ወልደዋል፡፡ ነገረ ማርያ ስንክ እመቤታችን የመውለጃዋ ጊዜ ሲደርስ የሴፍ እንትንኝ አዋላጂያት አላት፡፡ ብትመጣ ብዬሀ ሐፃን ታቅፋ አገኘቻት ሕግም ምጥ ሳይሰማሽ ዘሽም የሚደርሰው ሳይደርስብሽ እንዴምን ወለድሽው? አለቻት፡፡ በማይመረመር ግብሁ በድንግልና ፀንሼ በድንግልና እንድወልደው አደረገኝ አለቻት፡፡ ካላሁ አላምንም ብላ ልትዳስሳት እጇን ዘረጋች፣ በእሳት እንደተለበለበ ግንድ ሆና ቀረ፡፡ የጌታዬ እናቱ እመቤቱ በእውነት ትንቢት የተነገረላትን ሰባኤ የቀጠረለትን አላኝ እንደወለድሽ አምኛለሁና ይቅር በይኝ ብላ አለቀሰች እኔንማ ምን አድርገሽኛል? ይልቁንስ የማይመረመር ግብሩን ለመርምር ብለሻልና እርሱን ይቅር በለኝ በይው አለቻት፡፡ እያለቀሰች ለመንቱን ብትዳስሰው ተፈውሳታል፡፡ አመስግናዋለች፡፡

ከዚህ በኋላ እንጨት ሰብራ ውኃ ቀድታ እመቤታችንን እያገለገለች ኖራለች፡፡ በስደቱም ጊዜ ሕፃኑን አዝላ ከርሷ ጋር ተሰዳለች፡፡ "ነበ ሐበሰት በግዕ አልባሲሁ ወአባሉ፡ሊሐፃ ድንግል ገቡ ሰሎሜ ዘተገዝሉ" እንዲል ደራሲ፡፡

ጌታም በመዋዕለ ስብከቱ ከ36ቱ ቅዱሳት አንስት ቀጥራታል፡፡ በስቅለቱ ጊዜ ከእመቤታችን ጋር ከመስቀሉ ሥር ሆና ታለቅስ ነበር፡፡ ዮሐ 19:25 በትንሣኤ ጊዜ በሌሊት ወደመቃብሩ ከሄዱ ሴቶች አንዷ ነበረች፡፡ ከዕርገት በኋላ ከሐዋርያት ሳትለይ ሐዋርያትን በተልእኮ ስታገለግላቸው ኖራ በዚህ ዕለት ዐርፋለች፡፡

ሰላም ለሰሎሜ ከብርት መበዐት
የጌታ አገልጋይ ሐዋርያዊት
ጌታ አምላክ ክርስቶስ እንዳን ለክብር መርጦሽ
በገድሽ ታቀፍሽው አዘልሽው በጀርባሽ
ድንግል ማርያምን የአምላክን እናት
ሊያጽናት ተመኘተው አለም ላያጸናት
በጎንዋ ሆንሽ ያገለገልሻት

ታድለሽ ነው እኮ ተመርጠሽ በእውነት
በግብጽ ጊዜ አዝለሽ ከርሷ ጋራ
ሲጨንቃት ተጨንቀሽ ተሰደሽ መከራ
ድንግል ወለዷ ጭንቅ ስታለቅስ በምር
አብረሽ ተገናኘሽ በመስቀሉ ሥር
ፍቅሯ አንብሮሽ የልጇም ፍቅር

ዮሐ 19 25

ግንቦት 26 ቶማስ ሐዋርያ

ቶማስ ማለት ፀሐይ ማለት ነው፡፡ ቶማሚ ስሙ ዲዲሞስ ነው ዲዲሞስ ማለት ጨለማ ማለት ነው፡፡ ቁጥሩ ከ12 ሐዋርያት ነው፡፡ማቴ 10:3 ዮሐ 20:24 ሐዋ 1:13.

ሰኔ 11 ገላውዴዎስ ሰማዕት

ገላውዴዎስ ማለት ስንቁላዘን ማለት ነው፡፡ ሀገሩ አንጾኪያ ነው፡፡ አባቱ አብጥልማዎስ የንጉሡ ኑማርያኖስ ወንድም ነው፡፡ እንደ የቤቱ አስራኤላዊ መልክና እንደ የፍታሌ እንደ ጊዮርጊስ ኃይለኛ ነበረ፡፡ የሀገሩም ሰዎች ከመውደዳቸው የተነሣ በስሉን ሰለው ከአደባባይ አቁመው ያደንቁለት ነበር፡፡

ንጉሡ ዲዮቅልጥያኖስ ሃይማኖታችሁን ካዱ ለጣኦት ስገዱ እያለ ምእመናንን ሲፈጅ እርሱ ከቅዱስ ፊቅጦር ጋር ለአንባብ መጻሕፍት ይተጋ ነበር፡፡ ሰይጣን ለምቀኛነት አያርፍምና በአምሳለ አረጋዊ መጥቶ ልጆቼ ይህ ንጉሡ ምሕረት የሌለው ጨካኝ እንደሆነ እታውቁምን አሁንም ቢሰማ ይጣላችሁልና መበላችሁ እደሩ አላቸው፡፡ በገሩ ጠላትነቱን አውቀው አ አቡሃ ለሐሰት ሪሁቅ እምኔ ወግድልን አሉት እርሊያውን ለውጦ በአምሳለ ገብር ጸሊም ሆኖ ባማቸሁን አንገኝ ብሏቸው ሄደ ንጉሡን ገላውዴዎስና ፊቅጦር ሳሉ መንግሥትህ ይጸና መሰለሃልን አለው፡፡ ካሉበት አስጠርቶ ሃይማኖታችሁን ካዱ ለጣዖት ስገዱ አላቸው አይሆንም ይሆን እናደርገዋለን አሉት ከዚያ እንዳይቀጣቸው ቢተሰቦቻቸውን ፈርቶ ፊቅጦርን ወደ እስክንድርያ ሰደደው እርሱንም ወደ አንጾኪያ ላከው፡፡

የአንጾኪያው መስፍን አርያኖስ የነው ወንድሜ ንጉሡ የወደደውን ወደህ የጠላውን ጠልተህ በሹመትህ ተደላድለህ አትኖርምን አለው፡፡ አንተ ኢመጻሒ ኅሊና ከመታስሕቲ፣ በቃልከ ወለቲ የመጣህት በሐሰት ቃልህ ልታስተኝ ነውን? አለው፡፡ ለማስፈራራትም ቢሉ ተቆጥቶም ነው ቢሉ የያዘውን ጦር ቢጥልበት ንቱን ወግቶ በሰማዕትነት ዐርፏል፡፡

➢ ሰማዕትነት የተቀበለው በ304 ዓ.ም አካባቢ ነው፡፡

ቅዱስ ገላውዴዎስ የአንጾኪያ ወርቅ
ፊቅጦር ከርስቶስ ሐዋርያ ጸድቅ
... ... መሰለ ሊያስቱህ
... እንዲተው ሊዘርፉህ
መንገድሽ ብሎ በአምላክ ደል ነሥ
ሊቀወ ሊመስለት አሥረው እጆቹን
ሸንገላውን በሞት ቀን ሄደውን
ሳይታለልት ሳይፈሩ ሹሙን

ወዚህ የመጣህት አደራም ለሞኝ
በለሰተኛ ቃልህ እንድታስተኝ
ይላቅ አንተ እንተን በሰይፍ ቀጣኝ
እኔ የክርስቶስ አገልጋይ ነኝ
ብሎ አስመቸቀ በሰው እንተን
ወደ ፈጣሪው ሄደ ናዖቀ መሄደን
ከሰማ ኑሮ ደስቅ ፈተና ከማህን
የሚኖር ነውና ከአምላክ ጋር መሆን

ሰኔ 12 በዓለ ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ.መ

ሀ. ዕረፍታ ለቅድስት አፎምያ

ሀገሯ ኪልቅያ ነው፡፡ ባለቤቷ አስተራኒቆስ ይባላ፣ መስፍነ ኪልቅያ ነበረ፣ ታዋ ዋቶ ከሀብቷ ከንብረቷ እየሰጠች እየመጸወተች በጾም በጸሎት ተወስና ትኖር ነበር፡፡ ሰይጣን ለምቀኝነት አያርፍምና ደግ መነኩሴ መስሎ አጋንንትን መነኮሳይያት አስመስሎ መጥቶ ከደጅ ሆኖ አስጠራት፡፡ ከቤት ገብታችሁ በቅዱስ ሚካኤል ስዕለ ሬት ጸለዩልኝ አለቻቸው እኛማ በነገሁ ጸለየና፣ አንደው አንቺ ግን ይህ ሁሉ ጾም ጸሎት ምን ያደርግልሻል? ሲበላ ያለ ጊዜ እንደሚገድል እታውቂምን ሀብትሽን ለጥተሽ መጨረሻሽስ ለምንድን ነው? በዚያው ላይ አንቺ ስትደክሚ የሚደግፍሽ ስታረጂ የሚጦርሽ ልጅ የለሽም፣ ሁለተኛ ማግባት ኃጢአት መሰሎሻልን? እነ አብርሃም እነ ዳዊት ከብዙ ሴቶቹ ብዙ ልጆች ወልደው የለምን? አሁንም ቤት ሠሪ ጉልት ዘሪ ልጅ ያስፈልግሻልና ባል አግቢ፣ እሺ በይኝ አላት ኦ አባ እስኪማ ውኅይ ወቃልከ አኩይ አባ ቀብሀ መልካም ነበረ ንግግርህ ግን ክፉ ነው አትጥሚ አትጸልዪ ያልከኝ ጌታ ምጽዋት አበድር አመስጥአተ ብሎ የለምን፣ ሁለተኛ ባል አግቢ ማለትንስ ከምን አገኘኸው አርጋብ እንኳ ባሎቻቸው ከሞቱባቸው ከሌላ ወንድ አይቀርቡም ታዲያ ሰንቱን በንጽሕና ሊኖር የተፈጠረ ሰው ሁለተኛ አላገባም ቢል ልብ ፍዳ ሊሆንበት ነውን? ብላ ባሏ ታዋ ሳለ ያሠራላትን ስዕለ ሚካኤል አውጥታ ብታሳየው ሰኔ 12 ቀን መጥቼ ከተመለከትኩ ከዚህ ግብስስ ስዕል ጋር አጠፋሻለሁ ብሏት እንደትቢያ ጠፋ ጠፋ፡፡

ሰኔ 12 ቀን በነገሁ ብርሃናዊ መልአክ መስሎ መጥቶ ጾም ጸሎትሽ ሰማይ ምጽዋትሽ ዐርጉልሻል፣ ያዘዘኝ ሚካኤል በዚያ ዕለት ቅድመ እግዚአብሔር ይቆማልና መጥቼ እጠፋሻለሁ እንዳልሽ እውቀ ላድንሽ መጥቻለሁና ሰገጅልኝ አላት አንተ ማነህ? አለችው

ጌታ ከሙታን ተለይቶ ከተነሣ በኋላ ያየው በሄየው ቀን እሁድ ቢሆን ይመስላሉም በዐር የቀውስ ጉሉን ደለ ነው፡፡___ገጽ ተመልከት የእመቤታችንንም ትንሣኤ ሰርጎቿን አስቀድሞ ያየ እርሱ ነው___ገጽ ተመልከት

ሀገረ ስብከቱ ሕንደኬ ነው፡፡ ለምክንያት ይሁንኝ ብሎ በ30 ብር ተሾጦ ከመስፍን ብሔሩ ከሉክዮስ ቤት እያገለገለ ይኖር ነበር፡፡ ምን ምን መሥራት ትችላለህ? አለው፡፡ ሕንፃ ማነጽ ሐውልት መቅረጽ እችላለሁ አለው እንኪያስ ሥርተህ ቆየኝ ብሎ ብዙ ብዙ ወርቅና ብር ሠጥቶት አሕዛብ ምክሆን ናቸውና እንዲህ ያለ ጠቢብ እገኝ ለማለት ወደ ንጉሡ ሄደ፡፡ እሱም ሕንጻ ማነጽ ሐውልት መቅረጽ ከዚህ የበለጠ አለን ብሎ ለነዳያን መጸወተው፡፡ ከዚያውም ዘንድ አስተምሮ አሳምኗቸዋል፡፡ የሉክዮስም ሚስት አርሶንዋ ከልጆቿ ከአገልጋዮቿ አምና ተጠምቃለች፡፡

ሉክዮስ ከሄደበት ሲመለስ ያነጽከው ሕንጻ የቀረጽከው ሐውልት ወዴት አለ? አለው በወርቅና በብርህ ያነጽኳቸው ሕንጻዎች እኒህ ናቸው ብሎ ያመኑትን ደኃዎቹን አሳየው ይህ ከፉ ባሪያ ተጫወተብኝ ብሎ እጅ እግሩን አሥሮ ቆዳውን አስገፍፎ ስልቻ አስፍቶ በእሸዋ መልቶ አሸክሞ ገበያ ለገበያ ሲያዞረው ሚስቱ አርሶንዋ አይታ በድንጋጤ ወድቃ ሞተች፡፡ ሚስቴ የሞተች ባንተ ምክንያት አይደለምን ካዳንካት እኔም በአምላክህ አምናለሁ አለው፡፡ ጌታ ቁስሉን እንደ ውኃ አቀዝቅዞለት ካስችለት ሄዶ ስልቻውን ቢያለብሳት ተነሥታለች በዚህም ሉክዮስ አምኖ ተጠምቋል፡፡

ከዚህ በኋላ ስልቻውን ተሸክሞ ከቦታ ወደ ቦታ እየተዘዋወረ ሙት እያነሣ ደውይ እየፈወሰ አሕዛብን አሳምኖ አጠመቀ፡፡ ቀንጦፍያ ሲደርስ አንድ ሹማምል ሰባት ልጆቹን ገድለውበት ሲያዝን አግኝቶ ስልቻውን አያስነካ ሰባቱን አስነሥቶለታል፡፡ በኢናስም የቃሉን ትምህርት የእጁን ተአምራት አይተው ከንጉሡ ሚስት ከንግሥቲቱ ጀምሮ እስከ ተራ ገበር ድረስ ያሉት ሁሉ አምነው ተጠመቁ፡፡ ኋላ ግን ካህናተ ጣዖቱ ጥቅም የሚቀርባቸው ቢሆን በተንኮል ከንጉሡና ከመኳንንቱ አጣልተው በዚህ ዕለት አንገቱን በሰይፍ አስመትተውታል፡፡

➢ ሰማዕትነት የተቀበለው በ 72 ዓ.ም ነው

ንዑድ ክቡር ሰው ነው ቶማስ የኛ አባት
[illegible] የዳሰሰ የአምላኩን ጎን
ዘመዱ ወዳጁ ሲሆን አምላካው
እንዴምን በሰው ላይ ይጨክናል ሰው?
አምላክ ክርስቶስን ቢሰብኩላቸው
ልቡ ከፉታቸው መጨከናቸው
ስልቻ አደረጉት ቆዳውን ገፈው
የቆሰለው ሥጋው በጨው ታጥቦ ታሽቶ

የቆዳው ስልቻም በአሸዋ ተሞልቶ
ተሸክሞ ሲዞር በመከራው ብዛት
ከፊቱን መሸከሩ ስልቻውን ከነቱ
የሞተው ተነሥቶ ንግሥቲቱም ቆንጆ
ስትወለድ በምስሏ እንደ አለቅሳ ሴት
ከመሰደች ኋላ ደስ እንደሚሉት
ጻድቅም ለለቆይቅ የሚሞተው ሞት
የዛሬ ደስታን ያስገኛል ሕይወት

ዮሐ 16 21

ምዕራፍ 4

ሰኔ 9 ሳሙኤል ነቢይ

ሳሙኤል ማለት ሰምዐኒ እግዚአብሔር ማለት ነው፡፡ 1ሳሙ 1:20 አንድም ካህን ተሰማኢ ማለት ነው፡፡ 1ሳሙ 2:35 ትውልዱ ከነገደ ኤፍሬም ነው፣ አባቱ ሕልቃና እናቱ ሐና ይባላሉ የተወለደው የአርማቴም ልጅ በሆነች በመሴፋ ሲሆን የብፅዓት ልጅ ነው፡፡ ጡት ሲተው እናቱ አፋ እህል ሳይለምድ ሆዱ ዘመድ ሳይወድ ወስዳ ለቤተእግዚአብሔር ሠጥታዋለች፡፡

ሊቀካህናቱ ዔሊ ካህናቱ አፍኒን ፊንሐስ ይባላሉ፡፡ አፍኒን ፊንሐስ ጽኑእ ምግባር ነበሩ ጌታ ዔሊን ልጆችህን ሥራ ቅጣ አለው፡፡ እነሱ ተመክረው የማይመለሱ፣ ዔሊም ከእግዚአብሔር ይልቅ ለልጆቹ አድልቶ ከሹመታቸው ለሻሬቸው ከመገርጋቸው ዓዋርዳቸው የማይል ቢሆን ጌታ አስቀድሞ ለሳሙኤል በራዕይ አስታውቆ ቀጣውን በሞተ እስራኤል ጀምር ዉኤዋ ጽዮን፣ በሞተ አፍኒን ፊንሐስ ጀምር በሞተ ዔሊ ፈጽሞ ሳሙኤልን ሊቀካህናት አድርጉ ሾመው፡፡

ከሁት ከምስና አንድ አድርጉ ይዞ 40 ዘመን አስተዳድሮቸው አረጀ፡፡ ኢዩ ኤል አብያ የሚባሉ ሁለት ልጆች ነበሩት፡፡ ካህናት አድርጉ ሾማቸው፡፡ ደኃ የሚበድሉ ፍርድ የሚያጓድሉ ቢሆን እስራኤል "አንተሰ ልሁቀ ከመ ኢትመግቦ ወደቂቅከኒ ኢሖሩ በፍኖትከ" አንተ እንዳታስተዳድረን አረጀህ ሸመገልህ፣ ልጆችህም አመርህን አልተከተሉም በዚያውም ላይ በኢያቢስ ዘገለዓድ ባሉ 2 ነገድ ተኩል ወንድሞቻችን ናዖስ አምናዊ ተነ ተነ ዓይናቸውን ገብሩልን ይላልና ቅን ፍርድ የሚፈርድልን ከጠላት የሚታደገን ንጉሥ አንግሥልን አሉት ጌታ ከሙሴ ጀምሮ እስከአሁን ድረስ ካህናትን መሳፍንትን አስነሣ እንጂ እንደ አሕዛብ ንጉሥ እንገሥላችኋለን ተው አይሆንም አላቸው ጌታ "ስምዖሙ ቃሎሙ ዘይቤሉከ ሰማቸው" አለው ፡፡ ሳኦል ወልደቂስን ቀብቶ አንግሥላቸዋለ፡፡ ለእርሱም እንዲገዙ ሥርዓት ሠርቶላቸዋል፡፡ ኋላም ሳኦል ቢበድል የዕሴይ ልጅ ዳዊትን ቀብቶ አንግሥላቸዋለ፡፡ ዳዊትን ከቀባ በኋላ ጥቂት ጊዜ ቆይቶ በዚህ ዕለት ዐርፏል፡፡

➢ የዐረፈው ከ በ1100 ዓ.ዓ ገደማ ነው፡፡

ሊቀመላእክት ሚካኤል ነኝ አላት፡፡ የንጉሥ መልእክተኛ ያለማኅተም ይላካልን? በትረ መስቀል ወዴት አለ? አለችው፡፡ መስቀል አሊሥ መሳል ልማድ ነው እንጂ እኛስ አንይዝም አላት ቆየኝ ስዕሉን ላምጣሀ ብላ ዘውር ስትል እርሊያውን ለውጦ ደብረ ጸልመት መስሎ አነቃት ቅዱስ ሚካኤል እንደ ዓይን ጥቅሻ ፈጥኖ ደርሶ ቀጥቶ አምሎ ገዞተ እመቀ እመቅ ጥሎታል፡፡ አሊንም ብፅዕት ሆይ ጾም ጸሎትሽ ሰገድ ምጽዋትሽ ቅድመ እግዚአብሔር ደርሶልሻል ዕረፍትሽ ዛሬ ነው ብሏት ዐረገ፡፡

ወደ ቤተክርስቲያን ሄዳ ሥጋውን ደሙን ተቀብላ ጳጳሱን ካህናቱን ወደ ቤቷ ጠርታ ተመለሰች ጳጳሱን በወርቅ ካህናቱን እንደመዓረጋቸው በብር በናስ መንበር አስቀምጣ አብልታ አጠጥታ ወርቅ ብሯን ለቤተክርስቲያን መሥራፍና ለድሆች ምጽዋት ያደርገው ዘንድ ለጳጳሱ ሠጥታ ዐርፋለች፡፡ ስዕሉም ከእቅፏ ወጥቶ በር በር ያሳንዳች መስቀያ በቤተመቅደሱ በር ተሰቅሉ ተገኝቷል፡፡ ኋላም አብቦ አፍርቶ በአበባው በፍሬው ሕሙማንን የሚፈውስ ሆኗል፡፡

ቅድስት አፎምያ በሥጋሽ አንቺ
በሙ በትፋፋት ለይጣን ድል ነሺ
... ... ተቀዳጅ
... በመስፈች የልብት ትምህርት
መምህር ሳለሆን መስሉ ሰውን ከሚያስት
... ... ጠፋት
... አንዳንዱ ... ...

እርሱ መሆኑ ቢሆን ጀምር ከጎንት
የዘፍት መጋረጃ የልዑት አምት
... ...
... ...
... ...
... ...
... ...

ዮሐ 8:44 ኤፌ 6:11 ያዕ 4:8

ለ. ዘተፈነወ ኀበ ባሕራን

ሀገሩ እስክንድርያ ነው በዘመን በጥሊሞስ ልጁ አክሉብጥራ በግብጽ ሽላ በሚባል ከቡብ ሰም ቤተ ጣዖት አሥርቶ ሕዝቡ በየዓመቱ መሥዋዕት እየሠዉ ተረፈ መሥዋዕቱን እየተመገቡ እየዘፈኑ እያጨበጨቡ ያከብሩ ነበር፡፡ ሊቀ ጳጳሳት አባ እለክሳንድሮስ ንጉሡ ቆስጠንጢኖስ «አብያተ ጣዖታት ይትዐጸዋ አብያተክርስቲያናት ይትረኃዋ» ብሎ ካወጀ በኋላ አፍርሶ ከቦታው ላይ ቤተክርስቲያን ሠርቶ ታቦተ ሚካኤልን አግብቶ የጣዖቱን በዓል

ተው ይህን አከብሩ ብሎ በየዓመቱ በዚህ ቀን በዓል እንዲሆን ሥርዓት ሠራላቸው፡፡

ይህንንም በዓል ከሚያከብሩ ምእመናንን አንዱ የዚህ የባሕራን አባት ነበር፡፡ ተፀንሶ ሳለ ሞተ በተወለደ ጊዜ መላእክት ቅዱስ ሚካኤል ቅዱስ ገብርኤል ከቤቷ ገብተው ሕፃኑን ባርከው ይህ ሕፃን የዚህን ባለጸጋ ሀብት ይወርሳል ሲሏት ባለጸጋው ጎረቤቷ ሰማ፡፡ ነገሩን ከልቡ ሲያወጣ ሲያወርድ ኖሮ ሕፃኑ አሥር ዓመት ሲሆነው እናቱ ቀዳ የምታለብሰው ቆርሳ የምታጉርሰው አጥታ ስትቸገር ለርሷ ሃያ ወቄት ሠጥቶ ሕፃኑን ላሳድገው ብሎ ከቤቱ ወሰደው፡፡ ወዲያውም በሣጥን ከቶ ከባሕር ጣለው ማዕበል እየገፋ ወስዶ ከወደብ አደረሰው፡፡ አንድ በግ ጠባቂ አገኝቶ ወርቅ መስሎት ከቤቱ ወስዶ ቢከፍተው መልካም ብላቴና ሆኖ አገኘ፡፡ ልጅ ይሻ ነበርና ደስ አለው ከበላው እያበላ ከጠጣው እያጠጣ አሳደገው፡፡

ከብዙ ዓመታት በኋላ ያ ባለጸጋ ለንግድ ሲሄድ መሽቶበት ከዚሁ ቤት አደረ፡፡ ባሕራን ባሕራን እያለ ሲጠራው ሰምቶ ባሕራን ምን ማለቱ ነው? አለው ከባሕር የተገኘ ማለት ነው አለው፡፡ መቼ አገኘኸው አለው፣ ጊዜውን ጠቅሶ ሲነግረው ለካ አልሞተምና አለ፡፡ ሲነጋ ከቤቱ የረሳሁት አለና የድካሙን ዋጋ ላንተ እከፍላለሁ ልጅህን ልላከው? አለው እሺ አለ፡፡ «እንደደረሰ ግደሉት» ብሎ ጽፎ አትሞ ምልክት ነገር ሰንቆን እሲያ ወሰአም በጉሕሉት ከመ ይሁዳ ይላል እንደይሁዳ በሸንገላ ስሞ ሰደደው፡፡

ዘጠኝ ቀን ተጉዞ የአንድ ቀን ጎዳና ሲቀረው ቅዱስ ሚካኤል በአምሳለ ሊቀሐራ በፈረስ ተቀምጦ መላእክትን እንደ ሠራዊት አስከትሎ ከመንገድ ተገናኘው፡፡ አንተ ጉብዝ ወዴት ትሄዳለህ? አለው እንዲህ ካለ ቦታ መልእክት ላደርስ ተልኬ እሄዳለሁ አለው፡፡ እስኪ መልእክቱን አሳየኝ አለው ጌታዬ ለማንም እንዳታሳይ ብሎኛል አለ፡፡ ያም ባይሆን እንደተጠቀለለ አሳየኝ አለው፡፡ አሳየው ወመልአክስ ነፍሀ ውእተ ክርታስ ወደምሰሰ ኩሉ ዘጽሑፍ ውስተ ውእቱ ክርታስ ይላል እፍ ቢልበት የሞቱን ትእዛዝ አጥፍቶ የሕይወት ትእዛዝ ጽፎበታል፡፡ ያን ይዞ ሄዶ ለቤቱ ሹም ሰጠው ቢገልጸው ልጁን ዳሩለት ሀብት ንብረቱን አውርሱት ባሮቹ ይገዙለት የሚል አገኘ፡፡ በጌታው ማንገተም ታትሟልና እንዲሁ አደረጉለት፡፡

ባለጸጋው ከንግድ ሲመለስ የዘፈን የጨዋታ ድምጽ ሰምቶ ብላቴናውን አግኝቶ ይህ ሁሉ ዘፈን ጨዋታ ምን ተገኝቷል? አለው:: የላከኸው ሰው ልጅህን አግብቶ ሀብትህን ወርሶ ይኸው አርባ ቀን ሙሉ ይዘፍናል አለው:: ደንግጦ ከፈረሱ ወድቆ ሞቷል:: ባለራንም ይህ ሁሉ በቅዱስ ሚካኤል ረዳኢነት የተደረገለት መሆኑን በራዕይ ተረድቶ አምና መንገሩ ቅጽና ተቿቸሉ ቤተክርስቲያን አሳንጾ ሲያገለግለው ኖሯል::

[illegible]

ሰ. ቅዱስ ላሊበላ /ከ1180 - 1207 ዓ.ም/

ላሊበላ ማለት ንህብ አእመረ ጸጋው ማለት ነው:: በተወለደ ጊዜ ቤቱ በንብ ተከቦ ነበርና ሀገሩ ርግ ነው እባቱ ሸን ሥቶም ይባላል:: ትውልዱ ከዛግዌ ነገሥት ነው:: ያግሬ የተዋበ መልክ መልካም ነበረና ያለፈ ያገደመው የመጣ የወረደው ሁሉ ይህንን ያንገሠው ይሉ ነበር:: ንጉሡ ሐርብይ /ሐርቤ/ /ገብረ ማርያም/ ይህን ሲሰማ ታናሽ ወንድሙ ቢሆንም ንጉሥ በመንግሥቱ ቢነሣበት አይወድምና እንግዲህም መንግሥቱን ሊነጥቀኝ አይደለም ብሎ ይመቀኘው ጀመረ:: ይልቁንም ንብ የከፉ ክፉ እኅት ነበረችው:: ሆዱን በጥብጦ እንጀቱን ቆራርጦ ይገድለው ብላ መርዝ በጽዋ ሞልታ ላከችበት:: ተልኮ ያመጣው ዲያቆን ተሞክሮ እቀምሰው ብሎ ቢቀምሰው ጠምሟ ብሎ ሞቷል:: የሚንከባከበውም ውሻው ሲያየው ቢቀምሰው ሞቷል:: የተላከውን ልሰ ሞተ እርሱም ይህ ሁሉ የሆነ በኔ ምክንያት ነው:: ወዳጄ ሞቶ እኔ እቀራለሁን ብሎ የተረፈውን ጨለጠው ቅዱስ ገብርኤል ነፍሱን ከሥጋው ለይቶ ከጌታ ፊት አደረሰው:: የመላእክትን ምስጋና ሰምቶ ከነቢያት ጋር ብሩር በመደድ ነበር አለ:: በግብር አምላካዊ የተሠሩ ሥራዎች የሆኑ በዓታትን አሳይቶ እንዲህ ያሉ በሚ የሚቀደሱባቸውን ማደሪያዎቹን ብታሠራ ክብርህ ከክብራቸው ምስጋናህ ከምስጋናቸው አንድ ይሆናል አለው::

ከዚህ በኋላ ከሥቃዩን ኀቡዓቱን ሁሉ ሲያሳየው ቆይቶ በሰስተኛው ቀን ወደ ሥጋው መለሰው ከእንቅልፍ እንደሚነቃ ሰው እፈፍ ብሎ ተነሣ::

ሙቶት ሳይለይህ አይሆንም ብለን እንጂ ፕነዘን ልንቀብርህ ነበር፤ ወዴት ቆይተህ መጣህ? አሉት:: እስመ ፍቅር ከሞት ጽንዕት / / ፍቅር /እንደ/ እስከ ሞት የጸናች እንደሆነች አታውቁምን? የወዳጄ ፍቅር አገብርኝ ከደረሰበት ደርሼ መጣሁ አላቸው:: የበለጠ የሚጠሉት የሚቃወሙት ሆነዋል::

ወንድሜ ተፋቴን እንቴ ሞቴን ከተመኘልኝ ከእንግዲህ ከዚህ ምን ያስቀምጠኛል? ብሎ ከሰው ጋር ከመኖር ከአራዊት ጋር መኖርን መርጦ በረሀ ገብቶ በዓት ሠርቶ ተቀመጠ:: እንዲህ ሆኖ ሲኖር የታዘዘ መልአክ ነገ በዚህ ጊዜ እንዲህ ያለች ብላቴና ትመጣለችና እንዲህ በላት አለው ከሴት ርቄ ንጽሕ ጠብቄ እኖራለሁ እንጂ ይህንንስ አላደርገውም አለ፤ የፈጣሪህን ፈቃድ መተላለፍ ይቻልሀልን? አለው እሺ አለ::

በማግሥቱ ባለው ጊዜ መስቀል ክብራ እንጨት እየለቃቀመች ካጠገቡ ደረሰች:: መልአኩ እንዲህ ብሎ ሰላንቺ ነገረኝ አላት:: ሄዳ ለአባቷ ነገረች:: ጥሪው አላት ጠርታ አመጣችው የመልኩን ቀናነት የቃሉን ጥዑምነት አይቶ ለዚህስ ሊድሩለት ይገባል ብሎ ድሮለታል::

ከዚህ በኋላ እንደ አብርሃም እንደ ሳራ ተዋደው ለበጎ ምግባር ተግተው የሚኖሩ ቢሆኑ ሰይጣን ለምቀኝነት አያርፍምና በግዕተ ሐሰት አስነስቶ ለባል የታጨቻቸውን ሴት ግድ ብሎ አገባት ብሎ ከንጉሥ አስከሰሰው:: ንጉሡ አስጠርቶ አርባ አስገረፈው::

ከቤት ሲገባ መስቀል ክብራ ወንድሜ ንጉሥ በሰላም ነው ያስጠራህ? አለችው፤ እኔማ ከሰው ጋር ከመኖር ከአራዊት ጋር መኖር ይሻለኛል ብዬ በረሀ ወድቄ አልነበረምን እንግዲህም ከዚያው እኖራለሁ እንጂ ከሰው ጋር አልሆንም፤ ከወደደሽ ተከተይኝ አላት ተከትላቸው በረሀ ገብተው በዓት ሠርተው ተቀመጡ:: ንጉሥ ሠራዊቱን ልኮ ያስፈልገው ጀመር:: ጠባቂ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል መጥቶ ኢየሩሳሌም ሄደህ ቅዱሳት መካናትን እጅ ነሥተህ ትመለሳለህ አለው፤ ይህችስ እንቴ እንደምን ትሆናለች አለ:: ለርሷስ ሚካኤል እሰላት ብሎ በአምሳለ ወሬዛ ሆኖ እየመራ

ወሰደው መስቀል ክብራንም ቅዱስ ሚካኤል በአምሳለ ወሬዛ መንገድ አርአያሁ ሆኖ ከሴቶች ገዳም ወስዶ አደራ ሰጣት::

ላሊበላም ቅዱስ ገብርኤልን እየተከተለ ሲሄድ ደከሞት አረፍ ካለበት በክንፉ ነቶተህ ሰማየ ሰማያት እንዳደረሰኸኝ በክንፉህ ነቶተህ ኢየሩሳሌም አታደርሰኝምን አለው:: ክብር የክብር ክብር እንድታገኝበት ብዬ እንጂ ነው ብሎ በክንፉ ነቶቶ አደረሰው:: ቅዱሳት መካናትን አይቶ እጅ ነሥቶ በጣም የርዳኖስ ተጠምቆ ሲደሰት ጌታ በብሩህ ደመና ተገለጸ ክብርህ መንግሥትን ለመስጠት ዓለምን ከሥሩ ከኢትዮጵያ ከላውሎስ የተባለ ይሁን፤ በተከፋህ የጸናውን ቢክዳህ የተማከሩውን ከሞት ነፍስ ከርደት ዝንም አድንልሃለሁ፤ መቃብርህን እጅ የነሣ ኀላኅታ መቃብሬን እጅ እንደነሣ ይሆንለታል፤ ብሎ ቃል ኪዳን ገብቶለታል:: ከዚህም በኋላ ቅዱስ ገብርኤል በክንፉ ነቶቶ መስቀል ክብራ ካለችበት አደረሰው::

በዚያ ሌሊት ጌታ ንጉሡን መንግሥትህን ለወንድምህ ስተተህ ብለዕት ንስፈት የሌለበትን ሰማያዊ መንግሥት ፈልግ አለው:: መንግሥቱን ለላሊበላ ለቆ በረሀ ወድቆ ከፍጹምነት ደረሰ ገድሏል::

እሱም መንግሥቱን ከያዘ በኋላ በየሀገሩ ብዙ አብያተ ክርስቲያናት አሠርቷል:: በከተማውም ላይ 11 አቢያተ ክርስቲያናት ከቋጥኝ አስፈልፍሎ አሠርቷል:: ሲሠራም ፈቃደ እግዚአብሔር እንደሆነ ለማጠየቅ አንድ ክንድ ያህል ተቀርጾ ያደረው በማግሥቱ 2 ክንድ ያህል ሆኖ ይገኝ ነበር:: አብያተ ክርስቲያናቱም

1. ቤተ አማኑኤል
2. ቤተ መድኃኔዓለም
3. ቤተ ማርያም
4. ቤተ ሚካኤል
5. ቤተ ገብርኤል
6. ቤተ መስቀል
7. ቤተ ጎልጎታ
8. ቤተ ጊዮርጊስ
9. ቤተ መርቆሬዎስ
10. ቤተ ሊባኖስ
11. ቤተ ደናግል ናቸው::

እንዲህ አብያተ ክርስቲያናት ሲሠራ እጥቶ እስከ መቸገር ደርሶ ገንዘቡን ሲድኃ ሲመጸውት ለጸሎት ሲተጋ ኖሮ በዚሁ ዕለት በክብር ዐርፏል::አለመከሩን የሚበላ ልጅ የበረው ቢሆንም መንግሥቱን የወረሰው ግን የወንድሙ ልጅ ነአኩቶ ለአብ ነው::

[illegible]

ሉቃ 4. 1ማቴ 25፤ 40 ያዕ 2.16

ሰኔ 17 አባ ገሪማ ዘመደራ

ቀዳሚ ስማቸው ይስሐቅ ነው አባታቸው ሰናንያስ ንጉሥ ሮም ነበር:: ከልጅነታቸው ጀምረው መንፈሳዊ ትምህርት ሲማሩ በዲቁናና በቅስና ቤተክርስቲያንን ሲያገለግሉ አድገዋል፤ አባታቸውም የአባታቸውን መንግሥት ወርሰው ሰባት ዓመት ገዝተዋል::

ከዚህ በኋላ አባ ጰንጠሌዎን ዘማኅበት ምድራዊ መንግሥት ያልፋ ይጠፋ የለምን? የማያልፈውን ሰማያዊ መንግሥት ትወርስ ዘንድ ፈጥነህ ወደእኔ ና ብለው ላኩባቸው ቅዱስ ገብርኤል በክንፉ ነቶቶ እስከም አድርሷቸው ተገኙ መግርግ ምንኩስና ተቀብለው በጾም በጸሎት ተወስነው ይኖሩ ጀመር ሥጋቸው አልቆ አጥንታቸው እስኪቆጠር ድረስ ነበር:: ሲጸልዩም ለምላቸው ከጉንጫቸው እስኪያልፍ ድረስ አብዝተው ይሰግዱ ነበር::

እንድ ቀን መቃኑናቸውን ተተብለው ከወንድሞች ጋራ ወደ መንገድ ሲሄዱ ቤተክርስቲያን አግኝተው እጅ ሲነሡ ካህናቱ እየተቻኮሉ መጥተው ቅዳሴ ሊታጎልብን ነውና ከእናንተ የሚያውቀው አንድ ሰው ይርዳን አሏቸው ሌሎቹ መነኮሳቶቹን ተመልከው ነበርና እንችልም አሉ፤ እሳቸው ጠቅለለው የያዙት መጽሐፍቸውን ከቅጽሩ አስቀምጠው ገብተው ቀድሰውላቸዋል:: እኒያም በላተው የቀደሱ መጽሐፍቸው ለአባ ጰንጠሌዎን ነገሩ:: እርሳቸውም ቢጠሩ መነኮሳቱን አድርጋችሁ ከሆነ እንዳያዩ ተቂት አልፍ በሉ አሏቸው:: አባ ገሪማ ይህን አውቀው ጎርጎስ ሰብአ ዕጣኒ ይሰበሰብ ሰማታቸው ይስበስሉ ለኝ እንጨቶችና ደንጊያዎችም ይመጉልኝ እንጂ አሉ:: በዙርያቸው የነበሩ እንጨቶችና ደንጊያዎች ሰባት ምዕራፍ ያህል ሸሽተዋል:: «አምላክ ዕብዞ መናይ ወእምነ ገሩም ቃሉ፤ አለማ ተገብሮ ወዕመ ለበሉ» እንዲል እርኬ:: አባ ጰንጠሌዎን ያዩት የሰሙት ሁሉ ደንቋቸው ገሩም ገሩም ገሪማ ገሪማኪ ኦ ወልድየ ይስሐቅ ገሩም ድንቅ ልጄ ይስሐቅ አስገረምከኝ /አስደነቅከኝ/ አሉ:: ገሪማ የተባሉት ከዚህ በኋላ መነኮሳቱም አጥፍተናል ብለው ይቅርታ ጠይቀዋል::

ከዚህ በኋላ መደራ ገብተው በዓት ሠርተው 23 ዓመት በትኅርምት ኖረዋል:: ጌታም ልዩ ሀብት ነቢረ

ተአምራት ሠርቷቸዋል:: በንገሀ ስንዴ ዘርተው ዕለቱን ለመሥዋዕት አድርሰዋል:: ከመሥዋዕትነት የተረፈውንም በጠፍጣፉ ደንጊያ ቢወቅጡት 77 ቁና ዱቄት ሆኖላቸዋል:: በኋላም ደንጊያ ላይም ወይን ተክለው አብቅለዋል:: እንድ ቀንም መጽሐፍ ሲጽፉ ውለው የጀመሩትን ሳይፈጽሙ ፀሐይ ልትገባ ስታቆለቁል ጸልየው የጀመሩትን እስኪፈጽሙ ድረስ ባለችበት እንድትቆይ አድርገዋል:: የሚጽፉበትም ብዕር ከእጃቸው ቢወድቅ ወዲያው አብቦ አፍርቶ ተገኝቷል::

ከዚህም የበዙ ተአምራትን ሲያደርጉ ኖረው በዚህ ዕለት በሠረገላ ብርሃን ተሠውረዋል:: ወደ ኢትዮጵያ የመጡት በ480 ዓ.ም ነው::

[illegible]

ማቴ 19፡20

ሰኔ 20 ሕንጸተ ቤታ ለእግዝእትነ

እመቤታችን ባረገች በ4 ዓመት ሳውሎስና በርናባስ ፊልጵስዩስ ገብተው አስተማሩ፤ ሕዝቡም አምነው ተጠምቁ እንግዲህ ወደ ቤተ ማርያም እትሐሉ እኛቸው የለመድነውን ከዝለከሐቸሁንማ ሙከ ጸሎት ሰጡን አሏቸው:: እንዲህ ብንላቸው እንዲሁ አሉን ብለው ወደ ጴጥሮስና ዮሐንስ ላኩ አልዐ በትንብሩ ወልጵንተኒ ዘእንበለ ትእዛዝ ወምክሩ ለእግዚእን ኢየሱስ ክርስቶስ ያለጌታችን ፈቃድ እንዳች ልታደርጉ አይገባም እናንተም ጸልዩ እኛም እንጸልያለን ብለው ላኩባቸው:: ሰባቱ ሰዉርሱ በዚህ ዕለት ጌታ በሩቅም በቅርብም ያሉ ደቀመዛሙርቱን በደመና ጠቅሎ ፊልጵስዩስ ሰብስባቸው:: ዮሐንስ ጌታዬ ለምን ሰበሰብከን ብሎ ጠየቀ ጌታም በእናቴ ስም ጽንፍ እስከ ጽንፍ አብያተ ክርስቲያናት

እንዲታነጹ ፈቃዴ ነውና ሕንጸ ቤተክርስቲያን ላሳያችሁ ሥርዓት ላስተምራችሁ ነው አለው::

ይህንን ብሎ ወደ ምስራቅ ወስዷቸው ተራርቀው የነበሩ 3 ደንጊያዎች ነበሩ፤ በተአምራት አቀራርቦ ቁመቱን ወርዱን መጥኖ ሠጣቸው ወእስብከኒ ይለመልሙ ይላል እሳት እንዳየው ሰም ከእጃቸው እየለመለሙ /እየተሳቡ/ ቁመቱን 24 ወርዱን 12 ክንድ አድርገው ሠርተውታል:: ወይእዜኒ እንተሙኒ ከመዝ ግበሩ እንግዲህ እናንተም እንዲህ እደርጋችሁ ሥሩ ብሏቸው ዐረገ::

በማግሥቱ እመቤታችንን መንበር ጴጥሮስን ተራዳኢ ካህን አስጢፋኖስን ሠራዒ ዲያቆን አድርጐ ቀድሶ አቁርቧቸዋል:: ዳግመኛም ወእርእሶ ለጴጥሮስ ይላል ጴጥሮስን እጁን ጭኖ ፓትርያርክ አድርጎ ሾሞታል:: በዚህም ጊዜ ሰማያውያን መላእክት ምድራውያን ሐዋርያት አንድ ሆነው አመስግነዋል:: «በሠ

ላብ አዕባን ዝሕ ሥላሴሁ ለአምር፤ ሐኒጸ ቤትከ ድንግል ድንገሌ ፈጸመ ሚርር፤ እመ ወረደ ለበዓል ምስሌከ በአንብር፤ እንዘ ይብላ ቃለ ለዘምር አዑል ቀደሰ ማኅደር፤ ደናግል ለጽጌከ ዘበጣ ከበር» እንዲል አርኬ፤

➢ ታሪኩ የተፈጸመው በ53 ዓ.ም ነው

ሰ. ኤልሳዕ ነቢይ /ከ852 – 798 ዓ.ዓ/

ኤልሳዕ ማለት ፀቃቤ ሀገር ማለት ነው ትውልዱ ከነገደ ይሳኮር ነው፤ አባቱ የሳፍጥ ይባላል 1ኛ ነገ 19፡16

መምህሩ ኤልያስ ከርሱ የሚለይበት ጊዜ ሲደርስ ካንተ ሳልወሰድ የምትሻውን ለምን ብሎት ባንተ ያደረ መንፈስ እግዚአብሔር በኔ እጽፍ ድርብ ይሁን ብሎ ለምኖ አድርጎለታል:: ይህም ሊታወቅ ኤልያስ አንድ ሙት ቢያስነሣ እርሱ 2 ሙታን አስነሥቷል ኤልያስ 1 ጊዜ ዮርዳኖስን ከፍሎ ቢሻገር እርሱ 2 ጊዜ ከፍሎ ተሻግሯል::

መምህሩን ሸኝቶ ዮርዳኖስን ተሻግሮ ሲመለስ ኢያርኮ ከከተማ ገብቶ ሠናይ ንብረታ ለዛቲ ሀገር በዚህች ቦታ መኖር መልካም ነው አሉ:: ሊቀበሉት የመጡ ደቂቀ ነቢያት ውሃ ብሎልስ እኩይ ውእቱ ውኃው ግን ወላድ የሚያመክን መካን የሚገድል ክፉ መራራ

ነው አሉት:: በአዲስ ሸክላ ጨው አምጡልኝ አላቸው:: አመጡለት ከምንጩ ላይ አድርጎ ከመ ይቤ እግዚአብሔር አምላከ እስራኤል ዘይመውት እምኔሁ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ከርሱ የሚሞት የሚዋጥም እንዳይኖር ይህ ውኃ ይፈወስ ብሎ ቢጸልይበት ምሬቱ ጠፍቶ ጣፋጭ ሆኗል ምሳሌነቱን ከዘመን ሰብከት ታሪክ ተመልከት::

ከዚያ አልፎ ቤቴል ሲደርስ ሕፃናት ዕርግ በራህ ውጣ መላጣ እያሉ ዘበቱበት 2 ድቦች አስነስቶ 42ቱን አስፈጅቶ 2 ነገ 21-25

በቀርሜሎስ ሳለ እንዲት ሴት መጥታ ነቢየ እግዚአብሔር ባሌ ሞቶ ባለ ዕዳ ልጆን ሊነጥቀኝ ነው ብላ ደረሰት ዘንድ ተማጸነችው ከቤትሽ ምን አለ? አላት ጥርኝ ዘይት አለችኝ አለችው:: ከባልንጀሮችሽ ግድጓ ተውሰሽ መጥው አላት:: ሰበት አራት ግድጓ ተውሳ ጠብ ጠብ ብታደርጋቸው በዘይት ተሞልተው ተገኙ:: ይህን ሽጠሽ ዕዳሽን ከፈዪ የተረፈውን ተመገቢ ብሏታል:: 2 ነገ

በምቶተ ሱናም በሚያልፍም ጊዜ በእንግድነት የምትቀበለው እንዲት ሱናማዊት ነበረች፤ ማረፊያ በሰገነት ሠርታለታለች:: እንድ ቀን ደቀመዝሙሩ ግያዝን ምን እናድርግላት? አለው:: እርሱም ልጅ ስለሌላት ታዝናለች ይሆናል አለ:: አስጠርቶ የዛሬ ዓመት እንደዛሬ ሕፃን ትታቀፊያለሽ አላት እንዳላትም በዓመቱ ወንድ ልጅ ወለደች:: ሕፃኑ ባደገ ጊዜ አባቱን ተከትሎ መስክ ወጥቶ ሳለ ድንገት ሞተ:: ሄዳ በውኑ ትውልዳ ያለሽ ብትለኝ እንጂ እኔ ለምኜ ነበርን? ብላ አለቀሰችበት ቢሄድ ከአልጋው ተኝቶ አገኘው:: እጁን ከእጁ አፉን ከአፉ ገጥሞ እየወደቀ እየተነሣ ሲጸልይ በሰባተኛው ተንሥቶላታል:: 2 ነገ 4:25-37

ከዚህ በኋላ ዘመን ረሀብ ሆኖ ደቂቀ ነቢያት ወደርሱ ተሰበሰቡ:: ደቀመዝሙሩ ግያዝን ትልቁ ለቅመህ ቀቅለህ ስጣቸው አለው:: እርሱም ሳይመርጥ ያገኘውን ሁሉ ቀቅሎ ሠጣቸው:: ቀምሰው ቢመርራቸው እምነ ዓቲ ለልአኩ ነቢይ መርዝ አለበት አሉ:: በበሶ ቆቶ አቅንው ስጣቸው አለው፤ አላትኖ ቢሰጣቸው ምሬቱ ጠፍቶ ጣፍጦላቸው ተመግበውታል 2 ነገ ምዕ 4 ምሳሌነቱን ከዘመን ሰብከት እይ::

በጊዜው የነበረ የሶርያ ሊቀ ሠራዊት ንዕማን በፈረስ በሠረገላ ሆኖ ሠራዊት አስከትሎ ወደርሱ መጣ በለምጽ ቢሉ ሰውነቱ በለምጽ ነዶ ነበርና ሚስቱ ሲገባ ሲወጣ እያየችው ታዝን ነበር ከእስራኤል የተማረከች እገልጋይ ነበረችበት በሀገራችን ደዌይ የሚፈውሱ ሙት የሚያስነሡ ነቢያት እሉ ከርሱ ዘንድ ቢሄድ ይድን ነበር ብላ መከረቻት:: ነገረችው እርሱም ንጉሡ ወልደ አዴር አፈውስ ለንዕማን ቀልጼሮ ወላጁ ንዕማንን እንዲፈውስ አድርገው ብሎ ለእስራኤሉ ንጉሥ ጽፎለት ወደ ኢየሩሳሌም መጣ ንጉሡም መልእክቱን አንብቦ እሁን በምን ልጣው ብሎ ነው እንጂ እኔ መግደል ማዳን የምችል አምላክ ነኝን? አለ ኤልሳዕ ይህ ተገለጸለት ወደኔ ላከው ብሎ ልኮበት በዚህ ምክንያት መጥቷል:: ሂና ከደጅ ቆሞ ሳለ በዮርዳኖስ ውኃ 7 ጊዜ ተጠመቅ አለው ነቢይ ሲል በቃሉ ተናገር ወእጁ ላዕ የሚፈውስ መስሎኝ እንጂ ውኃማ በሀገሬስ መች እጣው ብሎ ተቆጥቶ መለስ ሲል ነቢየ እግዚአብሔር የተናገረው አይቀርምና ያለህን አድርግ አሉት ሄዶ 7 ጊዜ ተጠምቆ ድኗል::

በሚሄድም ጊዜ 10 መክሊት ብር 6 ሺህ ወቄት ወርቅ 10 እጀ ጠባብ ይዞ ይህን ተቀበለኝ አለው እግዚአብሔር ሰጸጋ እግዚአብሔር በወርቅ መብብሩር የእግዚአብሔርን ስጦታ በወርቅ በብር አሽጦማለሁ ብሎ እንቢ አለ:: እንኪያስ ምን ላደርግልህ አለው:: በእግዚአብሔር እምነ ለሱም ብዙ ሰገድ አለው:: ለዚህም ጌታዬ ከቤተ ጣዖት ሲገባ እኔን አስከትሎ ሲሰግድ ትከሻዬን ተደግፎ ነው ከፈቀድከልኝ ግን አፈር ጭኜ ወስጄ መደብ አሠርቼ እሱ ለጣዖቱ ሲሰግድ እኔ ስመ እግዚአብሔር ጠርቼ ልሰገድ አለው:: ይሁን አለው ጭኖ ወስዶ መደብ አሠርቶ ስመ እግዚአብሔር እየጠራ የሚሰግድ ሆኗል::

ግያዝ ወርቅ ብር አልቀበልም ሲል አይቶ ነበርና ሲሄድ ከወደ ኋላ ተከትሎ ነቢየ እግዚአብሔር እንግዶች መጥተውበት ወርቅ ብር ላክልኝ ብሏል አለው:: እደሆንም ቢለኝ እንጂ ሁሉንስ ውሰድ ብዬ አልነበረምን ብሎ 2 መክሊት ብር 2 እጀ ጠባብ ሠጠው:: ሲመለስ ከወዴት መጣህ አለው እዚሁ ነበርኩ አለ:: ንዕማን ሊቀበልህ ከሠረገላው ሲወርድ ልቤ ካንተ ጋራ አልሄደምን ከእግዚአብሔር ጸጋ ይልቅ ወርቅ ብር ሽተሀልና የርሱ ለምጽ ባንተና በቤተሰቦችህ ይሁን አለው በለምጽ ተመቶ እንደ በረዶ ነጭ ሆኖ ወጥቷል:: 2 ነገ ምዕ 5

ደቂቀ ነቢያት ቦታ ጠበበን በዮርዳኖስ ቤት ሠርተን እንኑር አሉት እሺ ይሁን አላቸው:: በዮርዳኖስ ዳርቻ እንጨት ሲቆርጡ አንዱ ምሣሩ ከባሕሩ ገባበት የተበደርኩት ምሣር ገባ ብሎ አዘነ ኤልሳዕ ቅርፊት ልጦ በገባበት በኩል ቢጥል የማይዘቅጠው ቅርፊት ዘቅጦ የሚዘቅጠው ምሣር ተንሳፈፈ ያውልህ ብሉት እጁን ዘርግቶ ወሰደታል::

ከዚህ በኋላ ወልደ አዴር ንጉሠ ሶርያ እስራኤልን ሊጣላ ምሽግ መሽጉ ተቀመጠ:: ኤልሳዕ የእስራኤልን ንጉሥ በዚህ ሂድ በዚህ አትሂድ ብሎ ላከበት ያም የማይሆንለት ቢሆን ምሥጢር የሚያወጣ አለን? አለ:: የምታስበውን የምትናገሩውን እያወቀ የሚነግረው ነቢዩ ኤልሳዕ ነው አሉት ይላቸሁ አምጡልኝ ብሎ ሠራዊቱን ሰደደ:: ግያዝ በፈረሰና በሠረገላ ሆነው ከበዋቸው ቢያይ ደነገጠ ኤልሳዕ ከኛ ጋር ያሉት ይበዛሉ አለው ቢመጣ በእነርሱ ወገን መላእክት በሠረገላ እሳት ሆነው ታዩት:: ኤልሳዕ ይህ ሕዝብ ዕውር ይሁን ብሎ ወደ ጌታ አመለከተ:: ሁላቸውም ታወሩ:: ሄዶ ወዴት ትሄዳላችሁ ማንንስ ትፈልጋላችሁ? አላቸው:: የምንሄደው ደደታን የምንፈልገው ኤልሳዕን ነው አሉት:: እንኪያስ መንገድ ስታሳስቱ ብሎ እየመራ በማርያ አድርሶ ዓይናቸውን የሚያዩ ይሁኑ ብሎ ጸለየ፤ አዩ:: የእስራኤል ንጉሥ አባቴ ልግደላቸውን? አለው:: የሚበሉት የሚጠጡትን ስጣቸው እንጂ ክፉ አታድርጋባቸው አለው:: ኢትግላ ለእኩይ በእኩይ የምትል ሕግ ወንጌል እንድትሠራ አውቆ ጠላቶቹን አብልቶ አጠጥቶ ሸኝቷቸዋል:: እነዚያም ጠላቱን አገኝቶ አብልቶ አጠጥቶ የሚሸኝ አለን ብለው እያደነቁ ወደሀገራቸው ተመልሰው ብዙ ዘመን ሳይጣሉ ኖረዋል::
ኤልሳዕም እንዲህ ባለ ግብር 50 ዘመን አስተምሮ በክብር ዐርፏል ካረፈም በኋላ እስራኤል በሞአባውያን የተገደለ የአንድ ሰው በድን ወስደው ከመቃብሩ ቢያኖሩት ተነሥቷል::
2 ነገ 13:20

ሰኔ 21 ቅዳሴ ቤታ ለእግዝእትነ

በሰኔ 20 ቀን የተተረከውን ከገጽ ________ ተመልከት

ሰኔ 23 ሰሎሞን ንጉሥ /ከ983 - 931 ዓ.ዓ/

ሰሎሞን ማለት መስተሳልም ማለት ነው:: አባቱ ዳዊት እስራኤልን 40 ዘመን ገዝቶ አረጀ፤ አዶንያስ ወልደ አጊት /የዳዊት ልጅ ነው/ አባቴ ዳዊት አረጀ አቤሴሎምም ሞተ ወንድሜ ሰሎሞን እንዳይነግሥ ሕፃን ነው የአባቴ መንግሥት ለኔ ይገባል ብሎ ከኢዮአብ ጋር ሰሙ ለኔ መብቱ ላንተ ይሁን ብሎ መክሮ ቅብዐ መንግሥት የሚቀባው አብያታርን ይዞ በኬልቴ: ዘዘኤልቴ: በዓል አድርጎ ነገ ሥሁ አለ::

ነቢዩ ናታን የአዶንያስ መንግሥት እንደማይጸና አውቆ የሰሎሞንን እናት ቤርሳቤህን /የኦርዮ ሚስት የነበረች ኋላ ዳዊት ያገባት እስራኤላዊት/ ኢስማዕኪኑ ከመ ነግሠ አዶንያስ ወልደ አጊት: አዶንያስ እንደነገሠ አልሰማሽምን አሁንም ሂደሽ ንጉሥን ተሐሰውኑ ቃልከ እግዚእየ ከመ ሰሎሞን ወልድየ ይነግሥ እምድኅሬየ በዪው እኔም መጥቼ ነገርሽን አጸናልሻለሁ አላት ሄዳ ጌታዬ ከኔ በኋላ ልጄ ሰሎሞን ይነግሣል ያልከው ቃልህ ታበለን? አለችው:: ወዲያውም ናታን መጣ እሷ ወደ እልፍኝ ገባች:: ምነው ደገኛ ልጅህ አዶንያስ ሲነግሥ ሳትጠራኝ ቀረህ? አለው ነገራቸው አንድ እንደሆነ አውቆ ቤርሳቤህን አስጠርቶ ሕያው እግዚአብሔርን ከኔ በኋላ ልጄ ሰሎሞን ይነግሣል አላት:: ዕለቱንም ነቢዩ ናታንን ካህኑ ሳዶቅን ብንያስ ወልደ ዮዳኤን ኬልቴ: ፌልቴ: የሚባሉ ጭፍሮቹን ጠርቶ በበቅሎዬ አስቀምጣችሁ ግዮን ወደሚባል መናፈሻ ወስዳችሁ ቀብታችሁ አንግሡት አላቸው ወስደው ቀብተው አነገሡት ሕዝቡም ሕያው ወልደ ንጉሥ ሺህ ዓመት ያንግሥህ እያሉ በዕልልታ በሆታ ተቀበሉት::
የአብያታር ልጅ አኪማሆስ አባቱን ከነገር ሊያድን ወደ እነ አዶንያስ ሄዶ የሆነውን ነገራቸው ወእንዘ ይሠረቁ ጽዋዓሁ ለአዶንያስ ይላል ታዳሚዎቹ አንድ አንድ እያሉ ከድተው ከሰሎሞን ገብተዋል:: አዶንያስ ኢዮአብና አብያታር ግን ላቅርንተ ምሥዋዕ ይዘው ተማጸኑ ሰሎሞን ለጊዜው ምንም አላላቸውም::
ሰሎሞን ወደ ቤተ መንግሥት ሲደርስ ዳዊት ከሁሉ አስቀምጦ እጁን በራሱ ጭኖ እግዚኦ ኩነኔከ ሀቦ ለንጉሥ አቤቱ ፍርድህን ለንጉሥ ስጥ፤ ጽድቅህንም ለንጉሥ ልጅ ብሎ ጸለየለት፤

ሁሉን ያስቀመጠ አምላክህ እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን ብላ አመሰገነች::
ግብር ሲመለስ ወደ ማረፊያዬ ሂጂ እንዳርፍ አስናብተኝ አለችው:: ዛሬማ ከዚህ እደሪ እንጂ ለምን ትሄጃለሽ? አላት ድንግል ስለሆንኩ በዚህ ለማደር እፈራለሁ ድንግልናዬንም ካልጠበቅሁ አባቴ ከሕዝቡ ጋር የገባው ቃል ኪዳን ይፈርሳል አለች:: ስለምን? አላት ጥንቱን የሀገራችን ሰዎች ንጉሥ ነው እያሉ 400 ዘመን ለዘንዶ ሲገብሩ ይኖሩ ነበር የእኔ አባት አንጋበስ ዘንዶውን ገድሉ ነገሠ:: በፍጻሜ ዘመኑ ሕዝቡን አረጀሁኝ ከኔ በኋላ ልጆቼን እንድታነግሡልኝ ቃል ግቡልኝ አላቸው እነርሱም ወንድ ልጅህ ወንድም ባይኖር ወንድ ሳታውቅ ሴት ልጅህን እናነግሣለን አሉት እሱም ሲሞት እኔን አነገሡኝ አለችው:: እንዲህስ ከሆነ ተላልፌ አልነካሽም አላት:: ማልልኝ አለችው እንቺም ከሀብቴ ከንብረቴ እንዳትነኪብኝ ማይልኝ አላት ጥበበኛ ስትሆን እንዲህ ያለ ተራ ነገር ትናገራለህን ወርቅ ብር በሀገሬ ሞልቷል ወጸንተ መምጣቴ ጥበብህን ላይ እንጂ ወርቅ ብር ፈልጌ ነውን?አለችው፡ ግድየለም ማይልኝ አላት ማለችለት፡ እሱም አስቀድሞ መሐላ ላያፈርስ ማለ:: ደንገጡሯን ይዛ ተኛች::
ተቂት ተኝታ ውኃ ጠማት ውኃ ጠማኝ ከኮሰኮሰኝ ቀድተሽ አምጪልኝ አለቻት ሰሎሞን ሲያንቀላፋ ዓይኑን ይገልጻል ሲነቃ ዓይኑን ይከድናል:: ዓይኑን ገልጾ ብታየው ንጉሥ ያየኛል አለቻት ሁለተኛ ጠምቶኛል አምጪልኝ አለቻት አይሆንም ያያል አለቻት:: ሶስተኛ አሁንስ አያይም አምጪልኝ አለች ሰሎሞን ከእንቅልፉ ነቅቶ ዓይኑን ከድኖ ነበር:: የተኛ መሰለች ቀድታ ስጠቻት ስትጠጣ እጇን ይዞ ምነው መሐላሽን አፈረስሽ? አላት ውኃ ቢጠጡ መሐላ ይፈርሳልን አለችው ምድር በውኃ ላይ ጸንታለች አትክልት አዝርዕት ሰዕዋት በውኃ ይበቅላሉ ያብባሉ ደግሞም እንጂ ውኃ ቢጠጡት ያረካል ቢታጠቡበት ያነጻል: ታዲያ ከዚህ የበለጠ ምን ሀብት አለ? አላት በዚህ ተረታች አብረው አደሩ::
በምትሄድ ጊዜ ጸንሻለሁና በወለድሁ ጊዜ ሴት ወይም ወንድ መሆኑን እንዳስታውቅህ ምልክት ስጠኝ አለችው ወንድ የወለድሽ እንደሆነ ይህን ላኪልኝ ብሎ የወርቅ ቀለበት ሴት ከሆነችም ይህን ላኪልኝ ብሎ የብር ቀለበት ሰጣት:: ይህንንም ምክንያት አድርገሽ ለእግዚአብሔር ስገጂ ብሎ ከታቦተ ጽዮን ሀብት 1 መጋረጃ ሰጣት፡

ይህን ይዛ በክብር በመገረግ ወደ ሀገሯ ተመለሰች:: ስትሄድም ዓምደ ብርሃን ተከትሏት ሲሄድ አይቶ ክብር ወደ ኢትዮጵያ ሄደ ብሏል::
መቀዕለ ጽንሷ ሲፈጸም ወንድ ልጅ ወለደች:: ስሙንም ዕብነሐኪም አለችው የጠቢብ ልጅ ማለት ነው:: የምስራቹንም የወርቁን ቀለበት ላከችለት:: ወንድ ልጅ አገኘሁ ብሎ ደስ አለው አደታችሁት ኑ ብሎም ባለሟሎቹን ብዙ ወርቅና ብር አሲዞ ላከ::
ዕብነ ሐኪም 19 ዓመት ሲሆነው አባቱን ሊያይ ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ ሰሎሞን መኳንንት መሳፍንቱን ልጁን ተቀበሉ ብሎ ልብሰ መንግሥቱን፣ ዘውዱንና የሚቀመጥበትን ሠረገላ አሲዞ ላከ ልብሰ መንግሥቱን ለብሶ ዘውዱን ደፍቶ በሠረገላው ሆኖ ሲገባ መልኩ አባቱን ይመስል ነበርና ንጉሥ ወዴት ሄዶ ነበር? አሉ ሲደርስም ምኒልክ እንደምን ዋልህ እንደምን አለህ ብሎ ሳመው ከዚህ በኋላ ስሙ ምኒልክ ተብሏል:: ምን ያምር ማለት ነው::
ከዚህ በኋላ ምኒልክ ሲወጣ ሰሎሞን እየመሰላቸው ተከትለውት ይወጣሉ ሲገባ ይገባሉ:: ይህ የሚያስቸግራቸው ቢሆን ለሁለት ጌታ መገዛት አይቻለንምና አንግሠህ ወደናቱ ሀገር ላከው አሉት:: እኔን የበኩር ልጄን ላክ ካላችሁኝ እናንተም ወንድም ሆነ ሴት የበኩር የበኩር ልጆቻችሁን ከልጄ ጋራ ትልካላችሁ አላቸው እሺ ይሁን አሉ:: ሊቀ ካህናቱ ሳዶቅ ልጁ አዛርያስን ሠጠ:: ሌሎቹም እንዲሁ የበኩር ልጆቻቸውን ሠጡ:: የካህናቱ ልጆች ሂዱ ካላችሁን ምክንያት አድርገን ለእግዚአብሔር እንሰግድበት ዘንድ ከታቦተ ጽዮን ሀብት አንዱን ስጡን አሉ:: የታቦተ ጽዮን የውስጠኛው ልብስ ይሰጣችሁ አላቸው:: እነርሱ ግን ከታቦተ ጽዮን መለየት አልወደዱምና አንድ አንድ ወቄት ወርቅ አዋጥተው በታቦተ ጽዮን ልክ ታቦት ቀርጸው በወርቅ ለብጠው በታቦተ ጽዮን ቦታ አኑረው ታቦተ ጽዮንን ይዘው ሄዱ::
ከተማውን ለቀው ሲወጡ ኢየሩሳሌም ተናወጠች:: ሰሎሞን ሳዶቅን አስጠርቶ ይህ ልጅ በተፀነሰበት ሌሊት ፀሐይ ከምድር ወርዳ በኢየሩሳሌም ተቂት ስታበራ አይቻለሁ አሁንም ሂደህ ታቦተ ጽዮን መኖሯን ተመልከት አለው:: ቢገባ ልጆቻቸው የሠሯትን እንጂ ታቦተ ጽዮንን አጣት ደንግጦ ሄዶ የለችም ወስደዋታል አለው:: እንደ ነፋስ በሚበር ሠረገላ ሆኖ ተከተላቸው በ3 ቀን የሄዱትን በ1 ቀን ተጉዞ ዜናቸውን ቢጠይቅ ከኛ በሠለስት ተነሡ

እርሱንም ኩንን በጽድቅ ሕዝብህን በእውነት ገዛ /ምራ/ ብሎ መከረው፤ ሕዝቡንም የ12 ዓመት ሕፃን ሾመብን እንዳይሉ ወይ ወርድ ከመ ጠል ውስተ ፀምር - ጠል ከሰማይ ወርዶ ከምድር እንዲስማማ ነገሩ ምክሩ ከሰው ልቡና ይስማማልና ብሎ መክሯቸዋል:: 1 ነገ ምዕ 1 መዝ 71-1

ከዚህ በኋላ ዳዊት ዐረፈ እርሱም «ልጄ ሰው ሁን» /1ነገ/ ያለውን የአባቱን ቃል እያሰበ ደኃ እንዳይበድል ፍርድ እንዳያጓድል እየተጠነቀቀ መንግሥቱን ይመራ ጀመር:: በገባኦን መሥዋዕት የሠዋ ዕለት ጌታ ምን ትሻለህ?ሲለው፤ እሱም ጌታ ሆይ ደኃ እንዳልበድል ፍርድ እንዳላጓድል ጥበብንና ማስተዋልን ስጠኝ ቢለው እውነት እልሀለሁ ካንተ በፊት የነበሩ ያላገኙትን ካንተም በኋላ የሚነሡ የማያገኙትን ጥበብ ሠጥቼሀለሁ ያልለመንከኝ ሀብትንም የሚመስልህ የሌለ አድርጌ ሠጥቼሀለሁ:: እንደ አባትህ እንደ ዳዊት በፍጹም ልብህ ከኔ ጋር ብትሆን እኔም ካንተ ጋራ እሆናለሁ፤ ሲለው ራዕይ አዩ:: እንዲያውም ድንቅ ጥበብንና ማስተዋልን አገኘ:: 1 ነገ 3 4:15
አንድ ቀን ንጉሥ ፍረድልን ብለው ሁለት ሴቶች ቀረቡ ምን ሆናችኋል አላቸው አንዲቷ ንጉሥ ፍርድ ልብስ ሁለታችን ካንድ ቤት እንኖራለን፤ እኔ በወለድሁ በ3ኛ ቀን እርሷም ወለደች፤ እንቅልፍ ሲይዛት ሕፃኑን ተጭና ገደለችው፤ እኔም ተኝቼ ሳለሁ ልጄን ወስዳ የሷን ልጅ ከኔ አስተኛችው ልጄን አስመልሰኝ አለችው ሁለተኛይቱም ሞቷል የሞተው የርሷ ነው ይህ ልጅ ነው አለች:: እርሱም የሞተውን አንድ ጊዜ ሞቷል ይሁን ያለውን ከፍላችሁ ሁሉ መንፈቀ ለዛቲ ወመንፈቀ ለእንታክቲ አኮ ሊታውን ለዚህች እኩሌታውን ደግሞ ለዚያች ስጡ ብሎ አዘዘ ያች አልወለደችውምና እሺ ብላ እጅ ነሳች ይህችኛዋ ግን ልጇ ከሚሞት እሷ ትውሰደው አለች:: የዚያች ልጅ እንዳልሆነ አውቆ ለዚህች ሰጥቷታል፡ እስራኤልም ጥበቡን አደነቀዋል:: 1ነገ 3:16- 28
አባቱ ዳዊት ቤተ መቅደስ ልሥራ ባለ ጊዜ አኮ አንተ ዘትነድቅ ሊተ ቤተ አላ ወልድከ ዘወጽአ እምሐቌከ ውእቱ ይነድቅ ሊተ ቤተ በስምየ ከአብራክህ የተከፈለ ልጅህ በስሜ ቤት ይሠራልኛል ብሎት ነበርና /2 ሳሙ 2:12/ ሰሎሞን ጌታ ጥበቡን ገልጦለት ከጢሮስ ዝግባና ጽድ አያስመጣ ቤተ መቅደስ ሠርቷል::

በ586 ዓ.ዓ ስለምናሶር ያፈረሰው የመጀመሪያው ቤተ መቅደስ ነው

ቤተ መንግሥቱንም አብሮ በ20 ዓመት ውስጥ ሠርቷል:: 2 ዜና ፎ:1

መንግሥቱን አጽንቶ ግዛቱን አስፋፍቶ የዳዊት ከተማ ጽዮንን አድሶ አስፍቶ ሲኖር በ4ቱ መዓዘናት ያሉ ነገሥታት ጥበቡን ለማየት እየመጡ ይጠይቁት እጅ መንሻም ይሰጡት ነበር:: ከነዚህም አንዷ የሀገራችን ንግሥት የነበረች ማክዳ ነበረች:: ታምሪን የተባለ ኢትዮጵያዊ ጥበቡን ነገሯት ልታየው ወደደች

ክብረ ነገሥት ገጽ 12

ለንግድ በሚሄድ ጊዜ እኔ ወደርሱ እሄዳለሁና መንገድ እንድትመራኝ በቶሎ ተመለስ ብላ ለሰሎሞን የሚሰጥ ለርሱም የሚሆን ብዙ ወርቅና ብር ሰጠችው:: እርሱም ኢየሩሳሌም ደርሶ መልእክቱን አድርሶ በቶሎ ተመለሰ በሀገራችን ብቻ ያለ ሽቱ የዝሆን ጥርስ ዕንቁ፤ ወርቅና ብር ይዛ 500 ደናግል አስከትላ ሄደች:: ከእግሯ ላይ እንደ በግ እንደ ፍየል ዘርዛራ ሰኰና ነበረባት ስትገባ ከደጁ ወድቆ የነበረ ግንድ ቢነካው ተቀርፎ ወድቆላታል:: ግብሬ ተአምርነቱን ተረድተው እሱ በ 1 ብር እርሷም በ 1 ብር ለብጠው ከቤተ መዛግብት ተቀመጠ

ከርሱ በኋላ የተነሱ 28 ነገሥታት በ1 በ1 ብር ለብጠውት አይሁድ 30 ውን ብር ለይሁዳ መጥተው በዓንዱ ጌታን ለሽጠውታል::

ወደሀገሯም እስክትመለስ ድረስ የሰባ እያረደ የጠራ እያወረደ ብማረ ቦታ አስቀምጧታል::
አንድ ቀን ግብር አግብቶ ካዳራሽ ተገኝቶ በቀኝ አስቀመጣት መኳንንት መሳፍንቱ ወይዛዝርቱ እንዳያዩአት መንጦላዕተ መጽሔት ጋረደላት እርሷ ግን ታያቸዋለች ምግቧን ከርሱ ጋራ ጋለታ የአሳላፊዎቹን ሥርዓት የምግቡን ዓይነት ሌላውንም ጥበቡን ሁሉ አይታ ቀች ብዙም እንቆቅልሽ አምጥታ ጠየቀችው ወአልቦ ዘኢፈከረ ላቲ: ወተሠወረ እምኔሁ ይላል ሳይመልሳት ተሠውሮት የቀረ የለም ሁሉን መለሰላት ጥበብህን ነገረውኝ መጥቼ በዓይኔ እስካይ ድረስ አላመንሁም ነበር፤ አሁን ግን ከሰማሁት እጅግ የሚበልጥ ጥበብህ አየሁ አንተን በእስራኤል

ሊጸልም መረገውዎቹ ሊርበዎቹ በንጉሥ ያለ መሬት ለቀው ይታቆ ነበር ይህን ጊዜም የ7 ቀን ጉዞ ተጉዘው ይሆናል አሉት፤ እያዘነ ተመለሰ:: እኪያም ብንፈገረው መልሶ ለእኛቱ ይሰጠናል ብለው ፈርተው አልነገሩትም ነበር:: የምንገርህ አለ ለእኛቱ መልአክ እንዳትሰጠን ቃል ግባልን ብለው ቃል ካገቡ በኋላ በቤተ መቅደስ የነበሩ የልጆችና የጥቂቱ መኳንንትና ታቦተ ጽዮንን ይዘን መጥተናል አሉት:: ፈቃደ እግዚአብሔር እንጂ ቢሆን ነው ብሎ እጁን ደስ አለው::
ቢያርግም እናቱ 40 ቀን በበገ እያረደች የጠራ እያወረደች ታላቅ ፈንጠዝያ አድርጋለታለች ታቦተ ጽዮንንም በቤተ መቅደስ አኑራ አስተምሮባቸው ለሠራዊቱም ርስት ጉልት ሰጥታቸዋለች:: ክብ ነገ
ሰሎሞን የጌታ ጉባዔ ሰም የተቀረጸበት ገርግ ምንኩ ትእምርተ መንግሥቱ የሆነ ቀለበት ነበረው አንድ ቀን ከሁሉም አስቀምጦት ሳለ ሰይጣን ለምቀኝነት አያርፍምና ከሰሎሞን ጠቅለሎ ወስዶ ከባሕር ጣለው ሰሎሞን ሊገባ ሲል ሁሉን ጠብቂው አትገባም ብሎ ከለከለው:: እረ ሰሎሞን ነኝ ቢለው ሰይጣን በምትሐት እሱን መስሎ በሁሉ ተቀምጦ ነበርና ሰሎሞን በሁሉ ተቀምጦ ሰሎሞን ነኝ ትላለህን? ብሎ ገፍቶ አስወጣው እርሱም ወጥቶ በከተማው 2 ዓመት ያህል እየለመነ ሰነበተ አንድ ቀን ሰይጣን እየተከታተለ የለመን ልብ እያጸናበት የሚመግበው አጥቶ ከባሕር ሄዶ ዓሣ አጥማጆችን ለመነ:: እንዱ ይህ ዘብጦ ብሎ የሞተ ዓሣ ሣለለት ሆዱን ቢቀደው ቀለበቱን አገኘ ገርግ ምንኩ ትእምርተ መንግሥቱ ነውና በዚያ የነበሩት ንጉሥን ከዚህ ምን አመጣው እያሉ ከበው እጅ ነሥተው ከቤተ መንግሥቱ አደረሱት:: ሰይጣኑ ወጥቼ እሄዳለሁ ሲል እንግዲህማ ወዴት ትሄዳለህ ብሎ ምድር አስቆፍሮ ቀበረው እንዳይወጣም መርበብተ ሰሎሞን የሚባል ስመ አምላክ አትሞበታል:: ከዚህም ያደረሰው አንድ ቀን የራበው ችግረኛ ሲለምን ምን ሆኖ ነው ቢል ርቦት ብለውት በምጊዜት እድን ኋላም በመንግሥት ሆኖ ረሀብን እያውቅምና ረሀብ ደግሞ ምንድር ነውን? ብሎ ነበርና እንዲቀጣው ነው::
ኋላ ግን መፍቀሬ አንስት ሆነ 700 ሚስቶች 300 ቅምጦች አስቀምጦ እረማውያት የሆኑት ለጣዖት እንዲሠዋ ልቡን አስበለጡት ንጉሥ በመንግሥቱ ሲገዛበት እንደማይወድ ጌታም በአምላክነቱ ቢገዛበት አይወድምና መንግሥትህን ከልጅህ እጅ ከ12 እቀዳለሁ::

ለባሪያዬ ለዳዊት ስለማልኩት መሐላ ግን አንዱ እጅ ለልጅህና ለቤቱ ይሆናል አለው 1 ነገሥ.16.
በፍጻሜ ዘመኑ ንስሓ ገብቶ ይቅርታ ለመነ ጌታም ንስሓውን ተቀብሎ ኃጢአቱን ፋቀለት መርገም ያልወደቀባት ንጽሕት ዘር ከአዳም ባሕርይ ተከፍላ በሴት አካል ተቀርጻለች፤ ከሴት ሲወርድ ሲዋረድ በኖኅ በሴም ከሴምም ሲወርድ ሲዋረድ በአብርሃም በይስሐቅ በያዕቆብ፤ ከያዕቆብም ሲወርድ ሲዋረድ በዳዊት ከዳዊትም ባንተ ካንተም በሮብዓም አካል ተቀርጻለች ከርሷ አምላክ ይወለዳል እርሱም በሞቱ ዓለሙን ያድናል ብሎ የዓለምን የድኅነት ተስፋ ሌላውንም እስከ ምጽአት ድረስ የሚሆነውን ሁሉ ገልጾለታል:: ጥበባቱን ምሳሌያቱን ተግሣጻቱን በመጽሐፍ ጽፎ /አጽፎ/ በተወለደ በ52 በነገሠ በ40 ዓመቱ ዐርፏል::

ሰኔ 24 ሙሴ ጸሊም

አባት እናቱ ፀሐይን ያመልኩ ነበር፤ ኃጢአት በሠራ ጊዜ ተው አምላካችን ፀሐይ ይጣላሀል ይሉታል:: ፀሐይማ አምላክ ቢሆን እስከዛሬም ባቃጠለኝ ነበር ይላቸዋል:: አንድ ቀን ፀሐይና ጨረቃን የሚያፈሩትን እውነተኛውን አምላክ ባውቀው በወደድሁ አለ:: መንፈስ ቅዱስ አነሳስቶ ወደ ገዳመ አስቄጥስ ወሰደው ካህን ለተልዕኮ ሲገባ አይቶት ሊፈጀን የመጣ ነው ብሎ ፈራው:: እርሱ ሄዶ አምላክ ግን እንደሆን አስተምረኝ አለው ከመምህር ኢሲድሮስ አገናኘው:: አስተምረው አጥምቀው ለመዓርገ ምንኩስና አበቁት::
አርባ ዘመን ከሰው ተለይቶ በዓቱን ዘግቶ ከኖረ በኋላ በ500 መነኮሳት ላይ አበምኔትነት ተሾመ:: ቀን ቀን ሲያስተምር ይውላል፤ ሌሊት ሌሊት ከበረሀ ወርዶ እንጨት ሰብሮ ውኃ ቀድቶ ለየመነኮሳቱ በየደጃፋቸው ያኖርላቸዋል:: እርሱ መሆኑን አያውቁም ሰይጣን ለምቀኝነት አያርፍምና አንድ ሌሊት እንጨት ሰብሮ ውኃ ቀድቶ ሲመለስ:: በደንጊያ መህል አገዳውን መታው እርሱ ግን ጸብዕ መሆኑን ተረድቶ የበለጠ እንዲህ ባለ ትሩፋት የሚጋደል ሆኗል::
በኋላ በሚያደርጉ ጊዜ አባታችን መዓርገ ቅስና ተቀብለህ ናዘን ብለው ወደ ሊቀ ጳጳስ ይዘውት ሄዱ ሊቀ ጳጳሱ እንዲህ

ያለውን ጠጃራ ታመሙብኛችሁን አለ። ሥናየ ንብሩ ብከ አ እሊም ዘኅሉም ኀጢ መልክ የከፋ እንተ ጠጃራ ደግ አደረጉብህ እያለ ራሱን እየገሠጸ ወጣ። እመቤታችን ለሊቀጳጳሱ ተገልጻ መልኩ ቢጠቁር ልቡ ይነጻ የለምን ብላ ገሥጸችው ደግ አላደረግሁም ብሎ አስጠርቶ ሾመው። ይህም የእመቤታችን ቃል ኪዳኗ ዘማሚውን እንደ ድንግል ጉዮአን ጻድቅ የሚያደርግ መሆኑን ያስረዳል «ይትባረክ ጽጌኪ ማርያም ለልብየ ፍቅርኪ ዘከፈሉ፤ወእያር ጎቀ እምኔየ ለኪዳንኪ ማህሉ፤ ትምህርተ ኪዳንኪ ይሁብ ለዘማውያን ተደንግሎ» እንዳለ ደራሲ። የንስሓንም በቁጄት ይገልፃል ንስሓስ ትሬስዮ ለዘእበስ ከመዘኢአበሰ» እንዲል።

ከዚህ በኋላ ከደቀመዛሙርቱ 7ቱን አስከትሎ ወደ አባ መቃርስ ሄዶ ሳለ በርበር ገዳሙን ሊያቃጥሉ እነርሱንም ሊገድሉ መጡ። ከናንተ የፈራ ይሽሽ አለ። አባታችን አንተስ አትሸሽምን አሉት ሞት ፈርቼ ሰማዕትነት ጠልቼ እሸሻለሁን አለ። ወዲያው በርበር ደረሱ በኀልማሳነቱ ጊዜ ደም እፍስስ ነበርና ኢይነጽሕ ደም ዘእንበለደም፤ደም ያለ ደም አይነጻምና የኔም ደም ይፍሰስ ብሎ አንገቱን ለሰይፍ ሰጠ በሰማዕትነት ዐርፏል። ከደቀመዛሙርቱም 6ቱ እሱን ተከትለው አንገታቸውን ለሰይፍ እየሰጡ ሞቱ። አንዱ ግን ፈርቶ ከጥሻ ተደብቆ ነበር፤ መልአኩ ሰምንት አክሊላት አምጥቶ 7ቱን ለሰባቱ ሲያቀዳጃቸው አንዱ ከእጁ ሲቀር አይቶ ከተደበቀበት ወጥቶ በሰማዕትነት ሞቶ ተቀዳጅቷል።

➢ የነበረው በ 4ኛው ም.ዓ ድ/ልክ ነው።

የዘም ኀደኛየ የሉት ወዳጅ
የሆሁ አባ ሙሴ በራሱ ፈራጅ
ጠገሱ ታጥቦ ነጭ ከበረድ
በሰድቶ ነፍና ሲሄድ ቢራመድ
ሰይጣን ተመትቶ ሊያጠፋው ቢወድ
እረሙን ሊረዳ ቢመጣ ቢወርድ
ምኅዘን እንጂ በፈጣሪው ዘንድ

ሙሴ በነ ሰው ነው እውነተኛ ምዕመናን
ለእምነቱ ተገቶ ያፈሰሰ ደሙን
ጻድቅ ሆኖ ሳለ ፍቅሩም የበዛ
ሁሉ በደለኛ ሰው ነኝ ይል ነበረ
ምን በነ ብንመራ ከበደል ርቀን
ከቶ አይገባንም ልንል ጻድቃን ነን
በሥራችን ሁሉ ፍቅሩም በለሁን

ሰኔ 25 ይሁዳ ሐዋርያ /ረድእ/

ይሁዳ ማለት ታማኝ ማለት ነው። ቁጥሩ ከ 7ቱ አርድእት ነው የጌታ አሳዳጊ የዮሴፍ ልጅ የያዕቆብ ወንድም ነው። ማቴ 13:55 ይሁዳ 1:1

ጌታ «ሑሩ ወመሀሩ ውስተ ኩሉ አጽናፈ ምድር» ማቴ 28:19 ብሎ ደቀ መዛሙርቱን ወንጌልን ለዓለም እንዲሰብኩ ያዘዛቸውን እስቦ ሐዋርያትን መስሎ ሐዋርያትን አክሎ ዞሮ በማስተማር ብዙዎችን ከይሁዲነት ወደ ክርስቲያንነት ከአረማዊነት ወደ ምእመንነት መልሷል።

በፍፃሜ ዘመኑ በዓውያን ጸልተው ተመቅኝተው ከዝየ ቤት ጥለውት ሳለ ያስተማራቸው ምእመናን ከሃይማኖት እንዳይፋለሱ በኃጢአት እንዳይረክሱ ተግሣጽዊ መልእክት ጽፎ ልኮላቸዋል። በመጨረሻም በችንካር ተቸንክሮ በመስቀል ተሰቅሎ ዐርፏል።

ሰኔ 26 እያሱ ወልደ ነዌ

እያሱ ማለት መድኃኒት ማለት ነው ትውልዱ ከነገደ ኤፍሬም ነው አባቱ ነዌ የባላል። መምህሩ ሙሴ በምድረ ምእብ ካረፈ በኋላ ጌታ ባንተ አድሬ ሕዝቤ እስራኤልን ለወላጆቼ ለአብርሃም ለይስሐቅና ለያዕቆብ ወደ ማልሁላቸው ምድር አገባቸዋለሁና በርታ ጽና ከሃሬያኤ ከሙሴ ጋር እንደነበርሁ እንዲሁ ካንተ ጋር እሆናለሁ አለው። እርሱም ጠንክር ሕዝቡን ይመራ ያስተዳድር ጀመር።

ከኤብሮና በላዋንን ኢያሪኮን በለሉ ብሎ ላካቸው። ደጋውን ሲሰልሉ ሰንብተው እያሪኮ ደረሱ የኢያሪኮ ንጉሥ እስራኤል ከግብጽ መውጣታቸውን ሰምቶ ሰባት የብረት ቅጽር ቅጥር ይጥር ነበር። የሀገሩም ሰዎች ጠርጥረዋቸው ሊጣሏቸው መጡ። ረዓብ ራኬብ ከምትባል ዘማ ቤት ገብተው መውደን አዷት ከሰገነት አውጥታ በቀርከሃ ጠቅልላ አቆመቻቸው ተኪታትለው መጥተው የእስራኤል ሰዎች ከቤትሽ ገብተዋል አሏት። ቀራሽ ተምከው ወጋ ተንንዋተው ከናንተ ቀቲት ቀደም ብለው ወጥተው ሄዱ አለቻቸው፤ መንግሥቶቹን ለልእከቶች መመንግሥቶውን እምነውተኛ ተመለሰዋል። ንብታ ትብሎ ሀገሪን ወትቀትሉ ንጉሥታቲን ሀገሪችን ትግዙላችሁ ንጉሥታቱን ትገድላላችሁ ይህም ሊታወቅ ኃያላኑ ይዘሙሩ ለ50 ለ60 የሚከፈተውም የብረት በር በገዛ እጁ ሲከፈት ሲዘጋ ያድራል ነገር ግን ወገናቺ ተድላ ደስታ ሲያደርጉ

ብለው ሐሳ የተሳፈት
መንገዱ ነው ሰሌ ያዕቆብ በመንገድ
ጥትና መቅዳን በእግዚአብሔር ፊት
ጌታ ሊፈርድብን ፍርዱንም መናገት
ነፍሱን አስጨነቀች እኒህ ሰዎች ንፍሬት
እያለ ሊያሳዩ ብዙኅ ሲሰሉ ፊት

ነገ ሰበት ዓመት ቢዘረሩ
እንደም አሳቀው ሕዝቡ ከፍቶ
ከቤት ርቀን በነ እምወራን
የሰም ተድላ ደስታ ባደታላን
እንዝን ወንድሞች ለለዓለሞች
የምንታዩትን ቀኝን አስብን

ሲራ 28: 6፡3 መቃ 6:1

ሰኔ 30 ልደቱ ለዮሐንስ መጥምቅ

የተፀነሰው በቅዱስ ገብርኤል ብስራት መስከረም 26 ቀን ነው። በ6ኛው ወር እመቤታችን መልአኩ ኤልሳቤጥን እንተ እም እዝማድኪ ይዕቲኒ ጸንሰት ወረከበት ወልደ በልህቃቲሃ ወበርስአቲሃ ብሏት ነበርና ኤልሳቤጥን ልትጠይቃት መጣች ኤልሳቤጥ የሰላምታዋን ድምፅ ስትሰማ እንፈርጸ እሳል በውስተ ከርሥ ይዕል ጽንዕ በማኅፀኗ በገኧል። ኤልሳቤጥም መንፈስቅዱስ መልቶባት ቡሩክት አንቲ እምአንስት ከሴቶች ተለይተሽ የተባረክሽ ነሽ ወቡሩክ ፍሬ ከርሥኪ የማኅፀንሽም ፍሬ ቡሩክ ነው፤ ወምንት እነ ከመትምጽኢ ኀቤየ እሙ ለእግዚእየ - የጌታዬ እናት ወደኔ ትመጪ ዘንድ እኔ ምንድን ነኝ የሰላምታሽን ድምፅ ስሰማ ጽንሱ በማኅፀኔ በደስታ ዘለለና ወብፅዕት አንቲ እንተ ተአምኒ ከመ ይከውን ቃል ዘነገሩኪ እምኀበ እግዚአብሔር ከእግዚአብሔር ተልከው የነገሩሽን ቃል እንዲሆን የምታምኚ ንዕድ ክብርት ነሽ ብላ አመስግናታለች። እመቤታችንም ከርሷ ተቀብላ ተዐቢ ነፍስየ ለእግዚአብሔር ብላለች 3 ወርም ከርሷ ጋር ቆይታለች።

እመቤታችን ወደ ቤቷ ከተመለሰች በኋላ ብዙም ሳትቆይ በዚህ ዕለት ኤልሳቤጥ ወለደች በስምንተኛው ቀን ሊገዙሩት መጥተው ስሙን ማን እንበለው አሉ፤ የሐንስ ይባል አለች። አባቱ እምእዝማድኪ ቢ ዘስሙ ስሙ - ከመዶችሽ በዚህ ስም የተጠራ የለም። እንደምን ይሆናል ብለው ዘካርያስን ማን ቢባል ትወዳለህ አሉት ብዕርና ከርታስ ሰጡት። የሐንስ ይሰመይ ስሙ ብሎ 10ሩን ፈደላት ጽፎ እንደበቀ ተፈትቶለት ተናግሯል። ወዲያውም «ይትባረክ እግዚአብሔር አምላክ እስራኤል ዘተሠሃሎ ወገብረ መድኃኒተ ለሕዝበ ዚአሁ» ብሎ ጌታን አመስግኗል፤ ሕፃኑንም ወአንተኒ ሕፃን ነቢየ ልዑል ትሰመይ እስመ ትቀድም እግዚአብሔር ከመትጺሕ ፍኖቶ - አንተም ሕፃን የልዑል ነቢይ ትባላለህ መንገዱን ትጠርግ ዘንድ በእግዚአብሔር ፊት ትሄዳለህና ብሎ ትንቢት ተናግሮለታል። ሉቃ 1:39 – 79

➢ ይህ የተፈጸመው 5500ው ዘመን ሊፈጸም መንፈቅ ሲቀረው /በ1ዓ.ዓ አጋማሽ/ ነው።

ምዕራፍ 5

ሐምሌ 2 ታዲዎስ ሐዋርያ

